ՄՐԲՈՅ ՆՇԽԱՐ

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው።።

Copyright © 1997, 2003 Amha Asfaw

ⲕⲙⲩⲧ ⲁⲙⲁⲑⲙ
ⲩ ⲯⲏⲧ ⲅ-ⲡⲩⲩⲩⲫⲧ

ማዉጫ

መግቢያ	07
የገጣሚዎች ጉባኤ	11
አውራ ጎዳና 55 እና ጥላሁን ገሰሰ	16
ስምንተኛው ሺ	23
መች ይሆን?	30
የእስራኤል አምላክ	44
ጌታቸው	57
ስጥ እንግዴህ!!	62
ተዘራ	71
የኛይትዋ	98
የበረሀ ግጥሞች	103
መጠየቅ ያለብንስ እኛ!	115
ድሮ ቀረ	128
የማያ ልጆች እጣ	134
የአባቶች መደብ	147

መግቢያ

ጨርጫ፣ ጫት የመቃም ስርአት ነው። ከሁሉ አስቀድም ምርጥ ጫት መግዛት ያስፈልጋልና፣ አቃራው ተመርጠ ገራባው እንዳይጠብቀን ከሀረር የሚመጣ አውቶብስ ጫቱን የሚያራግፍበት ቦታ ቆመን መጠበቁ የሚሻል ይመስለኛል። አውቶብሱ ሲመጣ የናዝሬት ጋሪ ሁሉ ወደዚያ ይሸ-መጥጣል። ነጋዴዎቹ እንኩዋ ከአውቶብሱ ተራ ጫት ፈተው አይሸጡም፤ ወንድወሰን ግን ዋና ደንበኛቸው ስለሆነ ሊያስቀይሙት አይፈልጉምና፣ ገና ሀራራ የያዘው ቃሚ ሳያየው በፊት የአስር ብር ጫት እንገዛለን። ለወትሮው እንኩዋን የሁለት ብር ይበቃን ነበር፤ ዛሬ ግን እናንተን ስለጋበዝሁ ልጎዳ።

አፊዳ፣ ቤቱን ጠርጋ ፍራሹን አስተካክላ፣ ሻይ ጥዳ ትጠብቀናለች። ራበን ካልናትም፣ ቢያንስ ቅቤ የጠገበ ሽሮ አትነሳንም። ላስተዋውቃችሁ፣ ያ መሀመድ ይባላል፣ ከጥግ አቀርቅሮ የተቀመጠው። አይን አፋር ይመስል የል? መሀመድ መዝፈን ይወዳል። ያልተጠራበት ሰርግ ቤት ገብቶ ሲጨፍር የሚያነጋ ጀግና ነው። አይን አፋር? አይን አፋር ማይ ፉት*(My foot)* ይላል አሜሪካ።

ወንድ ወሰንን ተዋውቃችሁታል። እንደገና በደንብ ተዋወቁት። የቤቱ ባለቤት ነው። አፊዳም የሱ ሚስት ናት። ያቺ ፍራሽ ላይ የምትድህ ሚጢጢም የወንድ ወሰን ልጅ ናት። ስምዋ ኤደል ይባላል። በራፍ በተንኩዋኩዋ ቁጥር «አማ» ትል ነበር። አምሀ ማለትዋ ነው። የት ደርሳ ይሆን? አድጋ ተምራ ትልቅ ሰው ሆነች? ወይስ እስዋንም እንደአባትዋ አብዮት በላት? ወንድ ወሰን ለመጨረሻ ጊዜ የፃፈልኝ ደብዳቤ ላይ፣ «አንድ ሳምንት ያህል በራፍ በተንኩዋኩዋ ቁጥር "አማ" ስትል ቆይታ አሁን ግን

እየረሳችህ ነው።።» ብሎኝ ነበር። እኔ ግን አልረሳትም። ጫት ስንቅም ተወልዳ ጫት ፍራሽ ላይ ስትንከባለል ነበር ጥያት የመጣሁ። ለኔ አሁንም የምትታየኝ አንድ የጫት ቅጠል ይዛ፣ አባትዋና እኔ የባጥ የቆጡን ስናወራ፣ አንዴ እሱን አንዴ እኔን የምታይ ህፃን ናት። አንዳዴ ዞር ብየ ሳያት የምናወራው እንደሚገባት ሁሉ ሳቅ ትላለች። ወይም በዛችው በምታውቃት ቃል ከወሬው መሳተፍዋ ነው መሰለኝ «አማ» ትላለች፤ ልረሳት አልችልም።

ተቀመጡ! ተቀመጡ! ጫት ልትቅሙ መጥታችሁ ሌላ የጊዜ ማህደር ውስጥ ከተትኩዋችሁ። ያ ጌትየ ይባላል፣ ያ ደሞ ታደሰ በሽታ። ጌትየ የሂሳብ ተማሪ ነው። ካርታም ሆነ ዳማ ከሱ ጋር ተጫውቶ ለማሸነፍ ያስቸግራል። ታዴ ግን ዝምተኛ ነው። ጥግ ይዞ ጫት ሲቅም፣ አብሮን እንዳለ የምንረሳበት ጊዜ ብዙ ነው። የሚነበብ መፅሀፍ ካገኘማ እሱም እኛን ይረሳናል።

ምላሰኞቹ እኔና ወንድ ወሰን ነን። ኤደልም ታግዘናለች፣ አንዳንዴ በሳቅ፣ አንዳንዴም በለቅሶ። ዛሬም ከወትሮው የሚለይ አይመስለኝም፣ ከወንድ ወሰን ዝምተኛነት በስተቀር። አሁን ያለበት ቦታ ሌላ ቢቀር ጫት እንደሚኖር አልጠራጠርም።

ያሜሪካ አዋቂዎች፣ በተለይ እኛን በሚመለከት ጉዳይ በሁለት ሰአት ነው ሊቅ የሚሆኑት። የሱማሌን ህዝብ የሚበጠብጡት ጫት ያሰከራቸው ናቸው ብለው ሲያወሩ ያስቀኛል። የሚገርመው ደግሞ፣ ጫት ከቡና የበለጠ ጠባይን የመለወጥ ባህሪ የለውም ብለው ሀኪሞች ሲነግሩዋቸው ይውሉና ያሜሪካ ጋዜጠኞች የተነገራቸው ሁሉ እረስተው ያችኑ ውሸት ይደግማሉ። ብቻ ለነሱ እስከጣማቸው፣ ውሸቱ እውነት እስኪሆን ድረስ ያናፉታል። ከሁሉም ያሚያሳዝነው ግን አንዳንድ አበሾች ያን ተቀብለው ማናፈሳቸው ነው። የራሳቸው የሆነ ነገር ሁሉ

የሚያስጠላቸው አበሾች ሳይ ያመኛል። ስለነዚህ ሆድ ስለሚያቃጥሉ አበሾች አልፎ አልፎ ማሰባችን አይቀርምና ጫት ብቻ ሳይሆን ወተትም ገዝተን መምጣት ነበረብን።

እንግዴህ ይህ መፅሀፍ በርጫ የተባለበት ምክንያት፣ የማወራላችሁ አንዱ ካንዱ ጋር ስለማይያያዝ ነው። እንደጫት ወሬ ሁሉ አንዴ ስነፍጥረት ቀጥሎ ግጥም ከዚያ ፖለቲካ፤ ምንም ልናወራው የማንችለው ነገር የለም። ልጅ ፊት እንዳይባል ያለችው ኤደል ብቻ ናት፣ የሚያሳዝነኝ ነገር ቢኖር የዛሬው በርጫ ላይ የማወራው እኔ ብቻ መሆኔ ነው። ሀሳቤ አንዱ ካንዱ ሲቃረን ዝም ብሎ የማያሳልፈኝ ወንድወሰን እንኩዋን ዛሬ ተሸነፈ።

የወሬውን እውነተኝነት፣ የጊዜውን ቅደም ተከተል፣ ማ እንደሞተ፣ ማ ደግሞ በህይወት እንዳለ ለመከታተል ባትሞክሩ ጥሩ ነው፤ በርጫ ላይ፣ ታሪኩ ትንቢት፣ ትንቢቱ ታሪክ፣ ሙዋቹ ህያው፣ በህይወት ያለው ደግሞ በድን ይሆናልና። ደቡሮች ውሸት ብለው የሚጠሩት ሁሉ ለኛ ውበት ነው፤ ነገሮችን ከተለየ አቅጣጫ መመልከት፤ ምስጢራዊ ቀለማቸውን ማሳየት፤ ይህ ሁሉ ከበርጫ ውጭ ላሉ ፍጡሮች እውነታን የተመረከዘ አይደለም። ግን እውነታ ምንድን ነው? ይህ መሰረታዊ የበርጫ ጥያቄ ነው። ስለዚህ እስክንመረቅን ቢቆይ የተሻለ መልስ እናገኝለታለን።

ሄ! ሄ! ሙሉጌታ መጣ። ሙሉጌታ እህል ነጋዴ ነው። በረንዳው እንኩዋን ያባቱ ነው፣ ግን አብዛኛውን ስራ የሚሰራው እሱ ነው። አንዳንዴ እህል ለመግዛትና ለመሸጥ ጅጅጋ ድረስ ይወርዳል። ሀምሳ እና ስልሳ ሺ ብር ይዞ በባቡርና ባውቶቢስ የሚጉዋዝበት ጊዜ ብዙ ነበር፤ ግን ተሰርቆበት አያውቅም። ብልሀቱን ሲነግረን፤ ለምን እንደሚነግረን እንኩዋ አላውቅም፣ በኪሳችን ከአስር ብር በላይ ካለ ራሳችንን እንደቱጃር የምንቆጥር ሰዎች የስልሳ ሺ ብር አጠባበቅ ትምህርት ይሰጠናል። ለማንኛውም ስኩዋር

የሚሸጥበት የወረቀት ኪስ አለም አይደል? ገንዘቡን እሱ ውስጥ ይከትና በጆ ይዞት ባቡር ላይ ይሳፈራል። አንዳንዴ እንቅልፍ ሲወስደው መሬት ይወድቅበታል። ከባቡር ጣቢያ የገዛው ሙዝ የወደቀበት የሚመስላቸው የዋሆች አንስተው ይሰጡታል። ያ ነበር የሙሉጌታ ካዝና። ምናልባት ትምህርቱ እንዳሰብኩት ከንቱ ላይሆን ይችላል። «እንቅልፋችንን አጥተን የምንጠብቀው ነገር የሌባ አይን ያርፍበታልና፣ ያለንን ባደባባይ ካወጣን፣ ልባችንን ለባዳ ካሳየን፣ ለዝርፍያ እንጋለጣለን፣ መከላከያም አይኖረንም።» ማለቱ ይሆን?

ጫቱንም ቃመ፣ ሻዩንም ጠጡ። ከጫት ባህል ውስጥ የማልወደው ነገር ቢኖር ጨብሲ ብቻ ነውና ያን አታገኙም። ሚርቃናችሁን ለማብረድ ከመጠጥ ይልቅ ጥሩው መድሀኒት ወሬ ነው። ችግሩ ግን፣ ዛሬ ግጥም አንባቢውም ሆነ ተረት ተራቹ እኔው ብቻ መሆኔ ነው።

በሉ እንግዴህ አድምጡኝ፣ እንደፈረደባችሁ፣
ግጥሙም ይኸው፣ ተረቱም ይኸውላችሁ።

አምሀ አስፋው።
ታህሳስ ፩ ቀን ፲፱፻፺፭ አ.እ

ኒውዮርክ ጉባዔ

ኒውዮርሌንስ፣ ፈረንሳዮች የቆረቆሩት፣ ካሜሪካ ከተሞች ለየት ያለ ቦታ ነው። ኒውዮርሌንስን እወደዋለሁ። የምወደው ከሌሎች ከተሞች በመለየቱ ብቻ ሳይሆን፣ ጃዝ የሚባለው የጥቁር አሜሪካኖች ሙዚቃ ሌሊቱን ሙሉ የሚዘፈንበት፣ አሸሸ ገዳሜ ሲባል የሚታደርበት ቦታ በመሆኑም ጭምር ነው።

ባለፈው ሳምንት በኒውዮርሌንስ የማልፍበት ምክንያት ነበረኝ፣ ጃዜን ሳዳምጥ ለማደር ነበር ከቤቴ ወስኜ የተነሳሁት። ግን ሰው ማሰብ እንጅ መፈፀም አይችልምና፣ ያላቀድኩት ሁኔታ ነበር ከኒውዮርሌንስ ያጋጠመኝ። ከተማው ልገባ ፫ ማይሎች ሲቀሩኝ፣ ከአውራ ጎዳናው አጠገብ ከትልቅ ሰሌዳ ላይ የሚከተለውን ማስታወቂያ ተለጥፎ አየሁ።

«የኢትዮጵያ ገጣሚዎች ሆሳእና ከሚባለው፣ ፈረንሳይ ሰፈር ከሚገኘው ምግብ ቤት አዳራሽ ውስጥ የግጥም ጉባኤ ያካሂዳሉና፣ ኑና ግጥሙንም ምግቡንም ጠጁንም ጠላውንም ተጋበዙልን።» ይላል ባማርኛ።

ሆሳእናን አውቀዋለሁ። ግን በኒው ኦርሌንስ ሳልፍ፣ እዛ ሳልደርስ የማልፍበት ጊዜ ይበዛል። የዛሬው ቀን ግን የተለየ ነውና ሰተት ብየ ሆሳእና። እኔ ስደርስ አዳራሹ ጢም ብሎ ነበር። ከበራፉ አጠገብ የተቀመጡ ሰዎች ወንበር አስጠግቼ ጠረቤዛቸውን እንድጋራ ስለፈቀዱልኝ አመሰግኜ ከዛ ተቀመጥኩ። ቢራ መጣልኝና አንድ ሁለቴ ጎንጨት ካልኩ በሁዋላ አካባቢውን መቃኘት ጀመርኩ።

የክብር እንግዶቹ ከፍ ካለ ቦታ ላይ ተቀምጠዋል። ሊቀ መንበሩ ሊናገሩ ነው መሰለኝ የድምፅ ማጉያውን በእጃቸው

ይቆረቁራሉ። አጠገቤ ካለው ጠረቤዛ ላይ ደግሞ፣ አንድ ከዚህ በፊት ያጋጠመኝ ዘረኛ ተቀምጦ ማየቴ «አለም እውነትም ትንሽ ሆናለችና!» አሰኘኝ።

«ክቡራትና ክቡራን!» አሉ ሊቀ መንበሩ፣ «ዛሬ የጉባኤያችን የመጨረሻው ቀን ስለሆነ፣ ጨዋታን ያዘለ መስተንግዶ ይዘንላችሁ ቀርበናል።» ቀጥለውም፣ «በጣም ልጅ ካልሆናችሁ በስተቀር፣ ይህችን ጉት (ቤት የማይመታ ግጥም) የምታስታውስዋት ይመስለኛል።» አሉና ከማህደራቸው አንድ ወረቀት አውጥተው፣ መነፅራቸውን ከአይናቸው ወደ አፍንጫቸው ጫፍ አንሸራተው፣

«ሱሬየን አጥቤ ከደጇ ባሰጣው፣
ተራምዳው አለፈች ወዳኛለች መሰል።»

ብለው አነበቡ። ተመልካቹም፣ ግጥሙን ብዙ ጊዜ ቢያዳምጠውም፣ ከዚህ በፊት እንዳልሰማው ሁሉ ሳቀ። ሊቀ መንበሩም «እኔ እንኩዋን ገጣሚ አይደለሁም። ግን ይህችን ማቃናት አያቅተኝም።» አሉና ሰዉ የተቃና ግጥም ያነባሉ ብሎ ሲጠብቅ የመጀመሪያውን እንግዳ አስተዋውቀው ተቀመጡ።

አቶ ከበደ ሚካኤል ከተቀመጡበት ሳይነሱ የድምፅ ማጉያው መሳሪያ ከፊታቸው ቀረበላቸው፣ የመጀመሪያው እንግዳ እርሳቸው ነበሩና። ከፊታቸው ያለውን ወረቀት በደከመ አይናቸው እየተመለከቱ፣ ወረቀቱን ከመነፅራቸው እያላቀቁ እያጋጠሙ የእይታቸውን ትክታ ሲያስተካሉ ከቆዩ በሁዋላ፣

«ሱሬየን አጥቤ ከደጇ ባሰጣው፣
ወዳኛለች መሰል አለፈች ተራምዳው።»

ብለው አነበቡ። ተመልካቹም ከመቀመጫው እየተነሳ አጨበጨበላቸው። ባውደ ንባብና በታሪክና-ምሳሌ

ያደጉትማ አይናቸው እንባ አቅርሮ ነበር። ጭብጨባው ጋብ ብሎ ተመልካቹ ወደመቀመጫው ሲመለስ፣ ሊቀ መንበሩ ሁለተኛውን እንግዳ፣ አቶ ፀጋየ ገብረ መድህንን አስተዋወቁ። እሳቸውም እንደተቀመጡ የሚከተለውን አነበቡ።

«ሱሬየን አጠብኩና፣ እንዲደርቅ ባሰጣው ከደጇ፣
ተረምዳው አለፈች ያች ውብ ልጅ፣
አፍቅራኝ ይሆን እንዴ?»

የሞቀ የአድናቆት ጭብጨባ ተደረገ። መጠጡ ያለቀበት ተመልካች ለማስሞላት እየተራወጠ ነበርና፣ ሊቀ መንበሩ ሶስተኛውን እንግዳ ሳያስተዋውቁ ትንሽ ጊዜ አሳለፉ። የሚቀጥሉት አንባቢ አቶ ሰለሞን ደሬሳ ነበሩ። እሳቸውም፣

«ታታ፣
አጠብ አጠብ፣
እሽት እሽት፣
ጨመቅ ጨመቅ፣
ሰጣ ሰጣ፣
እንዲደርቅ ሱሬየ ከሜዳ፣
ኤዲያልኝ ኤድያ፣
ታታ፣
ታታታ፣

እንጣጥ እንጣጥ፣
ሱሬየን ዘላ ዘጥ፣
ሲጢጢጢጢጥ . . .
ፍሬን እንደመያዝ፣
በፍቅሬ ባህር ላለመስመጥ፣

ታታ፣
ማነኝና።»

ብለው፤ በተለየ የአገጣጠም ዘዴያቸው ተመልካቹን አሳቁት። ከተመልካቹ አንዱ፣ ዘረኛው፣ መቁነጥነጥ ጀመረ። እንዲያውም ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ «ምነው እኛ መግጠም አይፈቀድልንም እንዴ?» ሲል ሊቀ መንበሩ ሰምተው ኖሮ፣ «ምነው ጌታየ ቢታገሱ! አቶ ሰይፉ ያንብቡና የርሶ ግጥም ቀጥሎ ይነበባል፣ እስከዚያው እባክዎ ይታገሱልን» ብለው ለመኑ። አቶ ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው፣ የመጨረሻው እንግዳ አንባቢ ነበሩና ሊቀ መንበሩ አስተዋውቀዋቸው፣ የድምፅ ማጉያው ተሰጣቸው። አቶ ሰይፉም ያገጣጠማቸውን ስልት እንደሚከተለው አሰሙ።

«አሰጣሁ ሱሬየን ከሜዳ፣
አጠብኩና፣
ከዚያም፣
አለፈችው ተራምዳ፣
የዛሬ ዘመን ልጅ፣
ወዳኛለች ለካ።»

ተመልካቹ አጨብጭቦ ሳይጨርስ ያ ቅብጥብጥ ተነስቶ፣ «እኛ አማራ ስላልሆን ነው ወይ ማንበብ የተከለከልነው?» ብሎ ጮኸ።

ሊቀ መንበሩ፣ ዘረኛው ሲቆም ከጣሪያው በቀጭኑ የሚወርደው ብርሀን ፊቱ ላይ ሲያርፍ፣ ደህና አርገው ተመልክተውት ኖሮ፣ «እንዴ! እንዴ! አንተ ነህ እንዴ? ደህና ነህ ልጄ? ደህና ነህ ገብረመድህን?» አሉ። ለካስ ሊቀመንበሩ ደጃዝማች አምሀ አበራ ኖረዋል።

«ምነው ደጃዝማች፣ ይችን ልጄ ልጄ የሚልዋትን ቢተውኝ። ዶሮን ሲያታልልዋት በመጫኛ ጣልዋት። አይደል የምትሉ?» አለ ገብረ መድህን።

«አዬ!» አሉ ደጃዝማች፣ እንደመተከዝ ብለው። «ገብረ መድህን ተረትና ምሳሌ ከጀመረ ማቆምያም የለው። እባክህ

ልጇ ስለዛች ቀውጢ ቀን ስትል፣ እኔም እንግዶቹም ደክሞናልና ግጥምህን አንብብና እንለያይበት።» አሉ።

ገብረ መድህን እንደመሳል ብሎ ጉሮሮውን አፀዳና ድምፁን ከፍ አድርጎ ግጥሙን ማንበብ ጀመረ።

«ሱሬያን አጥቤ ባሰጣው ከሜዳ፣
ረግጣው አለፈች፣ ያቺ ክፉ አማራ፣
ያውም እግርዋ ጭቃ፣
ያውም ልብዋ ጭቃ።»

እንኩዋንስ ተመልካቹ፣ አብረውት የተቀመጡት ጉዋደኞቹም አላጨበጨቡ። አጠፋህም፣ አለማህም ያለው የለም። ብቻ የደስታ የጨዋታ የነበረውን ቤት ሀዘን አጠላበት። ተመልካቹ ሂሳቡን እየከፈለ ሹክክ ብሎ ሲወጣ፣ የምዋቹን ቤተሰቦች፣ «እግዚአብሄር ያጥናችሁ»» እያለ ድንኩዋኑን የሚለቅ ለቀስተኛ እንጅ፣ የሰለሞን ደሬሳን ግጥም ያዳመጠ ጨርሶ አይመስልም ነበር።

እንግዴህ፣
የት እንሂድ፣ የት እንድረስ፣
እነዚህ ዘረኞች የሌሉበት፣
እነዚህ ዘረኞች ያልኖሩበት።
ሱሪያችንን አጥበን፣ አስጥተን ከሜዳ፣
ተሻግራው ስታልፍ፣ ወጣት ልጅ፣
ተሻግራው ስታልፍ፣ ኮረዳ፣
ደጉን የምናስብበት፣
ፍቅርዋን የምንመኝበት፣
የት እንሂድ፣ የት እንድረስ፣
እነዚህ ዘረኞች የሌሉበት።

፰ሙቴ ንጽዮ ሀምሳ ፰ምት እና ሻላሁን ገፋፋ

ሠደ ሰሜን ነበር የምግዋዘው፣ አይ-55 (I-55) እያሉ የሚጠሩትን መንገድ ተከትየ። የጥላሁንን አዲስ ክር እያዳመጥኩ፣ ነሸጥ ሲያደረንኝ አብሬ እየጮህኩ፣ እየዘፈንኩ፣ እንዲያ ነበር መንገዴ፣ ወደሰሜን ወደቤቴ።

ወገን አለኝ፣
ወንድም አለኝ፣
እህት አለኝ፣
እኔም አገር አለኝ።

አለ ጥላሁን። «Really!» አልኩ፣ እኔ ደሞ፣ አነጋገሬ የደበበ እሸቱን ቀልድ አስታወሰኝና ብቻየን እየሳቅሁ።

በኢትዮጵያ አየር መንገድ ተሳፍራችሁ ስትገዋዙ፣ አስተናጋጅዋን ትጠሩና፣ «እህት፣ የአውሮፕላኑ ክንፍ እየተቃጠለ ነው።» ትልዋታላችሁ። እስዋም፣ ፊትዋ ሳይለወጥ፣ ፈገግታዋ ሳይቀነስ፣ «Really!» ትላለች፤ ካይሮፕላኑ መቃጠል ይልቅ የእንግሊዘኛዋ ትክክለኛነት እያሳሰባት።»

ይል ነገር ደበበ። ደበበ ሳያደናቅፈኝ በፊት ወደጀመርኩት ጉዳይ ልመለስና፤

የቱ ነው ወንድሜ፣ ወገኔ?
ማናት እህቴ፣ አገሬ?
ባቀርብ ጥያቄ ብዬ፣
ለጥላሁን አይደለም፣

ለራሴ ለህሊናየ፣
መልሱ፣

ብዙም ክብደት የለው ለኔ፣
የት ነው ብሎ መጠየቅ፣ አገሬ፣
አገሬ ነውና ወገኔ።
ወገንም አይጠየቅ ማን ተብሎ፣
ስለሚገኝ ሚስጥሩ ሌላ ሆኖ፤
ናትና እህቴ ዘመዴ፣
ነውና ወንድሜ ወገኔ።

ስለዚህ መሰረቱ፣
ላገር ለወገን ድንጋጌ፣
መሆን አለበት መልሱ፣
የማናት እህቴ፣
የማነው ወንድሜ።

ይህም ቀላል ነው ለኔ፣
ነውና፣
የጥቁር ህዝብ እህቴ፣
የጥቁር ህዝብ ወንድሜ፣
የጥቁር ህዝብ ወገኔ፣
የጥቁር ህዝብ አገሬ።

ውርጌቻ ነው ቢል መንደሬ፣
አማኑኤል መቃብሬ፣
በጥቁርነቱ ካላመነ፣
በጥቁርነቱ ካልኮራ፣
ምኔም አይደል የኔ፤
ምኔም አይደል።

ከጥላሁን ጋር ጭቅጭቅ ትቼ ይልቅስ በዘፈኑ ብደሰት፣
አልኩና፣ አብሬ ወገን አለኝ፣ ወንድም አለኝ፣ .. ማለት

ጀመርኩ። «በየትኛው ድምፅ?» ትሉ ይሆናል፤ የዛሬን አያርገውና፣ ፀጉሬም፣ ድምፄም ሳይሸብት በፊት፣ ጥላሁን ስዘፍን ቢሰማኝ ኖሮ፣ የራሱ ቴፕ ይመስለው ነበር። ካላመናችሁኝ ሰይፉ ሀይለ ማርያምን ጠይቁት፤ ደንደስንም፣ ተፈራ ጉርሙንም፣ እቴቴ ሀዲስንም፣ ከበቡሽ ኪዳኔንም ብትጠይቅዋቸው ግድ የለኝም። አሁን ደግሞ አንድ የታወቀ የጀርመን ውሸታም ትዝ ብሎኝ ነበር፤ ግን ልተወው።

በቁጥር 55 የሚጠራው አገር አቁዋራጭ ጎዳና ሉዊዚያና ከሚባል ክፍለ ሀገር ተነስቶ ቺካጎ የሚሉት ከተማ ገብቶ ይጠፋል። የሚያልፍበት አገር ለአይን የሚታክት ሜዳ ነው። በዚያም ላይ መንገዱ ሰሞኑን ነው መሰለኝ የታደሰው፣ «አይ!! አንተ ደሞ እንደዚያ ያለ ጋቢ የለም።» አትበሉኝና፣ በነጭና በቢጫ ጥለት የተከፈፈ ጥቁር ጋቢ ይመስላል። «መንገዱስ መንገድ ነው!» አልኩ። የአለባቸውና የልመነህ ቀልድ ትዝ ብሎኝ።

መንገዱስ መንገድ ነው፣
ሲያሽቆለቁል በዝግታ፣
ሲያሻቅብም በዝግታ፣
ሲዞር ሲጠማዘዝ፣
በዝግታ በዝምታ።
የሚያጉዋጉዝ፣
መንገደኛውን አባብሎ፣
እንዳይወጣ፣
መንገድ ስቶ፣
ወገቡን አቅንቶ፣
አንተርሶ፣

መንገዱስ መንገድ ነው፤
ምን ያረጋል ብቻ፣
የሰው ንብረት፣
ከኛ ምድር የሌለው አቻ።

የመንገዱ እኛ አገር አለመኖር ሊያበሳጨኝ ሲቃጣው፣ ጥላሁን አይከዳሽም ልቤን ይዞ ደረሰልኝ። የዜማው ደራሲ፣ ተዘራ ሀይለ ሚካኤል፤ የግጥሙ ደራሲ፣ ሻምበል አፈወርቅ ዮሀንስ፤ ሙዚቃውን ማን እንደቀመረው እንጃ። ሙላቱ አስታጥቄ ቢሆን ግን ደስ ይለኝ ነበር። ዘፋኙ ጥላሁን ገሰሰ። ጥላሁን ገሰሰ!!!

ዮትዝታየ እናት የሰሜቴ እመቤት፣
የፍላንቴ ምንጭ የእድሌ ባለቤት።
የምታስታውሽኝ ያለፍኩትን ደስታ፣
አንች ብቻ እኮ ነሽ የኔ ልብ አለኝታ።
ያሳለፍነው ዘመን ደስታን ያየንበት፣
ተመልሶ ቢገኝ አሁን ምን አለበት።

በጣም ከምወዳቸው ዘፈኖች አንዱ በመሆኑ፣ ይሄ ዘፈን ሲዘፈን አብሬ ከመዝፈን በስተቀር ሌላ ትርፍ ነገር ማሰብ አልችልም ነበር። በተለይ ከዚህ የምትከተለዋን ሙዚቃ ሰምቼ ስለማልጠግባት የቴፑን ድምፅ ከፍ አደረግሁት። ግን በቴዎድሮስ ምትኩ ሳክስፎን ፋንታ አንድ የማይረባ የኤሌትሪክ ሙዚቃ መተካቱ አሳዘነኝ። ለጥላሁን ክብርም ሆነ ድምፅ ይህ የኤሌትሪክ ሙዚቃ አይስማማም። ጥላሁን እንደሌላው ሁሉ ኑሮውን ማሸነፍ እንዳለበት ይገባኛል። ግን የሀገር ቅርስ ነውና ባልባሌ የመንደር ሙዚቀኛ መታጀብ አልነበረበትም። «የሀገር ቅርስ አልከኝ?» ቢልስ ጥላሁን። ይሄ ደግሞ ወጋየሁ ንጋቱ ያለው ነው ተብሎ የተነገረኝን ቀልድ አስታወሰኝ።

ወጋየሁ ከጉዋደኞቹ ጋር ሲጠጣ፣ ከመሀላቸው አንዱ፣ «ወጋየሁ!» አለው፤ «አንተ እኮ መጠጣት የለብህም። ጤንነትህንና ክብርህን መጠበቅ ይገባሀል። አንተነትህ ያንተ ብቻ ሳይሆን የሀገርም ቅርስ ነው።» «ሂድ እባክህ!!» አለ፣

ወጋየሁ አዳምጠ ሲጨርስ፣ «ወጋየሁ የደን ሀብትና የዱር አራዊት መሰለህ እንዴ!::»

የቴወድሮስ ሳክስ ባይሆንም፣ ሙዚቃውን ጨርሶ አልጠላሁትም ነበርና ከጥላሁን ጋር ማንጎራጎሬን ቀጠልኩ::

ውበትሽን እንዳላይ ርቀት ማርኮታል፣
ልቤ ግን ብልጥ ነው መዝግቦ ይዞታል::
ባካል ባላይሽም ባሳብ ግስጋሴ፣
አልተነጣጠሉም ነፍስሽና ነፍሴ::
ያሳለፍነው ዘመን ደስታን ያየንበት፣
ተመልሶ ቢገኝ አሁን ምን አለበት::

ያች የምወዳት ሙዚቃ ስለምትከተል፣ ድምፄን የቴወድሮስን ሳክስ ለማስመሰል እየሞከርኩ ስጮህ ቤንዚኔም ቡናየም ወደማለቁ ስለተቃረቡ፣ አይ-55ትን ትቼ ውልቅ:: እንዳጋጣሚ ሆኖ ሜንፊስ-ቴናሲ የሚባል ከተማ ነበር የወጣሁት:: ሜንፊስን የማታውቁት ካላችሁ፣ የኤልቪስ ፕርስሊ አገር ነው:: ኤልቪስን የማታውቁ ካላችሁ ግን ልረዳችሁ አልችልም:: በነገራችን ላይ የነጭ ሙዚቃ ትወዳለህ ባትሉኝ የኤልቪስ ዘፈኖች ይጥሙኛል:: በተለይማ አትጨክኝ (Don't be cruel) የሚለው:: የኤልቪስን ዘፈኖች መውደዴ ያሳፍረኝ ነበር:: ግን አንድ ቀን፣ መሀመድ አሊ፣ ስለሀሊና ነፃነት የተሰራ ማስታወቂያ ላይ፣ «ጀምስ ብራውንን እና ኤልቪስ ፕሪስሊን የሚያክል ዘፋኝ የለም:: ከዚህ አስተሳሰቤ ሰማይ ዝቅ ምድር ከፍ ቢል ፍንክች አልልም::» ሲል ሰምቼው፣ ብቻየን አለመሆኔ ስለገባኝ ተፅናናሁ::

ቤንዚኔን ሞላሁ ቡናየን ጠጣሁና መንገዴን ቀጠልኩ፤ አሁንም የጥላሁንን ዘፈን እያዳመጥኩ:: «የጥላሁን ዘፈን

አያልቅም እንዴ?» ካላችሁ፣ አያልቅም። የምወደውን ዘፈን ደጋግሜ ስለምቀዳው፣ የክሩ አንድ ጎን በሙሉ «አይከዳሽም ልቤ» የሚለው ሙዚቃ ነበር።
ጥላሁን ቀጠለ፡

የተጫወትነውን ምን ጊዜም አልረሳም፣
እንዲህ ተለያይተን በናፍቆት ብከሳም።
አይከዳሽም ልቤ ሰው መክዳት አያውቅም፣
እስኪለያይ ድረስ ከለቅሶም ከሳቅም።
ያሳለፍነው ዘመን ደስታን ያየንበት፣
ተመልሶ ቢገኝ አሁን ምን አለበት።

ለመሆኑ ጥላሁን እድሜው ስንት ነው? ዜሮ ክፍል ሆኜ የዘፈናቸው ዘፈኖች ሁሉ ትዝ ይሉኛል። እኔ አርባወቼ እያለቁብኝ ነው። ለመሆኑ ጥላሁን እድሜው ስንት ነው? ለወሬው ነው እንጅ፣ የጥላሁንንስ እድሜ ያርዝምልን። ያለዚያማ የማንም አቦሬ አፍ ባንዳ ሲለፋደድብን ይውላል። «አሁን ማንን ለመሳደብ ነው አቦሬ አፍ የምትለው?» ማለት ካሰኛችሁ በሉ። እኔ ግን ፣ «አይ ወገኖቼ፣ እኔ ምን እሳደባለሁ፤ ነፍሱን ይማረውና ጳውሎስ ኞኞ ተሳድቦ ጨርሶታል።» እላችሁዋለሁ። ከየዘመኑ ገሸር ጋር አብሮ ለመብላት የሚያስችል ረጅም ምላስ የሚቀመጥበት ሰፊ አፍ እንደሚያስፈልገው፣ ጳውሎስ ለካ ቀደም ሲል ተረድቶት ነበር።

ለምንድን ነው ሰዎች፣
እንደቁም ሰአት መሪ የሚዋዥቁ ሁሌ፣
የቆሙበት መሰረት የሌላቸው፣
ወይም የቆሙለት እማኔ።

ለምንድን ነው ሰዎች፣
ከነፈሰው የሚነፍሱ፣
ጊዜያዊ ጥቅም ለማግኘት፣
የነገውን የሚረሱ፡፡
ለምንድነው?

አሁንስ እንቅልፌ መጣ፡፡ ለመሆኑ የት ነው ያለሁት? ሴንት ሉዊስ! እውነትም መንገዱ መንገድ ነው፡፡ ከጥላሁን ጋር ሲሆን ደግሞ፣ ጊዜውም ጊዜ ነው፡፡ በሉ ደህና እደሩ፡፡

ትምህርቱ ፲

ጀዲስ አበባ ይመስለኛል ያለሁት፡፡ ከተፈሪ መኮንን ት/ቤ (አሁን ምን እንደሚሉት እንጃ)፣ ድሮ ከትምህርት ቤት ስለቀቅ አደርገው እንደነበረው ሁሉ፣ የእግር ጉዞየን ጀመርኩ፤ በናዝሬት ት/ቤት በኩል አርባ ደረጃ የምትወስደውን ጠባብ መንገድ ተከትየ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የምሄደው እንኩዋን በ አራት ኪሎ በኩል ነበር፡፡ ዛሬ ግን ስራ ፈት ነኝና ረጅሙን መንገድ መረጥኩ፡፡

አርባ ደረጃን ወረድኩና፣ ባገር ፍቅር በኩል ወደ ጊዮርጊስ ዘለቅሁ፡፡ የምቸኩልበት ጉዳይ ከሌለኝ ጊዮርጊስ ገብቼ የአፈወርቅ ተክሌን ስእሎች መመልከት እወድ ነበር፡፡ አሁንም ያን ልማዴን ለማድረስ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ገባሁ፡፡ ጊዮርጊስ አያቸው የነበሩት ስእሎች የአፈወርቅ መሆናቸውን እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ለምን እንደሁ እንጃ፣ የአፈወርቅ ስእሎች መሆናቸው አሁንም ይሰማኛል፡፡ ምናልባት ስሙ ከስሩ ተፅፎ አይቼ፣ ረስቼው ይሆን?፡፡ ግን እንደዚያ ውብ የሆኑ ስእሎች፣ ያለዘበኛ አላፊ አግዳሚው እየገባ ያያቸው እንደነበረ ሳስበው ይገርመኛል፡፡

በተለይ ቅዳሴ ከሰማሁ የጊዮርጊስን ደረጃ ተደግፌ ሳላዳምጥ አላልፍም፡፡ ቅዳሴ ስሰማ፣ የቤተ ክርስቲያን እጣን ሲሸተኝ መንፈሴ ልገልፀው በማልችል ደስታ ይሞላል፡፡ የሀይማኖተኝነት ጉዳይ አይመስለኝም፤ ሀይማኖተኛ አይደለሁምና፡፡ ተፈሪ መኮንን፣ በረጅሙ የእረፍት ሰአታችን ጊዜ፣ የአሸናፊ ከበደ ልጆች «የህይወቴ ህይወትን» ሲዘምሩ ማዳመጥም ተመሳሳይ ደስታ ይሰጠኝ ነበር፡፡

ምናልባት፣

የዛፎቹ ጥላ፣ ያቀዘቀዘው ፀጥታ፤
ነፋስ ሲነካቸው የሚሰማው፣ የቅጠሎች ኮሽታ፣
የዝማሬው መልካም ቃና፣ የፀናፅሉ ድምፅ፣ የእጣኑ ሽታ፤
ሲቀላቀል የሚፈጥረው ውበት ይሆናል፤
የሚያሸብረው መንፈሴን፣ የሚሰጠኝ ደስታ።

ይወረራል ሰውነቴ፣ ባንዳች በማይገለፅ ስሜት፣
ተደምሮ፣ ተደማምሮ ነው መሰለኝ፣ ትዝታየ የልጅነት፣
ዲያቢሎሱ፣ የደብረብርሀን ስላሴ፣
የውርጌቻው አማኑኤል ቁርባን፣ ያራዳው ጊዮርጊስ ቅዳሴ፣
ይወረራል ሰውነቴ፣ ይወረራል መንፈሴ፣

ያባቶቼ የተጠራቀመ እውቀት፣
የተመኙልኝ መልካም ነገር፣ የተናዘዙልኝ በረከት፤
ይሰማኛል መኖሩ፣ ካለበት ፅላቱ፣
ይሰማኛል መኖሩ፣ ከቤተ ክርስቲያን፣ ከመቅደሱ።

ይመስለኛል የተቀመጠ፣ በባህል ብራና ተፅፎ፣
የወርቅ ሙዳይ ተከድኖበት፣ በእምነት ቁልፍ ተቆልፎ።
ይመስለኛል የተቀመጠ፣ እንዳወጣው ለችግሬ፣
እንዲኮሩበት ወገኖቼ፣ መጥፊያቸው እንዲሆን ጠላቶቼ።

ይመስለኛል የተቀመጠ፣ በረከታቸው ያባቶቼ፣
ምርቃታቸው የናቶቼ፣ ቱፍታቸው ያአያቶቼ፤
ተጠቅሎ በጊዜ፣
በዛፍ ጥላ፣ በእጣን ሽታ፣ በቅዳሴ፣ በዝማሬ፤

ይመስለኛል የተቀመጠ።

ዛሬ ግን ቅዳሴ አልነበረም፤ የጊዮርጊስ በራፎችም ተዘግተዋል፣ ተቆልፈዋል። «ምን ነካን!» አልኩ በልቤ፣ «ስምንተኛው ሺ የሚሉት ይሄ ይሆን እንዴ?» በተለይ ያሁኑ ዘመን፣ ያ ሁሉ ጨዋነታችን የጠፋበት፣ ቤተ ክርስቲያን እየዘረፉ ለፈረንጅ የሚሸጥ መንግስት የሰለጠነበት፣ ጳጳሱ ከአምላኩ ይልቅ ለሆዱ ያደረበት፣ ስምንተኛው ሺ እንጅ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?

ከጊዮርጊስ አካባቢ የአሮጌ መፃህፍት መደበሮች አሉ ሲሉኝ ሰምቼ ነበርና ወደዚያ አመራሁ፤ አንዱ ትዝታየ ቢጠፋ ሌላውን አገኘው ይሆናል ብየ፤ «አፈር ያነሳ ስጋ»፣ «መልካም ቤተሰቦች» ፣ «ዩልዬስ ቄሳር» ፣ «ዝክረ ነገር»፣ «የከርሞ ሰው»፣ «ጃፓን እንደምን እንደሰለጠነች»፣ «ልጅነት» . . ይህም አልተሳካም፡፡ ቸርቸር ጎዳናን ተከትየ ቁልቁል ማዝገም ጀመርኩ፡፡ ቸርቸር ጎዳናን እንዴት እንዳለፍኩት ትዝ አይለኝም፣ ብቻ ራሴን ዛሬ «ብሄራዊ ቴአትር» እያሉ ከሚጠሩት አዳራሽ ፊት አገኘሁት፡፡ ያጋጣሚ ነገር፣ «ስምንተኛው ሺ» የሚባል ቴአትር ይታያል፡፡ ስንት ከፍየ እንደገባሁ እንጃ፣ ከተመልካቹ መሀል ተቀምጬ ቴአትሩን ማየቴ ግን ትዝ ይለኛል፡፡ ስለቴአትሩ ያለኝ ትውስታ (Memory) የተቆራረጠ ነው፤ በዚያም ላይ ሳልጨርስ ትቼው ስለወጣሁ አፈፃፀሙን ልነግራችሁ አልችልም፡፡ ግን የማስታውሰው ይሄውላችሁ፡፡

ትእይንት ፩

ቦታው ኢዩቤሊዩ ቤተመንግስት ውስጥ ነው፡፡ መድረኩ፣ በአፄ ሀይለ ስላሴ ጊዜ አሽከሮች የሚውሉበት፣ ከቤተ መንግስቱ ምድር ቤት በሚገኝ አንድ ሰፊ ክፍል ተመስልዋል፡፡ የድሮው መቀመጫዎችና ጠረቤዛዎች ሌላ ክፍል ታጉረው ይሁን ወይም ወደ መቀሌና አስመራ ተጭነው እንጃ ከፍራሽና ከምንጣፍ በቀር ሌላ ነገር አይታይበትም፡፡ ክፍሉ የአሽከሮች መዋያ መሆኑ ቀርትዋል፡፡ ባሁኑ ጊዜ የሚያገለግለው ለከፍተኛ የኢትዮጵያና የጎረቤት ሀገር ባለስልጣኖች የጫት መቃምያ ሆኖ ነው፡፡ ዛሬ አፈወርቅ ለሳምንታዊ ጉብኝቱ ይመጣል ተብሎ ስለሚጠበቅ ክፍሌ ወዳጆ ታዞ ምርጥ ጫት ገዝቶ አዘጋጅትዋል፡፡ ክፍሌ ወዳጆ ፍራሹን ያስተካክላል፣ የሲጋራ መተርከሻውን ይጠራርጋል፡፡

ክፍሌ፡ በተከርኩበት፣ ሰው በነበርኩበት ሀገር፣
አባቴ በተዋጋላት፣ አያቴ በወደቀላት ምድር፣
ተበላሁ እበላ ብየ!
አዬ... የኔ ነገር!
ሆኜ ቀረሁ ቤት ጠራጊ፣

የምድረ ባንዳ ተላላኪ።።

ደሞ . . . . . ፣
እኔ ብሎ ተሳዳቢ...
ምንኛ መታደል ነው፣
መዋረድ መሰደብ፣
ከዚያም የባሰ ነገር አለ ለካ፣
ስድብ መምሰል፣ ስድብ መሆን።።

እኔን ለመስደብ፣ ለማንቁዋሸሽ፣
አያስፈልግም የመጥፎ ቃሎች ጋጋታ፣
ስሜን መጥራቱ ይበቃል፣
ስሜ በቁሙ ስድብ ነውና።።

ከኔ አልፌ ተርፌ፣
ጀግናውን አባቴን አሰደብኩት፣
የቤቴን ስም አበላሸሁ፣
አቆሸሽኩት አሳደፍኩት።።

ፕሬዜዳንት ነጋሶ ይገባሉ።።

ነጋሶ ፡ እባክህ እንዳታስጨርሰን ይህን ቤት በደንብ አፅዳ፣
ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንግዳ አለባቸው፣
ከፍተኛ የጫት በርጫ።።

ክፍሌ፡ እሽ ጌታየ፣
ነጋሶ ፡ ጌታየን እንኩዋን ተወኝ፣
እንዳንተው እኔም አሽከር ነኝ፣
የተገዛሁ ለሆዴ፣
ለከርሴ ለቀፌቴ።።

መለስ ዜናዊ ጠመንጃ ያነገቱ ወያኔዎች ከፊትና ከሁዋላው ከበውት ከመድረኩ ብቅ ይላል፣ ዳዊት ዮሀንስ የመለስን ቦርሳና ካፖርት ተሸክሞ ተከትሎ ይገባል።።

መለስ፡ ምነው ቤቱ ቀዝቅዝዋል፣ ሻይም አላፈላችሁ እንዴ፣
ነጋሶ ፡ ራሴ አፈላለሁ አሁን፣ ራሴ አፈላለሁ ጌታየ፡፡

መለስ፡ አልጋ ሲሉህ፣ መሬት ሆኖ ይቅር!
ያንተ ነገር፡፡
ፕሬዜዳንት እኮ ነህ ለስሙ፣
ትንሽ ኮራ በል እንጅ፣
ይታይብህ ሞገሱ፣ ክብሩ፡፡
ሌላ ሰው ያፍላ ሻይ፣
አንተ ተቀመጥ አርፈህ፣
እኛንም አብረህ ደምረህ፣
አታዋርደን ተዋርደህ፡፡

አለና፣ የኢትዮጵያ ፕሬዜዳንት ሻይ ካላፈላሁ እያለ መሽቆጥቆጡ ገርሞት ነው መሰለኝ፣ ከት ብሎ መሳቅ ጀመረ፡፡ የተከተሉት ወያኔዎችም እንዲሁ መሳቅ ጀመሩ፡፡ ዳዊት ዮሀንስ ደግሞ መሳቅ ይፈቀድለት ወይም አይፈቀድለት ባለማወቁ ነው መሰለኝ፣ ትንሽ ፈዘ ከቆየ በሁዋላ እሱም መሳቅ ጀመረ፡፡ ከክፍሉ ውስጥ የማይስቁ ቢኖሩ፣ የሚሳቀው በነሱ መሆኑን የተረዱት ፕሬዜዳንት ነጋሶና አሽከር ክፍሌ ወዳጆ ብቻ ነበሩ፡፡

«ዳዊት!!» ብሎ ጮኸ መለስ፣ ሳቁን በድንገት አቁዋርጠ፡፡ የዳዊትም ሳቅ ከመቅፅበት ጠፋ፡፡ ጌታው በመሳቁ የተቆጣው መስሎት እንደመንቀጥቀጥም ከጀለው፡፡ ፈገግታው ጥሎት ኮ ብልዋል፡፡ ግንባሩን ለማኮማተርና ኮምጨጭ ለማለት ደግሞ፣ ገና የፊቱ ጡንቻዎች በቁጥጥሩ ስር አልዋሉም፡፡ ብቻ ለንቦጩና ጉንጩ ተንጠልጥሎ ሲታይ፣ የማድረቂያው ጊዜ ሳይደርስ ከተበላሸ የልብስ ማጠቢያ መኪና ውስጥ የወጣ ፎጣ ይመስል ነበር፡፡ «ዳዊት!» አለ እንደገና መለስ፣ «እስቲ ሻይ አፍላ፡፡» አመድ መስሎ የነበረው የዳዊት ፊት፣ ደሙ ሲመለስለት ግልፅ ብሎ ይታያል፡፡ ሳይፈቀድለት በመሳቁ የተቆጣው መስሎት እንጅ፣ ሻይ መጣድማ መደበኛ ስራው አይደል እንዴ፡፡

ትእይንት ፪

አፈወርቅ ኢሳኢያስ በጠባቂዎቹ ታጅቦ ይገባል፡፡ ዘበኞቹ ከመለስ

ወያኔዎች ይልቅ ምግቡም አየሩም የተስማማቸው ይመስላሉ። በመለስና ባሽከሮቹ ላይ የበላይነት ስሜት እንደሚያሳዩ ከፊታቸው ይነበባል። የመለስ አሽከሮች እንደ ዳዊት ባይርበተበቱም አንገታቸውን ደፍተዋል።

አፈወርቅ፡ ዋ! የታለ ጫቱ፣
የታለ ሻዩ መጠጡ?

ክፍሌ፡ ሞልትዋል ጌታየ፣ አዘጋጅቻለሁ ምርጥ ጫት፣
የሻዩን ጉዳይ ግን አላውቅም፣ ሀላፊው ነውና ዳዊት።

መለስ፡ መቀናቱ ነው በዳዊት፣ እችም ስራ ሆና!
የመንገድ ዳር ለማኝ እንዳትሆን፣
እደጅ እወረውርህና።
ይልቅስ ፕሬዜዳቱን ጥራቸው፣
ጫቱና ወሬው እንዳያመልጣቸው።

የአንቱታው ጋጋታ ነው መሰለኝ፣ መለስና አፈወርቅ እርስ በራሳቸው ተያዩና፣ ፍራሽ ላይ እየተንከባለሉ መንከትከት ጀመሩ። ዳዊት ለመሳቅ ከጅሎት ነበር ግን ቀደም ሲል የደረሰበትን ግልምጫ አስታውሶ የጣደው እንደገፋፈለበት ሁሉ በችኮላ ክፍሉን ጥሎ ወጣ። ክፍሌም እንዲሁ እንባ እየተናነቀው መድረኩን ለቀቀ።

አፈወርቅ፣ መለስና ወታደሮቻቸው ብቻ ቀሩ፣ ቁዋንቁዋው አማርኛነቱ ቀርቶ ትግርኛ ሆነ። አብዛኛው ተመልካች ትግርኛ ስለማይናገር ተዋንያኑ የሚናገሩት ሊገባው አልቻለም። በዚሁ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ተመልካቹ አዳራሹን እየለቀቀ መውጣት ጀመረ። አንዳንድ ትግርኛ የሚናገሩ ሰወች እንኩዋን፣ የሚያዳምጡት ስላልጣማቸው ነው መሰለኝ ከህዝቡ ጋር ተቀላቅለው አዳራሹን ጥለው ወጡ።

የሚገርመው፣ ትግርኛ የማይችሉ ግን ተቀምጠው የሚስቁና የሚያጨበጭቡ ተመልካቾች መኖራቸው ነው። እኔም፣

ትግርኛ መናገር ስለማልችል፣ ከተመልካቹ ጋር አብሬ ወጣሁ፡፡ ከአዳራሹ ውጭ፣ በወጣው ሰው ፋንታ ለመግባት የሚጋፉ፣ ጆሮአቸውን ቢቆርጧቸው ትግርኛ የማይሰሙ ሰዎች አይቼ፣ ያ «ስምተኛው ሺ» የሚሉት ዘመን በእርግጥ መድረሱ ተሰማኝ፡፡

ከነቃሁ በሁዋላም የማስበው እምብዛም አልተለወጠም፤ ህልሜም፣ እውኔም አንድ ሆነዋልና፡፡ ስለክፍሌ ወዳጆ አንድ ትልቅ ኢትዮጵያዊ ሲናገሩ፣ «እሱን ተውት፣ እሱ ታኝኮ፣ ተመጦ የተተፋ አገዳ ነው፡፡» ያሉትን አስታወስኩና «አሁን ክፍሌ ወዳጆ ራሱ ምን ይሰማው ይሆን?» የሚል ሀሳብ መጣብኝ፡፡ እንዲህ አይነቱን ችግር፣ ላንግስቶን ሂውዝ የተባለ ጥቁር አሜሪካዊ ገጣሚ እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡፡ ለኔ እንደተሰማኝ ማለቴ እንጅ፣ ላንግስቶን ሂውዝማ ግጥሙን ሲፅፍ በአእምሮው ይብላላ የነበረውን ከራሱ በቀር ማን ያውቀዋል፡፡

<u>የመጨረሻው ኩርባ</u>

ኩርባውን ስትል እጥፍ፣
ከራስህ ጋር ስትገናኝ፣
ግጥም ስትል ከፊትህ፣
ይገባህል ያኔ፣
የቀሩህን ኩርባዎች፣
እንደጨረስክ ታጥፈህ፡፡

ወች ደሞነ?

ገ፩ዜው ፲፱፻፴፬ አም ነበር። ገና ጣልያን ኢትዮጵያን ለቆ፣ ህዝቡ ባዲስ ጉልበት ለመስራት፣ ባዲስ ህይወት ለማሸብረቅ፣ ባዲስ ተስፋ ለመደሰት ቆርጦ የተነሳበት ዘመን። የሰው ልጅ ከሌሎች እንሰሳት የሚለየው ህይወቱ በተስፋ የተሞላ እንደሆነ ብቻ ነው። ሀብታምነት፣ ሀብታም ለመሆን ከሚደረገው ጥረት እኩል አያስደስትም። ሀብታም የመሆን ተስፋ ከሌለ ደግሞ፣ ጥረቱ አይደረግም፣ ሰዉም ህይወቱን ከእንሰሳ ህይወት የተለየ አድርጎ አይመለከተውም።

ተስፋ፣ በገሾዎች ጭቆና፣ በእድሜ መግፋትና በጤና ማጣት ይወሰናል። ኢትዮጵያ መቼም በጨቋኞች ያልተገዛችበት ጊዜ አልነበረም ቢባልም፣ መጨቆን ማለት ያለተስፋ መኖር ከሆነ፣ ጣልያን እንደወጣ የነበረው አገዛዝ የጭቆና ነው ሊባል ጨርሶ አይገባውም።

በዚህ የተስፋ ዘመን አቶ ተፈራ የሚባሉ ሰው ነበሩ። አቶ ተፈራ ተስፋቸውን የሚቃረን የእድሜም ሆነ የጤና ችግር አልነበረባቸውም። ኢትዮጵያዊ ሁሉ የተስፋ አየር በሚተነፍስበት በዚያ ዘመን ጤናማ የ ፷፬ አመት ጎልማሳ መሆን እጥፍ፣ ድርብ ተስፋ ነበርና። አቶ ተፈራ በጣልያን ጊዜ ልጅ ነበሩ። ካንድ ከበርቴ ቤት በአሽከርነት ተቀጥረው ሲሰሩ፣ ከበርቴው ታታሪነታቸውን ተመልክቶ ኖሮ መኪና መንዳት እንዲማሩ ፈቀደላቸው። ተማሩና፣ የከበርቴውን መኪና መሾፈር ጀመሩ። ባለቤታቸውን ወይዘሮ ተዋበችን ያገቡዋቸውም ያኔ የዚያ ከበርቴ ሾፌር ሆነው ነበር። ወይዘሮ ተዋበች አንዳንዴ በትዝታ ወደልጅነታቸው ዘመን ሲመለሱ፣ «ተፈራ ጎፈሬውን አበጥሮ ያችን ባሊላ ይዞ ብቅ ባይል አያገኝኝም ነበር...» ይላሉ። እውነትም ባልና

ሚስቶቹ በልጅነታቸው የዘመኑን የፀጉርና የልብስ ቄንጥ ይከተሉ እንደነበር፣ አሁን ከሳሎናቸው የተሰቀለው በጣልያን ጊዜ የተነሱት ፎቶ ያሳያል። የጎፈሬአቸው አሰራርና የኩታቸው አለባበስ ሰአሊ የሰራው እንጅ ፎቶግራፍ አይመስልም ነበር። እንዳሁኑ ፎቶግራፎች ጥቁርና ነጭ ሳይሆን ቀለሙ ወደ ቡናነት ይወስደዋል። ከመሀከላቸው በላዩ ላይ አበባ የተቀመጠበት ነጭ ምሶሶ ቆምዋል። አቶ ተፈራና ወይዘሮ ተዋበችም አንድ አንዳንድ እጃቸውን ከአበባው ስር በማስቀመጥ ምሶሶውን ተደግፈውታል። ይህ አይነቱ አነሳስ የጣልያን ጊዜ ፎቶግራፎች ላይ በብዛት ስለሚታይ የዘመኑ ቄንጥ ይመስላል።

ጣልያን ከወጣ በሁዋላ አቶ ተፈራ ለአንድ ኩባንያ በሾፌርነት ተቀጠሩ። ደሞዛቸው ፹ብር ነበር። ዘመኑ ደግ ነበርና፣ ያች ፹ብር ከቤት ኪራይ፣ ከምግብና ከልብስ ተርፋ፣ ወይዘሮ ተዋበች የሷብር እቁብ መጣል ጀመሩ። ተስፋቸው፣ ምኞታቸው፣ የከተማ ቦታ ተመርተው፣ ትንሽ ቤት ለመቀለስ ነበር። ምኞታቸው ምኞት ሆኖ አልቀረም፤ ከጥቂት አመታት በሁዋላ ትንሽ ቆርቆሮ ቤት ለመስራት የሚያስችላቸው ገንዘብ አጠራቀሙ።

ጊዜው ፲፱፻፵፰ አም ሆነ። አቶ ተፈራና ባለቤታቸው ፭፻ ካሬ ሜትር ቦታ ከአቶ በለጠ ላይ ተመሩ። አቶ በለጠ የዮሀንስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ለህዝብ የመሩ የኦሮሞ ባላባት ነበሩ። በዚያ ዘመን አባታቸው ያቆየላቸውን መሬት እየሸነሸኑ ለሰርቶ አደሩ በጭሰኝነት የሚመሩ ሰዎች በአዲስ አበባ ሞልተው ነበር። አሁን የተያዘው ፈሊጥ እንደሚተርከው፣ እነዚያ ባለመሬቶች ነፍጠኞችና አማሮች ብቻም አልነበሩም። ያቶ ተፈራም ጎሮቤቶች ጉራጌዎች፣ ኦሮሞዎች፣ አማሮች፣ ወላሞዎች፣ ትግሬዎች ነበሩ። ስራቸውም ያንዱ ሸማኔነት፣ የሌላው ሾፌርነት፣ ያንዱ ውትርድና፣ የሌላው ደግሞ ህክምና ነበር። የሚመሳሰሉበት

ነገር ቢኖር ሁሉም ለፍተው አዳሪዎች መሆናቸው ነበር፤ ካቶ በለጠ በስተቀር ማለት ነው። ከመንደር ውጥስ ሳይሰሩ የሚኖሩ እሳቸው ብቻ ነበሩና።

በሁለት አመት ውስጥ ሰፈሩ አደገ፣ እቁቡም እድሩም ጠነከረ። አባሎቹም ካባ ኮራን ሰፈርና ከገነሜ ጫካ ድረስ ይመጡ ጀመር። የኢትዮጵያ ህዝብ የዴሞክራሲን ስርአት አልለመደም እየተባለ በገዥዎችና በቅኝ ገዥዎች የሚነፋው ቱልቱላ፣ ምን ያህል ስህተት እንደነበረ ለማወቅ፣ የነአቶ ተፈራን እድር መመልከቱ ብቻ ይበቃል። አቶ በለጠ ሀብታም ናቸው ተብሎ ከአቶ ተፈራ የበለጠ ድምፅ አልነበራቸውም። የእድሩ ዳኛ የሚመረጠው በህዝብ፣ የሚሻረውም በህዝብ ነበር። የሰፈሩን መንገድ በድንጋይ ማልበስ፣ ድልድይ መስራት፣ ሰፈሩን የሚያውኩ ሰዎች ካሉ መምከር፣ የተቸገረ መርዳት፣ የተጣላ ማስታረቅ የእድሩ ሀላፊነት ነበር። የተፃፈ መመሪያ፣ የሚጠቅሱት አንቀፅ አልነበረም። ብቻ፣ አበሻ ገዥዎች ካላደፈረሱበት በስተቀር፣ ዴሞክራሲ በደሙ ውስጥ የጠለለ የተፈጥሮ ባህሪው ነው ማለት ይቻላል።

ወይዘሮ ተዋበች፣ እቁብ እየጣሉ ባጠራቀሙት ገንዘብ አራት የሚከራዩ ክፍሎች ሰሩ። የአቶ ተፈራ ደሞዝም ፪፬ብር ደረሰ። ከቤት ኪራይ በሚገኘው ገንዘብ፣ ወይዘሮ ተዋበች ሶስትና አራት እቁቦች መጣል ጀመሩ። እቁብ ሲደርሳቸው፣ ወይንም ከደረሰው ሲገዙ፣ አዲስ የሚከራይ ክፍል መቀጠል የወይዘሮ ተዋበች መደበኛ ስራቸው ሆነ። ይሄ ሁሉ ልፋታቸው፣ መጠሪያቸውን ለማዘጋጀት፣ ልጆቻቸው እንደ አቶ በለጠ ብኩን ካልሆኑ በቀር፣ ህይወታቸውን የሚገነቡበት መሰረት ለመጣል እንጅ፣ ምግብ ጠፍቶ ተርበው፣ ልብስ ጠፍቶ ታርዘው አያውቁም።

አቶ በለጠ የገንዘብ ምንጫቸው መሬት መምራት ብቻ ነበር። የሚመሩት መሬት እያለቀባቸው መጣ። ስለዚህ

አንድም ሆነ ሁለት ሺ ብር ስጡኝና መሬቱን በእርስትነት ጠቅልሉት ማለት ጀመሩ። አቶ ተፈራና ባለቤታቸውም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ከጭሰኝነት ወደ ባለመሬትንት ተሸጋገሩ።

ወይዘሮ ተዋበች እንኩዋንስ ባለመሬት ጭሰኛም ሆነው፣ ቤታቸውን ማሳመር የሚወዱ፣ ቤታቸውን በንፅህና የሚጠብቁ ሴት ነበሩ። ሁሌ በሰም የሚወለወለው እጣውላ ፊት ያሳያል። ከበራፉ አጠገብ የበርኖስ ቁርጥራጮች ስለሚቀመጡ፣ የቤቱ ሰው በነዚያ እየተንሸራተተ ያልፋል እንጅ፣ ማ ወንድ በእግሩ ወለሉን ይረግጣል። የቤታቸው ሳሎን ግድግዳው፣ ከአቶ ተፈራ መስሪያ ቤት በሚመጣ የቀን መቁጠሪያ፣ የመጠጥና የሽቶ ማስታወቂያ ስእሎች የተሸፈነ ነበር። የዘመድ ፎቶግራፎችም አልፎ አልፎ ተሰቅለዋል። ባልና ሚስቶቹ፣ ከፎተግራፎቹ ወይም ከግድግዳው ባለጥበብ ወረቀት ይልቅ እነዚያ ማስታወቂያወች የበለጠ ውብ ሆነው ይታይዋቸው ነበር። ምናልባት፣ ተስፋቸውን ላምዋላላቸው መስሪያ ቤት ታማኝነታቸውን መግለፃቸው ይሆናል።

አሁን ከጠረቤዛው ላይ ዳንቴል የለበሰች ድቡልቡል መቁጠሪያ ያላት አረንጉዋዴ ራዲዮን ተቀምጣለች። መስሪያ ቤታቸው ራዲዮንም ስለሚሸጥ በየወሩ ከደሞዛቸው እየተቆረጠ እንዲከፈል ተስማምተው ነበር አንድ ቀን አቶ ተፈራ ራዲዮንዋን ይዘው ከተፍ ያሉት። ራዲዮንዋ ሳትገዛ በፊት አቶ ተፈራ ከስራ ሲመለሱ ጋቢያቸውን ይለብሱ፣ በረጅም ብርጭቆ ኩል የመሰለ ፊልተር ጠላቸውን ይይዙና፣ ትልቁን ልጃቸውን፣ «እስቲ ያለቃ ገብረሀናን መፅሀፍ አንብብ።» ይሉታል። ብዙ ጊዜ የተነበባቸው መፅሀፍ ነበር፤ ግን ሁሌም እንደ አዲስ ያስቃቸዋል። ያች አረንጉዋዴ ራዲዮን ከመጣች በሁዋላ ግን ቤተ ሰቡ ከአለማየሁ ሞገስ እና ከተክለፃዲቅ መኩሪያ ጋር ተቀያየመ። ሌላው አቶ ተፈራ መስማት የሚወዱት ያፄ ቴወድሮስን ታሪክ ነበር።

ወይዘሮ ተዋበች አሁንም እቁብ መጠጣታቸውን አላቆሙም። እቁቡ ሲደርሳቸው እጣውላ ለሌለው ቤት እጣውላ ማስገባት፣ ኮርኒስ ለሌለው ደግሞ ኮርኒስ ማሰራት እንጅ፣ አዲስ ቤት ለመጨመር ትርፍ መሬት አልነበራቸውም። ሆኖም በህይወታቸው ሊያደርጉ የፈለጉትን ሁሉ ስላምዋሉ፣ አዲስ መሬት ለመግዛት አልሞከሩም። ካልዋቸው ቤቶች የሚያገኙት ኪራይ፣ ላሁኑም ኑሮአቸው ሆነ ለጡረታ ዘመናቸው ይበቃል። «ከእንግዴህ፣ አቡየን እና ተክልየን፣ የምድሩን እንዳሰመሩልኝ ሁሉ የሰማዩንም እንዲያሳምሩልኝ መለመን እንጅ፣ ሌላ ምንም ነገር አልፈልግም።» ይሉ ነበር ወይዘሮ ተዋበች፤ አንዳድ ሰዎች፣ ይንን መሬት ግዥ፣ ያንን ቤት ወለድ አግድ ያዥ እያሉ ሲያማክርዋቸው።

አቶ ተፈራ ሁሌም ደስተኛ ነበሩ። እርሳቸውም እንደሚስታቸው ሁሉ በጣም ንፁህ ሰው ናቸው። በጥንቃቄ የተተኮሰ ሳሪያን ቅድ ልብሳቸውን ለብሰው፣ የተወለወለ ጫማቸውን አጥልቀው፣ ሀዘን ካልሆነ በቀር፣ ቀላ ያለ ከረባታቸውን አስረው ነበር ወደስራ የሚሄዱት። የመስሪያ ቤት መኪና ከቤት ማሳደር ስለማይፈቀድ፣ አቶ ተፈራ ጥዋት ወደ መስሪያ ቤት የሚሄዱት፣ ከስራም የሚመለሱት በእግራቸው ነበር። ከቤታቸው በታች፣ ጥዋትና ማታ የሚሻገርዋት አንድ ወንዝ ነበረች። የሚገርመው አቶ ተፈራ በክረምት እንኩዋን ጫማቸው ጭቃ ሳይነካው ወንዝዋን ተሻግረው ቤት ይገቡ ነበር። ያውም፣ አቶ ተፈራ ማታ ከስራ ሲወጡ፣ እማሆይ ጠጅ ቤት ጎራ ሳይሉ ቤት የገቡበት ቀን በጣት ይቆጠራል። ብዙውን ጊዜ ከአንድ ወይም ከሁለት ብርሌ በላይ አይነኩም። አንዳዴ ግን ሞቅ ብልዋቸው ከቤት ይገባሉ። አቶ ተፈራ ደግና ትሁት ሰው ነበሩና፣ ሚስታቸው በቁጣ ሲናገርዋቸው እንኩዋን እንዳልሰማ ያሳልፍዋቸው ነበር።

ሞቅ ብልዋቸው የገቡ ለት፣ «በየመንደሩ እየጠጣህ

ስትወላገድ፣ ሰው ምን ይለኛል ብለህ አታፍርም!» ይላሉ ወይዘሮ ተዋበች።

«ዝም በይ እባክሽ፤ አንች ምንም አታውቂም።» ይላሉ አቶ ተፈራ፤ ትልቁ ቁጣቸው መሆኑ ነው። ሞቅ ባይላቸውማ አንድም ቃል ካፋቸው አይወጣም።

□

አቶ በለጠ መሬታቸውን ሸጠው ጨረሱና፣ ችግር ላይ ወደቁ። ጤናቸውም ተበላሸ፣ በመጨረሻም ከቤት ዋሉ። ለአንድ አመት ያህል ያልጋ ቁራኛ ከሆኑ በሁዋላ የመስቀል እለት አረፉ። አቶ በለጠ ለራሳቸው ብኩን ይሁኑ እንጅ፣ ለሌሎች ደግ ሰው ነበሩና አገር ንቅስ ብሎ ወጥቶ አልቅሶ ቀበራቸው።

አቶ በለጠ ሁለት ልጆች ነበርዋቸው፤ ከበደና ታደሰ የሚባሉ። ታደሰ ፈረንጅ አገር ተምሮ ተመልሶ በቀዳማዊ ሀይለስላሴ ዩኒቨርሲቴ ታሪክ ያስተምራል። ከበደ ደግሞ የሆለታ ጦር ትምህርት ቤት ምሩቅ ነበር። ሁለቱ ወንድምማማቾች ሲገናኙ ብዙውን ጊዜ የሚያወሩት፣ አባታቸው መሬታቸውን ባይሸጡ ኖሮ፣ አሁን ሜትር ካሬው ፴ እና ፱ብር በሚሸጥበት ዘመን ባለብዙ ሚሊዮን ብር ጌታ ሊሆኑ እንደሚችሉ ነበር። የሰፈሩንም ሰው ለፍቶ ሰርቶ መሬታቸውን እንደገዛ ሳይሆን፣ በግፍ የነጠቃቸው የጠላት ጦር አድርገው መመልከት ጀመሩ።

ታደሰና ከበደ ባባታቸው እምነት የተነሳ፣ የተማሩት ስዊዲሽ ሚሽን ከዚያም ኩየራ እየተባለ የሚጠራው የሚሲዎኖች ትምህርት ቤት ነበር። ሚሲዎኖቹ፣ «ኢትዮጵያን ወደሁዋላ የሚጎትታት የኦርቶዶክስ ሀይማኖት፣ ኦሮሞዎችን ወደሁዋላ የሚያስቀራቸው ደግሞ፣ ከደቡብ አፍሪቃ ነጮች የማይለየው የአማሮች ጭቆና፣ የአማርኛ ቁዋንቁዋ እና

የአማርኛ ፅሁፍ ነው፡፡» እያሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሲሰብኩ ኖረዋል፡፡ አበበና ታደሰም ይህ ሰበካ ሳያውቁት ከልባቸው ገብቶ ተዳፈነ፡፡ የልብ ውስጥ እሳት ነውና፣ ሌሎችን ብቻ ሳይሆን ራሳቸውንም ያከስላቸዋል፡፡

ትምህርት፣ ሰውን ከበታችነት ስሜት የሚያላቅቀው፣ ጥላቻን የሚያጠፋ፣ ፍቅርንና መተባበርን በፋንታው የሚተካ፣ እውነትን በሀሰት፣ ሀቀኝነትን ደግሞ በሌብነት ላይ የሚያነግስ መሳሪያ ነበር፡፡ አሁንም ነው፡፡ ችግሩ፣ ጥንት ይደረግ እንደነበረው፣ አዲስ መጤ ሀሳቦች በባህል ወንፊት ሳይጣሩ፣ ከነዝቃጫቸው ትምህርት ተብለው መሰየማቸው ላይ ነበር፡፡

□

አቶ በለጠ ከሞቱ አመታት አለፉ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥሩ በዛ፣ መሬቱ ተራቆተ፣ አፈሩም ተበላ፡፡ ኢትዮጵያ የራስዋን ህዝብ ሳትመግብ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት የምትጨነቅበትን መንገድ ፈረንጆች አዘጋጁላት፡፡ ባላባቱ መሬቱን በመኪና ማረስ ጀመረ፤ ባላባቱ ራሱ ሳይሆን፣ የኮሌጅ መግቢያ ፈተናውን የወደቀው ልጁ፡፡ ሰርተው ለመኖር ማሰባቸው ክፉ አልነበረም፡፡ ችግሩ፣ መሬቱ በጭሰኛ ስለተከፋፈለና በመኪና ለማረስ ስለማያመች፣ ባለመሬቱ ጭሰኛውን መንቀል ጀመረ፡፡ ኢትዮጵያ ወደውጭ የምትልካቸው እንደ ቡና ያሉ ዋጋቢስ ምርቶች ረከሱ፡፡ የምታስመጣቸው እንደቤንዚን ያሉ ምርቶች ደግሞ ተወደዱ፡፡ ስለዚህ ከተሜውም እንደ ገበሬው ሁሉ ተጨነቀ፡፡ ኢትዮጵያ፣ በኤሌትሪክ ሀይል የታደለች አገር ሆና፣ በከተማም ሆነ በባላገር በኤሌትሪክ ሀይል የሚንቀሳቀስ አንድም ባቡር አልነበራትም፤ በፋንታው የማታመርተውን የፈረንጅ ቤንዚን የሚልፉ በሺ የሚቆጠሩ አውቶቢሶችና ካሚዎኖች ያገሪትዋን መንገዶች አጣበቡ፡፡

፲፱፻፷፩ አም ነበር። የኢትዮጵያ ህዝብ ከውጭ የሚመጣውን ዝቃጭ የማጣራት ፍላጎቱ አገረሸበት። የውጩን ነገር በድንጉት ጠላ። ቡና ቤቱ ክራራቸውን ይዘው «ጉብልየ» በሚሉ አዝማሪዎች ተሞላ። ጦሩን ሰብቆ ጋሻውን አንግቦ፣ ጫካ አልገባም እንጅ፣ ህዝቡ በልቡ ሸፈተ። ጣሊያን ሲወጣ የተጀመረው የተስፋ ጉዞ አበቃ። ሌላ የተስፋ በር መከፈት ነበረበት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ለዚያ አልታደለም።

የህዝቡ ልብ መንግስቱን እንደተቀየመ የሚከተለው ሁነታ(Incident) ያሳያል። ከናዝሬት ወደአዲስ አበባ የሚጉዋዝ ሊወንችና፣ ደብረ ዘይት ከመድረሱ በፊት ተበላሽቶ ቆምዋል። ተሳፋሪው መኪናው እስኪሰራ ድረስ፣ እግሩን ለማፍታታት ከመንገዱ ዳር ወዲያ ወዲህ ይላል። አፄ ሀይለስላሴ ታጅበው ወደሶደሬ ሲጉዋዙ፣ መኪና አቁመው ከመንገድ የፈሰሰውን ህዝብ መስታወታቸውን ሳያወርዱ ተመልክተው፣ ከዘበኞቹ ላንዱ ብርቱካን ለመንገደኛው እንዲሰጥ አዘው መንገዳቸውን ቀጠሉ። ዘበኛው፣ በዘንቢል ሙሉ ብርቱካን ይዞ፣ የመኪናው መንገድ መሀል ላይ ቆሞ፣ ወደሊዎንችናው አነጣጥሮ መሬት ላይ ዘረገፈው። ቡርቱካኖቹ እየተንከባለሉ ተሳፋሪው ካለበት ደረሱ። ከልጅ እስከሽማግሌ ብርቱካኑን ጎንበስ ብሎ ያነሳ አንድም ሰው አልነበረም። እንዲያውም አንዳንዶቹ እንደክዋስ በእግራቸው ያጎኑት ጀመር። እንደድሮ ቢሆን፣ የንጉስ በረከት እንኩዋንስ ከደረቅ ሜዳ ወድቆ ከቁሻሻም ቢሆን ተነስቶ ታጥቦ ይበላ ነበር። ዛሬ ግን ህዝቡ ተቀይምዋል። የተሰጠው ነፃነት አንሶታል፣ የተስፋው ጭላንጭልም ጨርሶ ጨልሞበታል። ነፍጥ ይዞ ከዱር አልገባም እንጅ፣ ህዝቡስ መሸፈቱን ሸፍትዋል።

□

ይህ በሆነ ባመቱ ያፄ ሀይለስላሴ መንግስት ተናደ።

የተዘጋጀ፣ የተሰናዳ የፖለቲካ ድርጅት አልነበረምና፣ ወታደሮች የህዝቡን ድል ሰረቁት። ከበደ፣ አባቱ የሸጡትን መሬት መልሶ ለመንጠቅ፣ ወይም ቢያንስ ሜትር ካሬው በዘመኑ ዋጋ እንዲከፈለው የማድረግ ምኞት ነበረውና፣ የአዲሱ መንግስት ዋና ባለምዋል ሆነ። ታደሰም፣ ትምህርቱ የሰጠ ስለነበር አዲስ «የጭቁኖች ታሪክ» የሚል መፅሀፍ አሳተመ። የጭቁን ህዝብ ነፃ ሲሆን የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ በግብር ለማሳየት፣ ዶክተር ታደሰ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ላይ የኢትዮጵያን ታሪክ በሚመለከት ጉዳይ ፈላጭ ቆራጭ ሆነ። ድሮ የሚያውቁት፣ ቴሌቪዥን ላይ አይተው፣ «እንዴ! ይሄ ታደሰ በለጠ አይደለም እንዴ!» ይሉ እንደሆን እንጅ፣ የፓስቴ ጉዋደኞቸው፣ የስዊዲሽ ሚሽኑ ታዴ መሆኑን ከስሙም ካስተሳሰቡም መለየት አይችሉም ነበር። ታደሰም ሆነ ከበደ አሁን የሚጠሩት፣ ታደሰ በ/ዋቅጅራ እና ከበደ በ/ዋቅጅራ ተብለው ነው። በስማቸው መሀል የተቸነከረችው «በ» ምን እንደሆነች እነሱም አላወሩ ደፍሮ የጠየቀም አልነበረ።

የሚከተሉት አመታት ለኢትዮጵያ ህዝብ የፍዳው ዘመን ሆኑ። ንብረቱ ተበዘበዘ፣ ልጆቹ ተረሸኑ፣ እንኩዋንስ የሰው የእንሰሳም ኑሮ ተነፈገው። ታደሰ እና ከበደም የብዙ ሰው ቤት አጠፉ። ሰው ገለዋልም ይባላል። ወንጌል ጨብጠ ሲገሉ አይቻለሁ ብሎ የሚመሰክር ግን አልተገኘም። እነ ታደሰ ያባታቸውን መሬት ዳግም ለመሸጥ ያቀዱት ሳይሳካ ቀረ። በዚያ የተነሳ የሰፈሩን ሰው አመሱት። ጉቦ የሰጣቸውን ይቀበላሉ፣ ያልሰጠውን ደግሞ ያስራሉ፣ ይገርፋሉ። አቶ ተፈራ ጉቦ አልሰጥም በማለታቸው በስተርጅና ለሁለት ቀን ታስረው ነበር። የሰፈሩ ሰው ኡኡ ብሎ ከበላይ ባለስልጣን ትእዛዝ መጥቶ ነበር የተለቀቁት። ከዚያን ወዲህ ጉቦ የጠየቃቸው ወይንም ያሰራቸው አልነበረም። ግን፣ ለዚህ ቀን ይሆኑኛል ብለው ያሰሩዋቸውን ቤቶች መንግስት ወርስዋቸዋል። የሚኖሩት በጡረታ ደሞዛቸውና ቀበሌ በቆረጠላቸው የቤት ኪራይ አበል ነበር።

ምንም ህይወታቸው እንዳሰቡት መጨረሻው ባያምርም፣ ባልና ሚስቱ አሁንም የሰው እጅ አላዩም።

ሻለቃ ከበደ በ/ዋቅጅራ ያባቱ ቤት ውስጥ ስለሚኖር፣ ንብረቱ ያው ያባቱ ቤት ብቻ ነበር። ዶክተር ታደሰ ግን ከመፅሀፍ ሽያጭ፣ ከደሞዙ እንዲሁም ከሌላ ምስጢራዊ ምንጭ በሚያገኘው ገንዘብ፣ ከቦሌ ትልቅ ዘመናዊ ቤት አሰርትዋል። ከበደ፣ ወንድሙን ቢወደውም በዚህ መቅናቱ አልቀረም። ታደሰም ከበደ እንደሚቀናበት አውቅዋል። ከወንድሙ ጋር ከሚጣላ ያለውን ቢያካፍለው ይወድ ነበር። ግን፣ ገንዘቡን የሚሰጠው ድርጅት፣ «አትቸኩል፤ አንድ ቀን እንዳንተው ሁሉ የሚያስፈልገውን ገንዘብ እንሰጠዋለን።» እያለ ያስታግሰው ነበር። ዶክተር ታደሰ ለምን ያ ሁሉ ገንዘብ እንደሚፈስለት ሊገባው አልቻለም። ድርጅቱ የሚጠይቀው የጭቁን ህዝቦችን ታሪክ በተከታታይ እንዲፅፍ ብቻ ነበር። አብዛኛውን ታሪክ ማስረጃ አስደግፎ ነበር የመጀመሪያውን መፅሀፍ የፃፈው። አሁን ግን ማስረጃውም እያለቀ ስለመጣ፣ ዶክተር ታደሰ ልበ ወለድ ታሪክ መፃፍ ከጀመረ ቆይትዋል።

በመጨረሻም ሻለቃ ከበደ የኮለኔልነት ማእረግ ተሰጠውና ወደ ሰሜን ግንባር የጦር አዛዥ ሆኖ ተሾመ። የዶክተር ታደሰ ምስጢራዊ ጌቶችም የሀያ ሺ ዶላር እጅ መንሻ ላኩ። ከበደ ከስግብግብነቱ የተነሳ ገንዘቡ ከየት እንደመጣ እንኩዋን አልጠየቀም፣ የዮሀንሱን ቤት ሸጠና ከቦሌ አዲስ ቪላ ገዛ። ፎቴው፣ ቪዲዮው፣ ቴሌቪዢኑ፣ ምኑ ቅጡ!!። ልጆቹን እንደ ታደሰ ልጆች ሁሉ እንግሊዝ ትምህርት ቤት አስገባ። ከታደሰ ጋር ለመስተካከል የቀረው ነገር ቢኖር አንድ ቮልቮ ብቻ ነበር።

ከበደ ወደ ሰሜን ዘመተ። ልጆቹና ሚስቱ ደግሞ ከዚህ በፊት ባልተለመደ ድሎት መኖር ጀመሩ። ሆኖም፣ የከበደ ደሞዝ ወጫቸውን መሸፈን አልቻለም። ስለዚህ ያ

ሚስጥራዊ ድርጅት በየወሩ የአንድ ሺ ዶላር ደሞዝ ቆረጠላቸው። ታደሰና ከበደም ስራቸው ይህን ያህል ገንዘብ እንደማያወጣ ገባቸው። ነፍሳቸውንም ለሰይጣን መሸጣቸውን ተረዱት።

ኮለኔል ከበደ፣ አዲስ አበባ በመጣ ቁጥር በሚስጥር ከአንድ ፈረንጅ ጋር ይገናኛል። የኢትዮጵያን ሰራዊት የጦር እቅድ፣ አቅምና ድክመት ለፈረንጁ በዝርዝር ያስረዳል። አልፎ አልፎ ፈረንጁ፣ አንዳንድ ሽምቅ ተዋጊዎች ያሉበትን ቦታና ሀይላቸውን ለኮለኔል ከበደ ይነግረውና በተወሰነ ሰአት እንዲወራቸው ይጠይቀዋል። እነዚያ ሞት ለምን እንደተፈረደባቸው የማያውቀውን ተዋጊዎች ኮለኔል ከበደ ከቦ እንዳልነበሩ ያደርጋቸዋል። እንዲህ በሚያገኛቸው አንዳንድ ድሎች ምክንያት ከበደ ከሊቀመንበሩ የጄነራልነት ማእረግ ተሰጠው። የሚያዳምጣቸው ሚስጥሮች፣ የሚገኝባቸውም ከፍተኛ ስብሰባዎች በዙ። በዶክተር ታደሰ በኩል የሚሰጠው ክፍያም እንዲሁ ጨመረ። ፈረንጁ በጄነራል ከበደ አስተዋዋቂነት ከከፍተኛ ባለስልጣኖች ጋር ተዋወቀ፣ መተዋወቅ ብቻ አይደለም ሎሌነት አሳደራቸው። የከበደና የታደሰ ጠቃሚነትም እዚሁ ላይ አበቃ።

አንድ ቀን፣ ጄነራል ከበደና ዶክተር ታደሰ ከፈረንጁ ጋር በድብቅ ተገናኝተው ሲያወሩ፤ ፈረንጁ፣ «ደርግ የሚወድቅበት ጊዜ ደርሰዋል። አሁን ጄነራል ከቻሉ ከወታደርና ከመሳሪያዎ ጋር ከድተው ከወያኔ ጋር ቢቀላቀሉ፣ ድሉን ማፋጠን ይችላሉ፣ የድሉም ተካፋይ ይሆናሉ። ዶክተር ታደሰም የወያኔን የመጨረሻ እንቅስቃሴ፣ የወንድምዎን ድል፣ ሌሎችንም ታሪካዊ ድርጊቶች የአይን ምስክር በመሆን ይመዘግባሉ። ይህም በመጭው መንግስት ተደማጭነትን ያስገኝልዎታል።» አላቸው።

«የተጨቆነውን የኦሮሞ ህዝብ ከአማራ ቀንበር ለማላቀቅ

የማናደርገው ነገር የለም!!» ብሎ ጀነራል ከበደ ጠረቤዛውን በጁ መታ። ዶክተር ታደሰም፣ የአማራ ጭቆና ያንገፈገፈው መሆኑን ለፈረንጁ ለማሳየት ጉንጮቹን አርገፈገፋቸው።

□

ደርግ፣ ድል ሆነ። ኢትዮጵያም የህዝብዋን ነፃነት ከገፈፈ መንግስት፣ ኑረታዋን ወደሚፃረረው ተሸጋገረች። እጆችዋን ለዘመናት የዘረጋችለት አምላክ ገና በቃሽ አላላትም። ዶክተር ታደሰ የወያኔ ህገ መንግስት አርቃቂ ሆኖ ተመረጠ። ጀነራል ከበደን ግን የሾመውም የሸለመውም አልነበረም። ከፈረንጁ የሚያገኘው ገንዘብ ስለተቁዋረጠ የቦሌ ቤቱን ለአቶ አብርሀ ክፍለእግዚ አከራይቶ እርሱ ካጥር ጥግ ከተሰሩት መደዳ ያሸከር ቤቶች ውስጥ መኖር ጀመረ። አቶ አብርሀ፣ «የተከራየሁት ግቢውን በሙሉ ስለሆነ፣ ለቀህ ውጣልኝ።» ባይ ነበር። በመጨረሻም ጀነራል ታደሰ የውጣልኝ ጭቅጭቅ ስለበዛበት፣ ቤተሰቡን ጠቅልሎ ከወንድሙ ከዶክተር ታደሰ ቤት ገባ። እንኩዋንስ የኦሮሞን ህዝብ ነፃነት የግል መብቱንም ማስከበር ተሳነው።

መቼም በሰው ልብ የእውነት ርዝርራሹ አይጠፋምና፣ ደክተር ታደሰ በህገመንግስቱ ስብሰባ ላይ፣ «የብሄረ ሰቦች የራስን እድል በራስ መወሰን፣ እስከ መገንጠል ድረስ» የሚለው አስተሳሰብ ሁዋላ ቀርና ፈረንጅ የጥቁርን ህዝብ ለመገነጣጠልና ለማዳከም የሚነዛው መርዝ ነው ብሎ በመከራከሩ፣ ከአባልነት እንዲገለል ተደረገ። የዩኒቨርሲቲ መምህርነት ስራውን ከሜዳ መልስ ጀምሮ ስለነበር፣ የድሮው የቅምጥል ኑሮ ቢቀርም በልቶ ያድራል። ሆኖም ነፍሱን ለሰይጣን የሸጠ ገሀነም መግባቱ አይቀርምና፣ የታደሰና የከበደ ስቃይ ገና መጀመሩ ነበር።

ወያኔ ተደላደለ፤ መንግስትነትም ተሰማው። አቶ አብርሀ የጀነራሉን ቤት ሊገዛ ፈልጎ ቢጠይቅ፣ ጀነራል ከበደ አሻፈረኝ አልሸጥም አለ።

«ተው! አንተንም ወንድምህንም ነው ያለቤት የማስቀራችሁ። ይልቅስ ብትሸጥልኝ ይሻልሀል።» አለ፤ አቶ አብርሀ።

ጀነራሉም፣ «ምን ሲደረግ! ነፍሱን ይማረውና፣ ያባቴን ቤት ሼጩ የገዛሁትን ቤት! ነፍሴ ቆማ አይደረግም!» አለ፤ መቼም ወኔ ጨርሶ አይሞትምና። ቤቱን የገዛው ግን ያባቱን ቤት ብቻ ሳይሆን አገሩን ጭምር ሸጠ መሆኑን ረስቶታል።

አቶ አብርሀ ብዙ የመንግስት ባለስልጣኖች ያውቅ ስለነበረ፣ ጀነራል ታደሰና ዶክተር ከበደ በቀይ ሽብር ጊዜ ሰው አስገድለዋል የሚል ክስ እንዲቀርብባቸው ተደረገና ቤታቸውን መንግስት ወርሶት እስር ቤት ገቡ። የወንድምማማቾቹንም ቤቶች መንግስት በርካሽ ለአቶ አብርሀ ሸጣቸው። ያቶ በለጠ ዋቅጅራ የአያት የቅድም አያት መሬት ጉዳይ እዚህ ላይ አከተተ።

□

አቶ ተፈራም፣ ወይዘሮ ተዋበችም አሁን እድሜያቸው ወደ ሰማንያው ተጠግትዋል። አቶ ተፈራ እርጅና ቢጫናቸውም፣ ከዘራቸውን ይዘው ካቦርታቸውን ደርበው፣ ቤተ ክርስቲያን ተሳልመው መመለስ ይችላሉ፤ ያውም ጫማቸውን ጭቃ ሳይነካው። ወይዘሮ ተዋበችማ የዝቁዋላን ተራራ ወጥተው፣ አቡየን ተሳልመው ይመለሳሉ። ይሄን ሳምንት ዜጋመል ሄደዋል። ዛሬ አቶ ተፈራ ከቤተ ክርስቲያን መልስ የእድር ስብሰባ አለባቸው። እድሩ የሚሰበሰበው በደርግ ጊዜ በተሰራው የኩዋስ ሜዳ ላይ የተጣለ ትልቅ ድንኩዋን ውስጥ ነበር። አቶ ተፈራ ከድንኩዋኑ ሲደርሱ ባዶ ነበርና ብቻቸውን ከአንድ አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀመጡ። ወዲያውኑ ጎረቤታቸው፣ መርፌ ወጊው፣ አቶ ተርፋ ከድንኩዋኑ ገቡ። አቶ ተፈራን እንደምን አደርክም አላልዋቸውም። ብቻ አጠገባቸው

መጥተው ተቀመጡ፡፡ አቶ ተርፋ ከጋቢያቸው ስር አንድ ጠርሙስና ሁለት ብርጭቆዎች ይዘዋል፡፡

«ተፈ!» አሉ አቶ ተርፋ፣ «የእማሆይን ቤት ረሳሀት መሰለኝ፡፡» አቶ ተርፋ የጉዋደኛቸውን ጠጅ መውደድ ስለሚያቁ፣ ከቤት ጠጅ ካለ ከሚስታቸው ሰርቀውም ቢሆን አንድ ጠርሙስ ሳይዙላቸው አይመጡም ነበር፡፡ አቶ ተርፋ ሁለቱን ብርጭቆዎች ሞሉና አንዱን ለአቶ ተፈራ ሰጥዋቸው፡፡

«ተፈ!» አሉ፣ አቶ ተርፋ እንደገና፣ «እማሆይ ቤት የለመድከው ስኩዋር እንዳይመስልህ፤ ይሄ ንፁህ ማር ነው፡፡»

አቶ ተፈራም፣ ብርጭቆዋን ግማሽ ያደርሱና፣ «ኧከከከከ!! ግደለው ተበለህ ተልከሀል እንዴ!» ይላሉ፤ የጠጁን ሀይለኛነት ሲገልፁ፤ ወደውታል ማለት ነው፡፡ አቶ ተፈራ እድር ስብሰባ የሚሄዱት ሀሳብ ለማቅረብ ወይም ጉዳይ ለመፈፀም አልነበረም፡፡ ብዙውን ጊዜ ከእድር ስብሰባ ምን እንደተወራ እንኩዋን አያስታውሱትም፡፡ በህይወት የተረፉ ወዳጆቻቸውን ማየት ቀልዳቸው መስማት ግን ይናፍቃቸዋል፡፡ በተለይ፣ አቶ ተርፋንና ቢጋቢ ደብቀው የሚያመጥዋትን ጠጅ በተስፋ ነበር የሚጠብቅዋቸው፡፡

አቶ ተፈራ በዚህ እድሜያቸው ብዙም የሚመኙት አልነበራቸውም፡፡ ብቻ ተስፋ በሌለበት በዚህ ዘመን የተፈጠሩ ወጣት ልጆች ሲያዩ ልባቸው በሀዘን ይነካል፡፡ «መች ይሆን እማምላክ የምትታረቅሽ?» ይላሉ፣ አገራቸውን ኢትዮጵያን፤ «መች ይሆን?»

የእስራኤል ቅምጣኔ

የአረብና የእስራኤል ጦርነት፣ የስድስቱ ቀን ማለት፣
የተደረገ ጊዜ ድሮ፣ ያበሻ ክርስቲያን ተጨንቆ፣
የተወረረ ይመስል አገሩ፣ የተደፈረ ድምበሩ፣
ሲማለድ ቆይቶ፣ የእስራኤልን አምላክ ነቅቶ፣
ጦርነቱ ሲያበቃ፣ የአረብ ጦር ሲፈታ፣ የይሁዳው ድል ሲመታ፣
ፈነደቀ አበሻ፣ ፈነደቀ ክርስቲያኑ፣ ኢትዮጵያ።

የእስራኤሉ የወታደር ተጠሪ፣ ነበርና ያዲስ አበባ ነዋሪ፣
ድሉን ለማክበር ደገሰ፣ ውስኪ ተረጨ፣ ሻምፓኝ ፈሰሰ።
ሲናገር እስራኤሉ በደስታ፣ አንቆት እንባ፣ ይዞት ሲቃ፣

«አገሬ እስራኤል ብቻ ትመስለኝ ነበር፣ የሚኖሩባት ወገኖቼ፣
«ለካስ ኢትዮጵያም አገሬ ናት፣» አለ «ነበርና ተሳስቼ።»

አበሻ አድናቆቱን ገለጠ፣ ምስጋናውን አጎረፈ፣
ጭብጨባውን አቀለጠ።
አሁን ነው የሚገባኝ ሚስጥሩ፣ ኢትዮጵያም አገሬ ናት የማለቱ፣
ለካስ ፍቅር አልነበረም የወጣው ከአንደበቱ፣
የጠላትነቱ መርዝ እንጅ፣ የጥፋታችን መሰረቱ።

አይ ኢትዮጵያ! የሚቀርብዋትን አረቦች ከድታ፣
የሚቀርባትን ሀይማኖት ረስታ፣ እስልምናን ጠልታ፣
እስራኤልን ፈጠረች፣ የመጥፊያዋን ዘር ተከለች።
ሀያል ናቸው ጠላቶችዋ፣ ተላሎች ደግሞ ልጆችዋ፣
እንዴት ይሆን የምትድን፣ ከዚህ አዘቅት፣ ከዚህ ገደል፣
እንዴት ይሆን የምትድን!
እንዴት ይሆን የምትድን?

፩

ክይጣን ጥቁር ነው ይሉናል፣ መልአክ ደግሞ ነጭ፤ ይህ ግን የዲያብሎስ ልጆች ራሳቸውን ለማሳመር የሚያወሩትና የሚያስወሩት እንጅ፣ እውነቱስ ሌላ ነበር። መቼም የተማራችሁ ሰዎች ስለሆናችሁ የሚከተለውን ስነፍጥረታዊና ታሪካዊ ሀቅ ታውቁታላችሁ። ተረቱ የተምዋላ እንዲሆን ግን እንድደግመው ፍቀዱልኝ።

የሰው ዘር ሁሉ ከአንድ ሄዋን እንደመነጨ የጅን ምሁራን አረጋግጠዋል፤ «ከአንድ አባት ከአዳም ነው የመጡት።» ብሎ አፉን ሞልቶ የተከራከረ አዋቂ ግን አልተገኘም። ሄዋን ከአዳም ብቻ ሳይሆን ከሌላም ፍጡር ልጆች ወልዳ ነበር። መፅሀፍ ቅዱስ አድበስብሶት አለፈ እንጅ፣ ሄዋን ከሰይጣን እፀ-በለስን ብቻ ሳይሆን ልጆችም አግኝታ ነበር። እግዚአብሄርም የተቆጣው፣ እፀበለስን በመብላትዋ ብቻ አልነበረም ከሰይጣን በመውለድዋም እንጅ። «እግዚአብሄርም ሰይጣንን ረገመው፣» ይላል፣ ከቅዱሳን መፃህፍት ሁሉ ቅዱስ የሆነ፣ ከደቀእስጢፋን ተደብቆ የተገኘ አንድ ጥንታዊ መፅሀፍ፤ «ቆዳህ ይንጣ፣ ፀጉርህ እንደ አራዊት ሁሉ ይለስልስ፣ ዘሮችህም የክፋትና የተንኮል ሁሉ ምንጭ ይሁኑ።» አዳምና ሄዋንን፣ ቆዳቸውን ጥቁር፣ ፀጉራቸውን ከርዳዳ ተፈጥሮአቸውን የዋህ አድርጎ ነበር የሰራቸው፤ አለም በተንኮለኞች የተሞላችው፣ የልጆችዋም ቆዳ የተዘበራረቀው የሰይጣንና የአዳም ልጆች በመዳቀላቸው ነበር።

ገነት ዛሬ የአፋር ሸለቆ ብለን የምንጠራው ሀገር ነበር። ዲያቢሎስ፣ ተረግሞ ከገነት ወጥቶ ወደሰሜን ሸሸ። ልጆቹን ይዞ ፭፻ አመታት ሲንከራተት ከኖረ በሁዋላ ዛሬ አውሮፓ ተብሎ የሚጠራው ምድር ደረሰ። ከዚያም ቤቱን ሰርቶ መኖር ጀመረ።

የሰይጣን መንታ ልጆች ወንድና ሴት ነበሩና፣ በመንገድ ብዙ ልጆች ወለዱ። ልጆቹም ልጅ እየወለዱ በየደረሱበት ቤትና ንብረት እያበጁ፣ ዛሬ ፈረንጆች የሚኖሩበትን ሀገር ሞሉት። ጊዜው እየረዘመ መሬት እየጠበበች ስትሄድ፣ የአዳምና የሰይጣን ልጆች አብረው መኖር ጀመሩ። አብሮ መኖር መጋባትና መዋለድን አስከተለ። እንዲያም ሆኖ አዳምንም ሰይጣንንም የማይመስሉ ሰወች ተፈጠሩ።

ያ ከቅዱሶች ሁሉ ቅዱስ የሆነ መፅሀፍ እንዲህ ይላል። «ፍጡር ከ ስምንት አንድ እጅ ያዳም ወይም የሄዋን ዘር ካለበት ሰው ነው።» ይህንን ጉዳይ ሰይጣን አስቀድሞ ተገንዝቧል። ስለዚህ ከመጀመሪያ ልጁ ከዚያም ከልጅ ልጆቹ በመውለድ የሰይጣን ዘር እንዳይጠፋ መጠበቁ አልተሳነውም። ሰይጣን እንደአዳም ሞት ስላልተበየነበት፣ ዘለአለም ይኖራልና ንፁህ የሰይጣን ዘር ማምረቱ ችግር አይሆንበትም። እነዚህ ንፁህ የሰይጣን ልጆች ቁጥራቸው አይብዛ እንጅ፣ አሁንም ከመህከላችን አሉ። ንፁህ ሰይጣኖች ሁሉ የከፉ ያዳም ልጆች ሁሉ ደግሞ የተባረኩ ናቸው ማለት አይደለም። ነፍሳቸውን ለሰይጣን የሸጡ ንፁህ ያአዳም ልጆች ብዛታቸው ስፍር ቁጥር የለውም፤ መንኩሰው እግዚአብሄርን ያገለገሉ ንፁህ ሰይጣኖች እንደነበሩም ታሪክ ይመሰክራል።

ከነዚህ ሰይጣኖች አንድዋ፣ ናዝሬት ከበላምበራስ ውነቱ ቡና ቤት ከፍ ብላ፣ ከዋናው መንገድ አጠገብ ትኖር ነበር። ስምዋ ሜራት በለጠ ይባላል። ሜራት ያለባት የአዳም ዘር ትንሽ ቢሆንም፣ የናዝሬት ፀሀይ ስለሚጠብሳት ይሆናል፣ ከፈረንጅነቱ ወደ አበሻነቱ ታደላለች። ቆዳዋ ሽክላማ ነው። ፀጉርዋ ጥቁር ሀር ይመስላል። ውበትዋ፣ እንኩዋንስ ያዳምን ዘር አባትዋን ዲያብሎስን ማርኮታል። የሜራት አባት አውሮፓ የሚኖረው ዋናው ዲያቢሎስ ነበር። ዲያብሎስ ኢትዮጵያ ሲመጣ በጅሮንድ በለጠ ተብሎ ነበር የሚጠራው።

የሜራት እናትም በልጅነትዋ ከፈረንጆች አገር ሸሽታ ነበር የመጣችው። የሜራት አያት (የእናትዋ አባት ማለቴ ነው። በጅሮንድማ፣ ተፈጠሩ እንጅ መች ተወለዱ!) በአውሮፓ፣ እሱም፣ ከሱም በፊት አባቱ፣ ከዚያም አስቀድሞ አያቱ፣ የታወቁ ወርቅ ሰራተኞች ነበሩ። ዲያብሎስም ከአዳም ልጆች ለሚመለምላቸው አሽከሮቹ የሚያድለውን የጣት ቀለበት የሚያሰራው ከዚያ ነበር። የሜራት አያት ምን እንደነካው አይታወቅም፣ ዲያብሎስን አላገለግልም፣ የሰይጣን ቀለበትም አልሰራም፣ አሻፈረኝ አለ። ስለዚህ ዲያብሎስ የሞት ፍርድ ፈረደበት። ዲያብሎስ ሞት የፈረደበት ሰይጣን የሚገደለው ከልጆቹ ጭምር ስለሆነ የሜራት አያት ያስር አመት ሴት ልጁን ወደኢትዮጵያ አሸሸ። እግዚአብሄር ለዲያብሎስ አልታዘዝም ብለው የተሰውትን ሰይጣኖች ከሲኦል መንጥቆ ስለሚያወጣቸው፣ የሜራት አያት አሁን የት እንዳለ መገመቱ አያስቸግርም።

አንድ ኢትዮጵያዊ የወርቅ ነጋዴ ነበር የሜራትን እናት ደብቆ አምጥቶ ያሳደጋት። በመጨረሻው ግን፣ ከዲያብሎስ ተደብቆ መኖር አይቻልምና ተያዘችና ከበጅሮንድ በለጠ ፊት ቀረበች። በጅሮንድ የሜራትን እናት ሲያዩ ልባቸው ወከክ አለ። በዚያም ላይ ያለባት የአዳም ዘር ከስምንት አንድ እጅ ብቻ በመሆኑ፣ ንፁህ የሰይጣን ዘር እንትፈለፍል ማድረጉ የተሻለ መስሎ ታያቸውና የሜራት እናት ለጊዜው ከሞት ተረፈች።

፪

የሜራት ጎረቤት በናዝሬት አሉ ከሚባሉት ሀብታሞች አንዱ ነበር። ስሙ ከድር መሀመድ ይባላል። ከድር ከናዝሬት ሱቆችና የዘይት ፋብሪካ ነበረው። ንፁህ የሰይጣን ልጆች እንደማይገኙ ሁሉ፣ ንፁህ ያዳም ልጆችም ማግኘት ያስቸግራል። ከድርና ቤተ ሰቡ ግን ንፁህ የአዳም ልጆች ነበሩ። ንፅህናው ባጋጣሚ ሳይሆን፣ እግዚአብሄር በሰይጣን እንዳይበከሉ ከሚጠብቃቸው ቤተሰብ አንዱ በመሆኑ ነበር።

ከድር የአዳም ልጅ በመሆኑ፣ ደግና የዋህ ሰው ነበር። ሜራት፣ በኢትዮጵያ የዲያብሎስ እንደራሴ ሆና ስትሾም፣ ብዙ ሰይጣኖች ቀንተውባት ያላደረሱባት ችግር አልነበረም። ሜራት ሰይጣን ስለነበረች ብዙውን ተንኮል መቁዋቁዋም ችላ ነበር። እናትዋ ግን ሰው ነበረችና ያልያዛት በሽታ ያልደረሰባት አደጋ አልነበረም። መጀመሪያ ቤንዚን-ቤትዋን አቃጠሉባት፣ ከዚያም ሶደሬ ያልተበረዘ ፍልውሀ ለቀው ግማሽ ሰውነትውን አቃጠልዋት። በመጨረሻም የማይድን የሳንባ ነቀርሳ ያዛት። ቤንዚን-ቤትዋ የተቃጠለ ጊዜ፣ ከድር ገንዘብ አበድርዋት ነበር እንደገና የተቁዋቁዋመችው። የተቃጠለች ጊዜም የከድር ሚስቶች እንደልጅ ሆነው ነበር ያስታመምዋት። ነቀርሳ ሲይዛትም እንዲሁ አስታመው፤ ስትሞት ደግሞ አልቅሰው ነበር የቀበርዋት። ውለታ ከፋይ ያርጋት እንጅ፣ ሜራትስ ያለባት እዳ ብዙ ነበር።

ሜራት ሰይጣን በመሆንዋ የምትከተለው ሀይማኖት የላትም። ገንዘብ አምላክዋ፣ ገንዘብ የሚያስገኝ ዘዴ ሁሉ ሀይማኖትዋ ነበር። እናትዋ ግን የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታይ ነበረችና፣ ሜራት ሳትወድ በግድ አርባዋን ማውጣት ነበረባት። አርባውን ባወጣች ማግስት፣ ላስቸኩዋይ ስብሰባ ተጠራች። ስብሰባውን የጠራው ዲያብሎስ ሲሆን፣ የተጠሩት ደግሞ የምእራቡ፣ የመካከለኛው ምስራቅና፣ የኢትዮጵያዋ እንደራሴዎች ነበሩ። ከሜራት በቀር ሌሎቹ የስብሰባውን ምክንያት ያውቁ ነበር። ስብሰባው እንዲደረግ አባታቸውን ይወተውቱ የነበሩት እነሱው ነበሩና። ሜራት ግን ለምን እንደተጠራች በተለይም ወንድሞችዋ ለምን የስብሰባው ተካፋይ እንደሆኑ አልገባትም።
ስብሰባው ሲጀመር፣ ዲያብሎስ ከሰፊው ጠረቤዛ በጠባቡ ጠርዝ በኩል፣ ዙፋን የመሰለ ወንበር ላይ ተቀምጦ ነበር። ዙሪያውን ደግሞ፣ ሜራትና ሁለቱ ወንድሞችዋ መጠናቸው ከአባታቻው ይንስ እንጅ እነሱም ዙፋን የመሰሉ ወንበሮች ላይ ተቀምጠዋል። በሁለተኛው ረድፍ፣ ተከታይ

ሰይጣኖችና ነፍሳቸውን ለሰይጣን የሸጡ የአዳም ልጆች ነበሩ።።

ዲያብሎስ «ልጆቼ!» አለ፤ «ዛሬ የጠራሁዋችሁ፣ ንፁህ የአዳም ዘሮች ቁጥራቸው እየጨመረ ስለሄደ ማድረግ ያለብንን እንድንመካከር ነው።። በተለይም ከኢትዮጵያ ከድር መሀመድ የሚባል የአዳም ልጅ፣ ዘሩ እየበዛ ሀብቱ እየካበተ በመሆኑ አንድ ነገር መደረግ ይኖርበታል።።»

ሜራት ደነገጠች።። ከድርን ባትጠቅመውም ልትጎዳው አልፈለችም ነበርና።።

«አባባ! ከድር ጥሩ ጎረቤቴ ነው።። ለችግሬ ብዙ ጊዜ ደርሶልኛል ለምንድነው የምንጎዳው?» አለች።። ይህ ለከድር መልካም ነገር ስታስብ የመጀመሪያዋም፣ የመጨረሻዋም ነበር።።

ዲያብሎስ አይኑ ደም ለበሰ።። ወንድሞችዋ ያባታቸውን መቆጣት ተመልክተው ወደ ተራ ጋኔንነት ይለውጣታል ብለው አስበው፣ ደስ ብልዋቸው ነበር።። ዲያብሎስ ግን ሜራት የሚወዳት ልጁ ነበረችና እንዲያ አላደረገም።።
«ሁለተኛ የርህራሄ ጠባይ አይብሽና ተራ ሰይጣን አደርግሻለሁ።። ይህ የለመድሽው ሁሉ ምቾትና ቅንጦት ይቀራል።።» አላት።።

ተራ ሰይጣን መሆን ለሜራት ኑሮ መጥፎ አልነበረም።። ከናትዋ የወረሰችው ቤንዚን-ቤት ስለነበረ ደህና ኑሮ መኖር ትችል ነበር።። ግን ተራ ሰይጣን ከመሆን ከድርን ማጥፋቱ የቀለለ መስሎ ታያት።። ድሮስ ከሰይጣን ወዳጅ ምን ይጠበቃል?

ከስብሰባው የተገኙ ሁለት ነፍሳቸውን ለሰይጣን የሸጡ ኢትዮጵያውያንም ነበሩ።። ያገሩ ሰው በመሆናቸው፣

መልካቸው የህዝቡን መልክ በመምሰሉ እና አባቶቻቸው ዲያብሎስን በታማኝነት ያገለገሉ የቤት ውልድ ባሮች በመሆናቸው ከድርን ለማጥፋት በሚደረገው ዘመቻ የሜራት ረዳቶች እንዲሆኑ ተወሰነ፡፡ እንደዚህ ነበር በሰይጣኖች ጉባኤ ከድርን ከአምላኩና ከልጆቹ ጋር ለማቀያየም ሴራው የተጠነሰሰው፡፡

፫

የምእራቡ ሰይጣን የዘይት ኢንዱስትሪ አዋቂ ነው ተባለና ወደ ናዝሬት ተላከ፡፡ ናዝሬት እንደደረሰም የናዝሬቱ የዘይት ፋብሪካ የሚሻሻልበትን መንገድ እንዲያጠና፣ ሜራት ከድርን እሽ አሰኝችለት፡፡ የከድር ፋብሪካ ከግሪክ አገር የተገዛ አሮጌ እቃ ነበር፡፡ ለስሙ ነው እንጅ አብዛኛው እቃ እየተሰበረ፣ በአይነቱ ጣና ገራዥ እየተሰራ፣ አየተለወጠ፣ ፋብሪካው ከግሪክ አገር የመጣው መሆኑ ከቀረ ቆይትዋል፡፡ ግን ይሰራል፡፡ ሲሰበርም ባገር ልጆች ይጠገናል፡፡ ከውጭ የሚመጣ መለዋወጫ ብዙም ስለሌለ፣ ከድር ፋብሪካውን ለማካሄድ የፈረንጅ ብር አያስፈልገውም ነበር፡፡

አንድ ቀን ሜራትና የምእራቡ አማካሪ፣ ከድርን አውሮፓ ሄዶ ዘመናዊ ፋብሪካዎችን ጎብኝቶ እንዲመለስ ጋበዙት፡፡ ከድርም እግረ መንገዱን መካ ለመድረስ ስላሰበ፣ አላንገራገረም፡፡ መጀመሪያ ጣልያን አገር ያሉትን ፋብሪካዎች አስጎበኙት፡፡ ከድር እንኩዋን፣ «የግሪክ እቃ ጥሩ ነው፡፡ ግሪክን ነው ማየት የምፈልገው፡፡» ብሎ ነበር፡፡ ግን ሜራት፣ «እነሱ ሁዋላ ቀር ናቸው፡፡ ጀርመን፣ እንግሊዝና፣ ጣልያን ነው ዘመናዊ ፋብሪካ ያለው፡፡» አለችውና ነገሩ በዚሁ ቆመ፡፡ እውነትም እንዳለችው ፋብሪካዎቹ ዘመናዊ ነበሩ፡፡ አንድ ትንሽ ነገር በመጫን ብቻ፣ ኑጉ ተጨምቆ፣ ጠርሙሱ ተሞልቶ፣ ቆርኬው ታሽጎ፣ በካርቶን በካርቶን እየሆነ የሰው እጅ ሳይነካው ይደረደራል፡፡ «ድንቅ!» አለ ከድር፣ «ይህ የሰይጣን እንጅ የሰው ስራ አይመስልም፡፡»

በየዋህነት ምን ያህል እውነት እንደተናገረ የሚያውቁት ሜራትና ወንድምዋ የኮረኮርዋቸውን ያህል ሳቁ።

ከድር እንደ ኢትዮጵያ ሰፊ፣ እንደ ኢትዮጵያ ለምለም፣ እንደ ኢትዮጵያ ሀብታም የሆነ አገር ያለ አይመስለውም ነበር። አሁን ግን የጣልያንን ፈብሪካዎች፣ የእንግሊዝን ለምለም ሜዳዎች፣ የጀርመንን ጫካዎችና አውራ ጎዳናዎች አሳይተው፣ እምነቱንና ኩራቱን አናጉበት። ያችን የዘይት ፈብሪካውንም ሲያስባት ታስቀው ጀመር።

እንግሊዝ አገር ሲደርሱ፣ ከዲያብሎስ ቤት ራት ተጋበዙ። የዲያብሎስ ቤት፣ ቤተ-መንግስት ነበር የሚመስለው። የክፍሉን ማማርና ንፅህና፣ የአልጋውንና የመቀመጫውን ምቾት፣ የምግቡን አይነትና ብዛት፣ የከድር አይኖች ማመን አቃታቸው። ራት ከተበላ በሁዋላ፣ ዲያብሎስ የትኛውን ፋብሪካ ለመግዛት እንደወሰነ ጠየቀው።

ከድርም ፣ «የጣልያኑ ይረክሳል፤ ግን እሱም ቢሆን ካቅሜ በላይ ነው።» አለ።

«አይ ከድር!» አለ ዲያብሎስ፣ «የማያሳስብ ነገር ነው የሚያሳስብህ። እኔ እንዲህ አጥሬ ብታየኝ ዋዛ ሰው እንዳልመስልህ። እንዳንተ ታታሪ ለሆኑ ሰዎች ገንዘብ የሚያበድር በአለም ሁሉ የታወቀ ትልቅ ባንክ አለኝ። ስለዚህ የገንዘቡን ነገር ለኔ ተውልኝ።»

ከድርም ከመቀመጫው ተነስቶ እጅ ነሳና፣ «አላህ! የጌታየን እድሜ ያርዝምልኝ።» ሲል፣ ዲብሎስና ልጆቹ፣ ከተቀመጡበት በድንጋጤ ደርቀው ቀሩ። ከድርም ያጠፋውን ባለማወቁ፣ እርሱም እንደሰይጣኖቹ ሁሉ ደነገጠ።
ዲያብሎስም ትንፋሹ ሲመለስለት፣ «ተቀመጥ ከድር፣ እባክህ ተቀመጥ ልጄ።» አለው።

ከድርም በልቡ፣ «እንዴት የተባረኩ አዛውንት ናቸው!» ብሎ አመሰገነ።

ፀ

ከድር ከሰይጣን ባንክ በተበደረው ገንዘብ አዲስ ፈብሪካ ገዛና ተከለ። የድሮው ፋብሪካም ተዘጋ። ለጥቂት ጊዜ፣ ድሮ ከሚመረተው አስር እጥፍ ዘይት ይመረት ጀመር፣ በጥራትም ቢሆን የከድርን ዘይት የሚወዳደር ጠፋ። በሁዋላ ግን እቃ በተበላሸ ቁጥር መለዋወጫው ከፈርንጅ አገር መምጣት ነበረበት። ፈረንጆቹ እንደ ጣና ገራዥ የኢትዮጵያን ብር አይቀበሉም ነበርና፣ የራሳቸውን እቃ ለመግዛት ከራሳቸው የፈርንጅ ብር መበደር ነበረበት። በመጨረሻም «ፋብሪካው የተሰራው የፈረንጅ ኑግ እንጅ ያባሻ ኑግ እንዲጨምቅ አልነበረም፣ ለዚህ ነው ቶሎ ቶሎ የሚበላሸው።» አለና ከፈረንጅ አገር ኑግ እያስመጣ እንዲሰራ የምእራቡ ሰይጣን አማከረው።

ከድር መታለሉ ገባው። አሁን ግን ምን ማድረግ ይችላል። እዳውን መክፈል ስላልቻለ ፋብሪካውን ተነጠቀ። ሜራትም ለሁለቱ ባሮችዋ፣ ከፋብሪካው መንቀል የቻሉትን እየነቀሉ ከናዝሬት ውጭ እንዲወስዱት ፈቀደችላቸው። ሜራት የድብብቆሽ ጨዋታ አቆመች። ሁለቱን ባሮችዋን አስከትላ ባደባባይ መዞር ጀመረች። ከዲያብሎስ ገንዘብ ተበድሮ ያልከፈለም ካለ እነዚሁኑ ባሮችዋን እያዘዘች ማስደብደብም የቀን ተቀን ስራዋ ሆነ።

ነፍሳቸውን ለሰይጣን የሸጡ ሰወች ከሌላው የሚለዩት፣ ዲያብሎስ በሸለማቸው ቀለበት ነው። በዚህም ቀለበት አማካይነት የሰይጣንን ሀይል ይካፈላሉ። እንዲህ አይነቱ የሰው ጋኔኖች ከናዝሬት ቁጥራቸው እየበዛ ሄደ። ከድር ብቻ ሳይሆን የናዝሬት ህዝብ በሙሉ ተጨነቀ። ከድር «ሜራት ሰይጣን ትሆን?» የሚል ጥርጣሬ በልቡ ለመጀመሪያ ጊዜ

አደረበት። ግን፣ «ያን ሁሉ ውለታ የዋለለትን ቤተሰብ ለማጥፋት የሰይጣንም አንጀት ቢሆን አይችልም።» የሚል አስተሳሰብ ስለነበረው፣ በአይኑ የሚያየውን እንኩዋን ማመን አልፈለገም። ግን ችግሩ እየጠናበት ሄደ። ሚስቶቹንና ልጆቹን እንኩዋን መመገብ ተሳነው። ዲያብሎስ የከድር መደህየት ብቻ አላረካውም ነበርና፣ «ከድር ቀለበቴን ካላጠለቀ እውነት እኔ ዲያብሎስ አይደለሁም።» ብሎ ፎከረ።

ሜራት በናዝሬት የናጠጠች ሀብታም ሆነች። አይንዋ ያየውን ልብዋ የወደደውን ሁሉ ትገዛ ጀመር። በአሜሪካ፣ በእግሊዝ፣ በጣልያን እና በእስራኤል ቤት ሰራች፣ ንብረት አበጀች። ኢትዮጵያውያንን እንደወገኖችዋ ቀርቶ እንደ ወዳጆችዋ መመልከት እንኩዋን አቆመች። የእናትዋንና የአያትዋን ስቃይ ስታወራ እንባ ይተናነቃታል፤ እርስዋ በሌሎች ላይ የምታደርሰው ስቃይ ግን አይሰማትም። ገንዘብ ያሸተተችበት ቦታ ሁሉ አገርዋ፣ ገንዘብ የሚያስገኝ ድርጊት ሁሉ እውነትዋ ሆነ። የዋህነት ነው እንጅ፣ ድሮስ ከዲያብሎስ ልጅ ምን ይጠበቃል!

ከድር ያለውን ለሌላ ይሰጥ ነበር እንጅ ከሌላ ለምኖ አያውቅም። ችግሩ እየባሰበት ሲሄድ ግን ከሜራት ገንዘብ ለመበደር ወስኖ አንድ ጥዋት ከቤትዋ ሄደ። ሜራትም ለምን እንደመጣ ስላወቀች ደስ አላት።

«ከድር አለችው» ሜራት። ጋሼ ከድር ነበር የምትለው፤ እንደዛሬ ቀን ሳይጥለው። ከድሮ ማእረጉ መውረዱን አወቀ። «በአለም ላይ ሁለት ሀይሎች ነበሩ፤ የዲያብሎስና የእግዚአብሄር። የዲያብሎስ ሀይል እያደገ የእግዚያብሄር ደግሞ እየደከመ ስለሄደ፤ እግዚአብሄር ራሱ የዲያብሎስ አሽከር የሚሆንበት ጊዜ ሩቅ አይደለም።» ከድር መብረቅ እንደመታው ሁሉ ከተቀመጠበት ደርቆ ቀረ። ለካስ የጠረጠረው እውነት ነበር። ሜራት ቀጠለች፣ «ለማይቀር

ነገር ለምን በችግር ትሰቃያለህ? ይህንን ቀለበት አጥልቅና፣ ሀብትህን በሙሉ ልመልስልህ፡፡» ብላ የዲያብሎስን ቀለበት ከፊቱ አስቀመጠችለት፡፡

የከድር ድንጋጤ ወደ ቁጣ ተለወጠ፡፡ በዚህ መሀል የሜራትን እጅ ተመለከተ፤ ቀለበት የለበትም፡፡ ሜራት ንፁህ ሰይጣን ናት ማለት ነው፡፡ አያቱ ልጅ ሆኖ፣ «ንፁህ ሰይጣኖች የዲያብሎስን ቀለበት ካጠለቁ፣ ነፍሳቸውን ለሰይጣን የሸጡት ደግሞ ቀለበቱን ካወለቁ ከመቅፅበት ይሞታሉ፡፡» ብለው የነገሩት ተረት ትዝ አለው፡፡ ከድርም «ተረት ይሁን እውነት የማወቂያው ጊዜ አሁን ነው፡፡» ብሎ አሰበ፡፡ ሜራት ተዝናንታ እንዳለች ቀለበቱን አንስቶ እጅዋን ይዞ ከጣትዋ ላይ ሰካው፡፡ የመፈራገጫ ጊዜ እንኩዋን አልነበራትም፡፡ እንዳልነበረች ሁሉ ተነነች፡፡

የናዝሬት ህዝብ በሰይጣኖች እንደተወረረ ገባው፡፡ የከተማው ትልቁ ወሬ ከድር የዲያብሎስን ልጅ መግደሉ ነበር፡፡ የናዝሬት ወጣቶች የዲብሎስን ቀለበት ያጠለቁትን ሰዎች እያሳደዱ ቀለበታቸውን እያወለቁ ያተንዋቸው ጀመር፡፡ ግማሾቹም እየሸሹ ናዝሬትን ጥለው ወጡ፡፡ የምእራቡ ሰይጣን፣ ሜራት የሞተች እለት ነበር አውሮፓ ገብቶ ያደረው፡፡

ፏ

የጣና ገራዥ ልጆች አሮጌውን የዘይት ፋብሪካ ጠግነው ስራ አስጀመሩት፡፡ የናዝሬትም ሰው የጣና ገራዥ ሊጠግነው የማይችል ፋብሪካ ሁለተኛ ከናዝሬት አይገባም የሚል ውሳኔ አሳለፈ፡፡ ከወደፊት ጥቃት ለመዳን ግን ይህ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የናዝሬት ህዝብ፣ ዲያብሎስ ኢትዮጵያንና ልጆችዋን ለማንበርከክ፣ ብዙ ጥረት እንዳደረገ ያውቃል፡፡ ጥንት የዲያብሎስ መልኩ ግልፅ ነበርና መከላከሉም ከባድ አልነበረም፡፡ አሁን ግን ዲያብሎስ ተንኮሉን የሚያሰራው በቤት ውልድ ባሮቹና እንደሜራት ያገሩን ሰው መስለው

በሚኖሩ ልጆቹ አማካይነት ነው። የተንኮሉ መሳሪያወች ብዙ ናቸው። አንዱ፣ የናዝሬትን ህዝብ ከሞጆ፣ የሞጆን ህዝብ ደግሞ ከደብረ ዘይት ማነካከስ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የኢትዮጵያን ህዝብ የፈረንጅ ብልጭልጭ ነገር ማስለመድ ነው። ከድር የቀን ፀሎቱን ሲያደርስ፣ ዲያብሎስ ተመልሶ እንደሚመጣ ይታየዋል። «ምን ማድረግ ይሻለናል?» ይላል። ጥያቄው ለራሱ፣ ለወገኖቹ ከዚያም አልፎ ለአምላኩ ነበር።

እናንተስ ምን ይሻለናል ትላላችሁ?
የሚረባ ልዩነት የለ መሀላችን፣ መሀላችሁ፤
ይሻላል ያን ይዘን መፋለጡ፣
ዘለአለማዊ ባርነቱ?
ወይስ እንከተል ምክሩን፣
የወልደ ማርያምን ልጅ፣ የመስፍንን?*

አልፈልግም ካለ የናዝሬት ህዝብ፣
አብሬ አልኖርም ከሞጆ፤
ይምረጥና በሰላም፣
ደስ ይበለው፣ ይውጣ ጎጆ።

ዲያብሎስ ሲያጣ ማጣያ፣
አንዱን ካንዱ ማለያያ፣
ጊዜ ይኖረናል ለማሰብ፣ ለመስራት፣
የራሳችንን ብልጭልጭ ለማምረት።

ያያት ቅድም አያቶቻችን ጀግንነት፣
መሰረቱ፣ የነፃነታቸው፣
ጦር አወራወራቸው፣ ብቻ አልነበረም፣
ጋሻ አመካከታቸው፤
ያላረሱትን አለመብላታቸው እንጅ፣

*ኢትዮጵያ ከየት ወዴት፣ መስፍን ወልደ ማርያም፣ ጉራማይሌ።

ያልፈተሉትን አለመልበሳቸው።

ነፃነት ድንበር መጠበቅ ብቻ አይደለም፣
ውሀ የሚያጥበውንም አፈር እንጅ፣
ነፃነት ወሰን ማስከበር ብቻ አይደለም፣
ፈረንጅ የሚበክለውንም ባህል እንጅ፣
ልጆች በፈረንጅ ቁዋንቁዋ እየተማሩ፣
በስነ-ልቡና ባርነት ሲዋጡ፣
ምን ዋጋ አለው፣ ዘብ መቆሙ፣
አሸዋ፣ ድንጋይ መጠበቁ፤
ምን ዋጋ አለው?

ጌታቸዉ

ወቼ ደስታን ፈለግሁ፣ ለግል ብቻዬ፣
በጅምር ቀረ እንጅ፣ ውጥኑ ምኞቴ፣
እሾህ አሜኬላ፣ አረሙን ነቃቅለን፣
መልካም ፍሬ 'ሚሰጥ፣ በፋንታው ተክተን፣
ለመኖር ነበረ፣ የኔ ፍላጎቴ፣
በጅምር ቀረ እንጅ፣ ውጡኑ ምኞቴ።

የጥላሁን ዘፈን ነው። የጊዜው ወሬ ሲያትት፣ ለመንግስቱ ንዋይ የተፃፈ ሙዚቃ ነው ይላል። የወሬው ጥቀት ግን የልቤን ስእል ሊለውጠው አይችልም። ለመንግስቱ ንዋይ የተፃፈ ነው ብየ ስላመንኩ፣ ዘፈኑን በሰማሁ ቁጥር ትዝ የሚለኝ የታህሳሱ ግርግር ነው።

ባለፈው ሳምንት ይህንኑ ዘፈን ሳዳምጥ አሁንም እንደቀድሞ ሁሉ የታህሳሱ ግርግር ትዝ አለኝ። በሀሳቤ የሚታዩኝ ሰዎች ግን መንግስቱ ወይም ገርማሜ ንዋይ አልነበሩም። መንግስት ግልበጣው ተሳክቶ ቢሆን ኖሮም፣ ኢትዮጵያ አሁን ምን ትመስል እንደነበረም አልታሰበኝም።

የአርበኞች ትምህርት ቤት ነበር የታየኝ። አስተማሪዎቻችን በየበረንዳው ሰብሰብ እያሉ ይንሾካሾካሉ - ምን እንደሚያወሩ ግን እንጃ። ከተማው እርጭ ብልዋል። ከቀኑ አምስት ሰአት ላይ ዳሬክተሩ ሰበሰቡንና ወደቤታችን እንድንሄድ ነገሩን። እኔና ጌታቸው ግን ተያይዘን ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ሄድን - ያኔ ፕሮፓጋንዳ ነበር

የሚባለው፣ መልከጥፉ በስም የማይደገፍበት ጥሩ ዘመን ነበርና።

የማስታወቂያ ሚኒስቴር በራፍ ላይ የክቡር ዘበኛ ወታደሮች ዘብ ቆመዋል። ሰዉ፣ አጥሩን ተደግፎ ይመለከታል። ወታደሮቹም ተመልካቹ ገለል እንዲል አይጠይቁትም ነበር። እንዲያውም ፊታቸው ፈገግታ ስለሚታይበት፣ የሰውን መሰበስበስ የወደዱት አስመስልዋቸዋል።

ጉዳዩ ጨርሶ ሊገባን ስላልቻለ፣ ወደቤታችን ተመለስን። የዮሀንስን ቤተክርስቲያን፣ የኒስትሮዎቹን መቀመጫ ሁሉ አልፈን በጠባብዋ ኮረኮንች መንገድ ቁልቁል ወረድን። ጌታቸው እናቱ ቤት ገባ -- እኔም ወደቤቴ። ቤት ስገባ ራዲዮኑ ያለሰአቱ ተከፍቶ ያወራል። ቤተሰቡ ሁሉ አገጩን ደግፎ፣ ተክዞ ያዳምጣል።

«የጭቆናው ዘመን ተፈፀመ። አለቀ። ደቀቀ።» ይላል ራዲዮኑ። ትንሽ ይቆይና ደግሞ፣ «ከዚህ ቀጥሎ የልኡል አልጋ ወራሽን ንግግር በድጋሚ እናሰማለን ። ። ። » ይላል። አልጋ ወራሽ ይናገራሉ። ሲጨርሱ የወታደር ማርሾች ይዘመራሉ። ከዚያም፣ «አለቀ፣ ደቀቀ፣ የጭቆናው ዘመን ተፈፀመ።» ሁሉም ነገር እንደገና ይደገማል፣ የአልጋ ወራሹም ንግግር፣ የወታደሩም ማርሽ። አሁንም ምን እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም ነበር። ከዚያ በፊት እንደዚያ ያለ ነገር አልሰማሁም ነበርና፣ ከምን ጋር አያይዘዋለሁ፤ ከምንስ ጋር አመሳስለዋለሁ።

ንግግሩ ብዙም አልገባኝም፣ ስለዚህ አላስታውሰውም። የወታደሮቹ ማርሾች ግን ለብዙ ዘመን ባንጎሌ ተቀረፁ። አሁን አንዱን ብቻ ነው የማስታውሰው። ሳዜመው አይኖቼ ይረጥቡብኛል። የአልጋ ወራሹን ንግግር ከሰፈራችን ጀርባው ላይ እባጭ ያለበት ጎቢጥ የምንለው ልጅ በቃሉ ይወርደው ነበር። «እንዴት ቢያጠናው ነው?» እያልኩ

ይገርመኝ ነበር። ሁዋላ ግን፣ ጎቢጥ አንዴ የሰማውን ቃል ሳይስት መድገም እንደሚችል አወቅሁ።

የዚያን ቀን ከሰአት በሁዋላ ተኩስ ተጀመረ። ማ፣ ከማ እንደሚዋጋ፣ ለምን እንደሚዋጉ፣ አላወቅሁም። ትላልቆቹም የቤቱ ሰዎች አልነገሩኝም። ምናልባት እነርሱም እንደኔው አያውቁ ይሆናል። ብቻ ሌሊቱን ሁሉ ሲተኮስ አደረ። ተኩሱ ለስንት ቀን እንደቀጠለ እንጃ፣ ብቻ አንድ ቀን ሰው ከቤት መውጣት ጀመረ። እኔና ጌታቸውም የሆለታ ወታደሮች በሰልፍ ሲያልፉ ለመመልከት ሄድን። ከስዊዲሽ ሚሽን ፊት ለፊት ቆመን ነበር ሰልፉን ያየነው።

ክቡር ዘበኞች ጃነሆይን እንደከዱ፣ ጦር ሰራዊቶች እንዳሸነፉና፣ የጃነሆይ ታማኝነታቸውን እንዳረጋገጡ አውቀናል። የሆለታ ወታደሮች፣ ከሆለታ ድረስ በእግራቸው ይምጡ ወይም በመኪና መጥተው አባዲና ሲደርሱ ወርደው በእግራቸው ይሰለፉ አላውቅም፤ ማወቅ ብፈልግ እንኩዋን እችል ነበር። ሰልፉን የሚመሩት የጌታቸው አባት ነበሩ። ብቻ ያኔ ይህንን ማወቁ አስፈላጊ መስሎ አልታየኝም ነበር። ለነገሩ ነው እንጅ፣ አሁንም አስፈላጊ አይደለም።

የጌታቸው አባት ያኔ ሻለቃ ነበሩ። ሰልፉን እየመሩ ደረታቸውን ነፍተው በኩራት ነበር የሚራመዱት። እኛጋ ሲደርሱ ወደቀኝ ዞር ብለው ተመለከቱን። ኩራታቸውን ወደ ልጃቸው አስተላለፉት መሰለኝ፣ ጌታቸውም ደረቱን ነፍቶ ቆመ።

«እንኩዋን የጦር ሰራዊት ልጅ ሆንኩ።» አለኝ ጌታቸው። «አባቴ ክቡር ዘበኛ ቢሆን ኖሮ፣ አሁን የሰፈሩ ሰው የከሀዲ ልጅ ይለኝ ነበር።»

ጌታቸው ቆዳው ወደ ጥቁርነቱ ያደላል። ሰውነቱ በጣም ትንሽ ነበር። ፀጉሩ ሉጫ ይሁን ከርዳዳ እረስቼዋለሁ። ግን

ባጭሩ ነበር የሚቆረጠው። ሲያወራኝም ሆነ ሲያዳምጠኝ እየሳቀ ስለነበር ጥርሶቹ አሁንም ይታዩኛል።

ከጌታቸው ጋር አብረን አንውልም ነበርና፣ ያደረግናቸው ነገሮች ብዙም አይታወሱኝም። የመስኮብን ኤግዚቢሽን አብረን ማየታችን ግን ትዝ ይለኛል። በየመሳሪያው ላይ የተቀመጡ የመኪናውን አሰራር የሚያስረዱ ፅሁፎችና ሌሎችን በነፃ የሚሰጡ የሶቭየትን ኑሮ የሚያሳዩ ስእላዊ መፅሄቶች ስንሰበስብ ዋልን። እነዚያን መፅሄቶች ሲያነብ አድሮ ይሁን ወይም ታላቅ ወንድሞቹ ነግረውት እንጃ፣ በበነጋው ወደትምህርት ቤት ስንሄድ፣

«አምሀ፣ እኔ እኮ ኮሚኒስት ነኝ።» አለኝ።

«ለምን ኮሚኒስት ሆንክ?» አላልኩትም። እንዴት ሰው ኮሚኒስት እንደሚሆንም አላውቅም ነበር። እውነቱን ለመናገር፣ አሁንም በደንብ የገባኝ አይመስለኝም። ጌታቸው እውነተኛ ኮሚኒስት እንደነበረ ግን አልጠራጠርም። ሰው፣ ላልሆነው ነገር ህይወቱን አሳልፎ አይሰጥምና።

ጌታቸውን ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ሰንዳፋ ነበር፣ ደመቀ ዘውዴ የሞተ ለት። ጌታቸው ማሩ ያኔ በተማሪ ንቅናቄ መሪነቱ መታወቅ ጀምሮዋል። አርበኞችን ከለቀቅን ወዲህ ተያይተን አናውቅም ነበርና፣ ሰላም ለማለት ከሩቁ እጁን ወደላይ አወጣ። አላናገረኝም፣ ግን ፈገግ አለ። አወ፣ እነዚያ የማውቃቸው ጥርሶች ያኔም ነበሩ።

<u>እዳ</u>

እምነታቸው የፀና፣ ምንኛ ናቸው የታደሉ፣
ራሳቸውን የሚሰዉ፣ ያዩትን ሌሎች እንዲያዩ።

ቀድሞ ቢሆን፣ እምነት፣ ከህይወት፣

አለም ውብ ትሆን ነበር፣
የሚኖርባት በእውነት፣
የሚሞትላት ለእውነት።

እውነት የግል ብትሆን እንኩዋ፣ የማትጥም ለሁሉ፣
ምንኛ ናቸው የታደሉ፣ እነዚያ፣
ለእውነታቸው የሚኖሩ፣
ለእውነታቸው የሚሞቱ፤
ምንኛ ናቸው የታደሉ።

ችግሩ ትምክህት አይደለም፣ የራስን እውነት ማስቀደሙ፣
የማያምኑትን መስራት እንጅ፣ የማይሰሩትን ማመኑ።
ያ ነው ያለማችን እዳ፣
ያ ነው ያለማችን ፍዳ።
ያ ነው።

ስም እንግዲኽ!!

ከዚህ ቀሰዬ፣
እዚያጋ ታሰሬ፣
ከእስር ቤት አምልጬ፣
ዘበኛውን ሁሉ በጡጫ በቡጢ፣
አንጥፌ ዘርሬ፣
ጣናን በዙል ሰአት ዋኘቹ አቁዋርጬ፣
ከዚያ ተንደርድሬ አባይን ዘልዬ፣

ኡፍፍፍ !!!
ብተወው ይሻላል፣ ለታሪክ ፀሀፊ፣
ለታምር ለገድሌ።

Wውየው በቅርቡ ነበር፣ ካዲስ አበባ የመጣው። ዋሽንግቶን ያሉ ዘመዶቹን ጠይቆ፣ ቦስቶን የነበሩ ጉዋደኞቹን ጎብኝቶ፣ አሁን ረዘም ላለ ጊዜ ለመዝናናት ነበር ወደሂውስተን የበረረው። ስሙ አበራ ደገፉ ይባላል። አበራ ባዬ ሀይለስላሴም ሆነ በደርግ ዘመን መለስተኛ ባለስልጣን ነበር። ቁመቱ ረጅም ባይሆንም ኩሩ አያሰኘውም። አንገቱ አጭር ስለሆነ ማጅራታም አስመስሎታል እንጅ፣ ውፍረቱ የሚያሳጣ አይደለም። በዚያም ላይ ክረምት በመሆኑ ወፍራም ሹራብ ይለብስ ነበርና፣ ውፍረቱ አእምሮየ የፈጠረው ስእል ሳይሆን አይቀርም።

አበራን መጀመሪያ ያየሁት፣ የፈረንጆች ገና ለት ሰው ቤት ራት ተጋብዤ ነበር። እንደገባን፣ ከረጅሙ ፎቴ ላይ ተቀምጦ እጆቹን አጣምሮ፣ አንገቱን ወደግራ ቀልብሶ ነበር የተቀመጠው። ካገር ቤት አዲስ እንደሚመጡ አበሾች ሁሉ አይን አፋር ይመስላል።

የቤቱ ባለቤት ፣ መቅደስ፣ ከእንግዳ ክፍል በገባች ቁጥር፣ «አበርየ የሚጠጣ ምን ላምጣልህ?» ትለዋለች። ታናሽ እህቱ ናትና ገና ናፍቆትዋ አልወጣላትም።

«አይ መቅዲ» አለ አበራ፤ ግማሽ አይኑን እህቱ ላይ፣ ግማሹን መሬት ላይ ተክሎ። «በሽታየን ስታውቂ ለምን ታስቸግሪኛለሽ! ሆዴን እንዳይነካኝ ወተቱን አብዝተሽ፣ መድሀኒትዋን ከላዩ ጠብ አርገሽ ብትሰጭኝ ምናለ!»

መቅደስ እኛን እያየች፣ «አበራ ሆዱን ያመዋል፤ ለዚህ ነው ውስኪ በወተት የሚጠጣ፤» አለች።

እኔም አበራ ተዝናንቶ ጨዋታ እንዲጀምር አሰብኩና፣ ድሮ እንደሚያውቀው ሰው ሁሉ «አበራ!» አልኩት። «ትንሽ ማር በላዩ ላይ ብትጨምርበትማ እንዴት ነበር የሚጣፍጥ።»

አበራ አየኝና ፈገግ አለ። እጆቹ ከደረቱ ላይ ወረዱና አጥንት እንደሌለባቸው ሁሉ ከፎቴው ላይ እዘፍ አሉ። እግሮቹን ከሰበሰበበት ስለዘረጋቸው ከጠረቤዛው ስር መፍታታት ጀመሩ። እህቱ ማር እንደሚፈልግ ለማወቅ አይን አይኑን ታየው ነበርና፣ ቀና ብሎ፣

«ጥሩ ሀሳብ ነው፤ ሁለት ማንኪያ ጨምሪበት።» አላት።
መቅደስ ወደጉዋዳ ገባች፣ አበራም ወሬውን ቀጠለ። «በውስኪ ለመጠጣት፣ ጥሩው የአፍጋኒስታን ማር ነው!!» አለ፤ «ይሄ የናንተ ማር አይረባም። በደርግ ጊዜ ለስራ ጉዳይ አፍጋኒስታን ሄጄ ነበር ይህንን ሚስጥር ያወቅኩት። አንድ ዋሻ ውስጥ የሚኖር ሼህ ነው፣ የጤና መሰረቱ የአፍጋን ማር ባረቄ መጠጣት መሆኑን የነገረኝ። ከዚያ ወዲህ በሽታ የሚባል ነገር ነክቶኝም አያውቅ።»

ውስኪ በወተት የሚጠጣው ሆዱን ስለሚያመው መሆኑን ከምኔው እረሳው! የአፍጋኒስታን እስላሞች፣ ያውም ሼሁ

መጠጥ እንደማይጠጡ አያውቅ ይሆን? እርስ በራሳችን ተያየንና በልባችን «ስጥ እንግዴህ!!» አልን።

አበራ ያን የወተት፣ የውስኪና የማር ቅልቅል አንድ አራቱን ብርጭቆ አገባደደ። አይን አፋርነቱ ጥሎት ከሄደ ቆይትዋል። አበራ፣ ያልረገጠው አገር፣ የማያውቀው ባለስልጣን፣ ያልተማረበት ዩኒቨርሲቴ፣ ያላገኘው ዲግሪ፣ ያልተቀዳጀው ክብር አልነበረም። ወሬው አንዱ ካንዱ ጋር አይጣጣምም። አበራ ግን ግድ አልነበረውም።

መቅደስ ነገሩ እያሳፈራት ስለመጣ፣«ቡና ላፍላላችሁ?» ብላ ጠየቀች። ቡና ከጠጣ ይበርድለትና መዋሸቱንም ያቆማል ብላ አስባ ነበር። አበራ ግን ሻይ እንጅ ቡና እንደማይጠጣ አወጀ፤ ያውም ያለስኩዋር።

ከመህከላችን አንዱ «አቤ!» አለው፤ አሁን ወዳጅ ስለሆንን ሁላችንም አቤ ማለት ጀምረናል፤ «ሻይ አጠጣጥህ እንደእንግሊዞች ነውና!»

አቤ ፈገግ አለ፤ ብዙ ጊዜ የመለሳት ጥያቄ ሳትሆን አትቀርም። «እዚያ ኦክስፎርድ ሻይ መጠጣት እንጅ ደህና ነገር ያስተምሩን መሰለህ።» ነበር መልሱ።

መቅደስም ማፈሩ ሰለቻት መሰለኝ ከኛው ጋር ቁጭ ብላ መሳቅ ጀመረች።

□

አበራ በሂውስተን ተወዳጅነትን አተረፈ። እሱ ያልተገኘበት ግብግ፣ ግብግ አልመስል አለ። ማታ ማታ ራንዴቩ ኩዋስ ጨዋታ ለማየትና ቢራ ለመጠጣት ከሚሰበሰበው ሰው ይልቅ በአበራ ቱሻ ለመጠፍነን የሚመጣው ሰው ቁጥር በዛ። አበራ ባንኮኒው ላይ ይቀመጥና ለተጠየቀው ሁሉ

አስተያየትና መልስ ይሰጣል፤ የክለብ አጫዋች ነበር የሚመስል። «አበባው! ለአቤ አንድ ቤክስ ስጥልኝ» ይላል አንዱ። አንድ ቢራ ስጥልኝ ማለቱ ይበቃ ነበር፣ ከራንዴቩ ያለቤክስ ሌላ ቢራ አይሸጥምና። ከዚያ አቤን ራት ለመጋበዝ ሽሚያ ይጀመራል። የጥቁር አባይ ደንበኛ ጥቁር አባይ ካልሄድን ይላል፣ የንግስት ሳባም እንዲሁ። የአዋሽ ደምበኞችም ካቤ ስጥ ጋር የተቀላቀለ ራት ይመርጣሉ። ባለምግብ ቤቶቹም ይህንን አውቀው አበራ ሲመጣ ልዩ መስተንግዶ ነበር የሚያደርጉለት።

«አቤ!» አለ ቢራውን የጨበጠ አንድ ተንኮለኛ። «ከአክ ስፎርድ ዶክትሬትህን ይዘህ አዲስ አበባ ስትመለስ ምን አጋጠመህ?»

«ብዙ ዶላር ይገፍ ነበር።» ይላል አበራ፤ «እንግሊዝንና አሜሪካን የሚያገናኘውን ሳተላይት እኔ ነበርኩ የነደፍኩት። ለናሳም ብዙ የሙቀትን ጨረራ የሚለኩ መሳሪያወች አዘጋጅቼላቸው ነበር። ራሴን ማድነቅ አይሁንብኝ እንጅ፣ እኔ የፈጠርኩዋቸው መሳሪያዎች ባይገጠሙባቸው የናሳ ሳተላይቶች ቀፎ መንኮራኩሮች ናቸው ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም።»

ቤክሱን ማግ እያረገ የሚያዳምጠው መሸተኛ ይስቃል። አበራ ግን ታሪኩ አስደንቅዋቸው እንጅ በውሸቱ የሚስቁ አይመስለውም ነበር። ውሸቱን ራሱም ሳያምነው የቀረ አይመስለኝም።

«አዲስ አበባ ሆኜ» ይላል አበራ ወሬውን ሲቀጥል «ጥዋት ጥዋት ከቤቴ በረንዳ ፀሀይ መሞቅ እወድ ነበር። አንድ ትንሽ ልጅ አበባ ይዞ ሲያልፍ አየሁና አበባ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት። ከመንገድ የቀጠፈው አበባ ስለነበር አንድዋን መዞ ሰጠኝ። እኔም አንድ ዶላር ሸለምኩት። ልጁ ደስ ብሎት እየፈነጠዘ ሄደ። በበነጋው እንደለመድኩት የጥዋት

ፀሀየን ልሞቅ ከበረንዳ ብቅ ስል፣ ያዲስ አበባ ህዝብ አንድ አንድ አበባ ይዞ ተሰልፎ ይጠብቀኛል። የኛ አገር ሰው ነገር ይገርማል! በስንት ዘመን፣ ጥናትና ምርምር ያገኘሁትን ገንዘብ በአበባ ሊለውጠኝ ይፈልጋል።»

ትንሽ ይቆይና ሌላ ተንኮለኛ ነቀርሳን ለማጥፋት ስላደረገው ምርምር ይጠይቀዋል። አበራ ስለጥናቱና ስለአደረገው ሙከራ ሲያስረዳ አፉን አይዘውም። አንዳንድ አበራን የማያውቁ ሰዎች፣ «ኢንጂኔር መስለኸን ነበር እኮ!» ይሉታል። አበራ ለእንዲህ አይነቶቹ ብዙም ጊዜ አይሰጣቸውም። እጁን ከአንጉዋው ላይ ያጥፈውና መዳፉን ወደሰማይ ዘርግቶ፤ «"አበራ አንድ ዶክትሬት ብቻ ነው ያለው።" ያለህ ማነው?» ይላል። አዲስ ጥያቄ ይቀርባል፣ አበራም አዲስ መልስ ይሰጣል። አዲስ ስል በእርግጥ አዲስ ማለቴ ነው። አበራ ራሱ የሚያወራቸውን ወሬዎች፣ ብዙውን ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር የሚሰማቸው።

□

አበራ፣ የሚዋሸው ራሱን ለመካብ እንጅ ሌሎችን ለመጉዳት አልነበረም። ስለዚህ ካንዳንድ ሰዎች በስተቀር ብዙዎች ይወዱታል። በተለይ ኦስተን፣ ዳላስ፣ ጋልቭስተን፣ ሳንአንቶኒዮ የሚሄዱ አበሾች አበራን ይዘው መሄድ ይወዱ ነበር።

አንድ ቅዳሜ፣ ጉዋደኞቹ «ሳንአንቶንዮን አይተን እንምጣ።» አሉት። ከዚህ በፊት አይቶ የወደደው ከተማ ስለነበረ አላንገራገረም። ከመሀከላቸው የማይጠጣ ሹፌር ተመርጦ የመኪናው ቁልፍ ተሰጠው። የቢራ ስንቅ በማቀዝቀዣ ተያዘ። ያንን እየጠጡ፣ ያበራን ውሸት እየኮ መኮሙ፣ አበራ ሲደክመው ያስቴርን ዘፈን እያዳመጡ ፓኛውን ጎዳና ተከትለው ወደምእራብ ነጎዱ። አቤ ከቅርብ ጉዋደኞቹ ጋር ሲሆን አንዳንድዋን ውሸት ያምናል።

እንዲያ ሲሆንበት፣ መውጫ ሲያጣ፣ «ታዲያ፣ ወሬ ካለእብለት ቀሚስ ካለጥለት አያምርም።» ይላል። ሳንአንቶኒዮ ሲደርሱ አበራ ወሬውም መጠጡም አድክሞት ስለነበረ ድብን አርጎ እንቅልፍ ወሰደው።

ሳንአንቶኒዮ የሰለቻቸው ከተማ ነበርና፣ ከመሀላቸው አንዱ፣ «እባካችሁ ላሬዶ እንሂድ» አለ።

ሌላው ተቀበለና «እንዲያውም ኑ-ላሬዶ ብናድር ይሻላል፤ መጠጡም መኝታውም ሜኪስኮ ይረክሳል።» የሚል ሀሳብ አቀረበ።

ሜክሲኮ ለመግባት ፍቃድ አያስፈልግም። ከድንበሩ ፷፭ ማይል ከራቁ ብቻ ነው የሜክሲኮ ፖሊሶች የይለፍ ወረቀት የሚጠይቁት። ስለዚህ አበራን እንደተኛ ይዘውት ሜክሲኮ ገቡ።

የዚያን ለት ከእነአበራ ጋር ኑ-ላሬዶ አልሄድኩም። ከተማውን ግን አውቀዋለሁ። መጀመሪያ ሳየው ናዝሬት የገባሁ ነበር የመሰለኝ። መኖሪያ ቤቶቹ ዙሪያቸውን በግንብ አጥር ይታጠራሉ፤ አጥሮቹ አናት ላይ ደግሞ ሌባ ለመከላከል የጠርሙስ ስብርባሪ ይለጠፍባቸዋል። እኔ የሄድኩ ቀን ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ሲለቀቁ ነበር የደረስኩት። ልጃገረዶቹ የደንብ ልብሳቸውን ለብለው ሰማያዊ ከረባታቸውን አስረው ወደየቤታቸው ሲሄዱ፣ የእቴጌ መነንን ተማሪዎች ቁርጥ። ሰወቹ በጣም ደግ ናቸው። ቁዋንቁዋቸውን ባለማወቄ የደረሰብኝ ችግር አልነበረም፤ ጊዜ ወስደው፣ በምልክትም ቢሆን ጥያቄየን ለመመለስ ይሞክራሉ። ከአሜሪካ ግዛት ፩ ማይል ባልሞላ ርቀት ላይ ይህን ያህል የስነ-ልቡና ለውጥ መኖሩ ያስደንቃል።

ከተማውን ለቆ ወደ ደቡብ የሚጉዋዝ አውራ ጎዳና አለ።

ሜክሲኮዎቹ አውራ ጎዳና ፹፩ ይሉታል። የአበራ ጉዋደኞች ጎዳናውን ተከትለው ፲ ማይል ከነዱ በሁዋላ ከአንድ ቡና ቤት በራፍ አቆሙ። ቡና ቤትዋ ገፈርሳ ወይንም ሰንዳፋ የነበሩትን መናፈሻ ቡና ቤቶች ትመስላለች። ቤትዋ ኮርኒስ የላትም፣ ወለልዋም የሲሚንቶ ሊንሾ ነበር። አበራ ገና ከእንቅልፉ ተቀስቅሶ አይኑን እየጠራረገ ነበርና ያለበት ቦታ የት እንደሆነ አላወቀም። መጀመሪያ ኢትዮጵያ የተመለሰ መስሎት ነበር፤ የአውራው ጎዳና ጠርዝ በደንብ አለመሰራቱ፣ ሳር ያልሸፈነው የተጋለጠ መሬት በብዛት መታየቱ፣ አበራን ክፉኛ አሳስበው። ቢሆንም ጉዋደኞቹን መረበሽ ስላልፈለገ አብሮ ከቡና ቤትዋ ገብቶ ተቀመጠ። አሳላፊዎቹ የሜክሲኮ ሰወች መሆናቸውን ሲያውቅ ግን ግራ ተጋባ።

አስተናጋጁ ምን እንደሚጠጡ መጠየቅ ጀመረ። አበራም ሲፈራ ሲቸር «በድ-ላይት» አለ። ጉዋደኞቹ ሳቁና፣ ያለው ሜክሲኮ ስለሆነ አርፎ ኮሮናውን እንዲጠጣ መከሩት።

አበራ እናቱን እንደተረዳ ሁሉ አንገቱን ደፋ። ኮሮናው መጣለት፤ ግን ሊጠጣው ቀርቶ ባይኑም ሊያየው አልቻለም ነበር።

«ወደ ቤታችን እንመለስ።» አለ አበራ፤ በረጅሙ ተነፈሰና። ጉዋዶኞቹም የመጡት ለማደር እንጅ ለመመለስ እንዳልሆነ ነገሩት። አበራም በቁጣ፣

«እዚህ አምጡኝ ብየ አልለመንኩዋችሁም፤ ስለዚህ አሁኑኑ መመለስ እፈልጋለሁ!!» አላቸው።

ጉዋደኞቹም፣ አበራ እንዲህ ሲቆጣና ሲያዝን አይተውት ስለማያውቁ፣ ወደ ሂውስተን ለመመለስ ወሰኑ።

እንደተኮራረፉ፣ አበራም ለምን እንደተጨነቀ ሳያውቁ፣

ላሬዶንና ኑቮ-ላሬዶን የሚያገናኘው ድልድይ ላይ ደረሱ። መጀመሪያ መኪናው ህገ-ወጥ እፅ በሚያነፈንፉ ውሾች ተፈተሸ። ከዚያም አንድ የድንበር ፖሊስ የመኪናውን መስኮቶችና የሻንጣ ማስቀመጫውን ኮፈን እንዲከፍቱ ጠየቃቸው። ከማቀዝቀዣ ሳጥን በስተቀር ሌላ ምንም አልተገኘም። ቀጥሎም ፖሊሱ ሾፌሩን የአሜሪካ ዜጋ እንደሆነ ጠየቀው። ሾፌሩም «አወን ነኝ።» አለ፤ አጠገቡም የተቀመጠው እንዲሁ። ከአበራ ጎን ያለውም፣ የአሜሪካ ነዋሪነቱን የሚያስረዳ መታወቂያ ከቦርሳው አውጥቶ አሳየ። አበራ ግን የሚሰጠው መልስ ወይም የሚያሳየው ወረቀት አልነበረውም። ለካስ በጉብኝት ስም መጥቶ ነበር አሜሪካ ቀልጦ የቀረው። ያሜሪካ ፖሊሶች፣ አበራን ለሜክሲኮ ፖሊሶች አስረከቡት። የአበራም ጉዋደኞች የዚያን ለት ተመልሰው ሜክሲኮ አደሩ፤ ግን የሜክሲኮ ፖሊሶች አበራን የት እንዳደረሱት ማወቅ ሳይችሉ ቀሩ።

ወሬው ሲሰማ የሂውስተን አበሻ አዘነ። በሂውስተን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው ለችግራቸው መፍትሄ መፈለግ ልማዳቸው ነበርና፤ ለአሜሪካ ምክር ቤት አባሎች፣ ለቴክሳስ ገዥ፣ ለፕሬዜዳንቱ ሳይቀር የአበራን ጉዳይ እንዲከታተሉላቸው አቤት አሉ። ባለስልጣኖቹም ጉዳዩን እንደሚመረምሩ ቃል ገቡላቸው፤ ሆኖም ከዚያን ቀን ጀምሮ ስለአበራ የተሰማ ነገር አልነበረም።

□

አበራ ሜክሲኮ ሄዶ ከቀረ ሁለት አመታት አለፉ። የሂውስተንም ሰው አበራን ረሳው። አንዳንድ ሰዎች ሲዋሹ ብቻ ነበር አበራ ትዝ የሚላቸው። አንድ ቀን ከራንዴቩ፣ አበሻ ግጥም ብሎ፣ ግማሹ ከረምቦላ ሲጫወት የቀረው ደግሞ ቴሌቪዥን ሲመለከት አበራ ከየት መጣ ሳይባል ሰተት ብሎ ገባ። ሰው ሁሉ እየተነሳ ከሞት ተርፎ እንደተመለሰ ዘመድ እያቀፈ ይስመው ጀመር።

መተቃቀፉና መሳሳሙ ጋብ ሲል፤ «ከየት መጣህ አበራ? እንዴት ተመለስክ?» የሚለው ሰው በዛ። አበራ አሁን ከባልኮኒው ላይ እንደድሮው ሁሉ ተሰይምዋል። ቤክስ ቀርቦለት አንዱን አገባዶ ሁለተኛውን ጠርሙስ አጋምስዋል።

«ወንድሞቼ» አለ አበራ፣ «አለማወቅን የመሰለ ጥሩ ነገር የለም። እውቀቴ ነው እንደዚህ ያንከራተተኝ።»

የራንዴቩ ደምበኞች ቴሌቪዥኑ እንዲጠፋላቸው ጠየቁ፤ ያበራን ስጥ የሚስተካለል ነገር የለምና።

አበራ ውሸቱን ቀጠለ፣ «የአሜሪካ መንግስት የወታደር ምስጢር ይዞ ይወጣል ብሎ በመፍራት ፓስፖርቴን ሁሉ ነጥቆኝ ነበር። የኔ ፓስፖርት ፔንታጎን በጥብቅ ከሚጠበቅ ካዝና ውስጥ ነው የሚቀመጥ፤ ለዚህ ነበር ያኔ ከሜክሲኮ መመለስ ያልቻልኩት። የሜክሲኮ መንግስት ደግሞ እኔ መሆኔን ሲያውቅ ሳይንቲስቶች ካላሰለጠንክልን በስተቀር አንለቅህም ስላለኝ ይሄው ለሁለት አመት ከፍተኛ የሜክሲኮ ሳይንቲስቶች ሳስተምር ቆይቼ መምጣቴ ነው።» አለና የቀረችውን ቢራ ባንድ ትንፋሹ ጨረሳት። ሌላ ቢራ ተከፈተለትና ትንሽ ጎንጨት ብሎ ጠርሙሱን ከባልኮኒው ላይ በሀይል አስቀመጠው። «አሁንም ቢሆን የሜክሲኮ መንግስት ሊለቀኝ አልፈለገም ነበር።» አለ አበራ የጠጣው ቢራ እንደ ማግሳት እያለው፣ «የአሜሪካው ፕሬዜዳንት አበራን ካልሰጣችሁን የናፍታን ውለታ አንፈርምም ብሎ ስላንገራገረ ነው የተለቀቅሁት።»

ስጥ እንግዴህ!!!

ትዝታዬ

በ፲፱፻፷ዎቹ አመተ ምህረቶች መጀመሪያ ላይ (እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር ማለት ነው።)፣ አንድምታዊ-ምክንያቱ ሳይታወቅ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ወደ አሜሪካ መምጣት ጀመሩ። ፲፪ኛን ክፍል የጨረሰው ተማሪ ቁጥሩ በዝቶ፣ ኮሌጁ ደግሞ ተጣቦ ይሆን፣ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን የጨረሰው ተማሪ እንደልቡ ስራ የሚያገኝበት ዘመን አካቶ፣ ወይም በደፈናው የዘመኑ ቄንጥ ሆኖ፣ «እነንትና ያደረጉትን እኔ እንዴት አላደርግም።» በመሰኘት፣ ብቻ በዚያ ዘመን ብዙ ወጣት ፈለሰ።

አመጣጣቸው የአፄ ሀይለስላሴን መንግስት ጠልተው አልነበረም። እንዲያ አለመሆኑንም ከስራቸውና ከምኞታቸው ማወቅ ይቻል ነበር። ገሚሱ እየሰራ ይማራል - ተምሮም አገሩ መመለስ ነበር ናፍቆቱ። አብዛኞቹ እርሻና ንግድ ነበርና የሚማሩት፣ ምን አስበው እንደመጡ መገመቱ አያዳግትም። ቀሪው ደግሞ ሀብት ለማካበት ጠንክሮ ይሰራ ነበር ። ደክሞኛልና እግሬን ሰው ካላጠበኝ፣ አሞኛልና እናቴ ካላጎረሰችኝ፣ ይል የነበር ቅምጥል ሁሉ፤ ሰው የበላበትን ሳህን አጥቦ፣ ሰው የተኛበትን አልጋ አንጥፎ፣ ለሰው ምግብ አሳልፎ፣ ለሌሎች በር ከፍቶ፣ አስገብቶ፤ የሰው መኪና ተቀብሎ፣ አስተካክሎ አቁሞ፤ እንቅልፉን ሳይጠግብ ደብተሩን ተሸክሞ ትምህርት ቤት ሲሄድ ማየቱ እንዴት ተስፋ ይሰጥ ነበር ። ። ። «የስራን ክቡርነት በስራ የተማረ ወጣት፣ ይህንን አዲስ የስራ ጠባይ ይዞ አገሩ ቢመለስ፣ ምን ተአምር ይፈጠር ነበር?» ብሎ በልቡ የማያስብ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም። ግን፣ ሳይመለስ የቀረ ጥያቄ ሆነ።

ኢትዮጵያ፣ በየዘመኑ «ለመሰልጠን» የምታደርገው ጥረት

እንቅፋት አያጣውም። የአፄ ቴዎድሮስን ጥረት የውጭና የውስጥ ጠላት አበላሽው። የአፄ ሚንሊክንም ሙከራ ዙሪያዋን የከበቡዋት የአውሮጳ ተኩላወች አደናቀፉት። የአፄ ሀይለስላሴም ቢሆን ከሁለቱ የተሻለ አልነበረም። እንዲያውም፣ «ስልጣኔ ማለት ፈረንጅ ያደረገውን ማድረግ ነው።» የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ በኢትዮጵያውያን መንፈስ ውስጥ ስለተጠነሰሰ ወደፊት ከሄድነው ይልቅ ወደሁዋላ የተጉዋዝነው መንገድ ረዘመ። የ«ስልጣኔ»ን ጉዳይ ወደፊት እንመለስበታለን። ፍላጎቴ የበቀለንና የጉዋደኞቹን ታሪክ ላጫውታችሁ እንጅ፣ ልጨቀጭቃችሁ አልነበረም። አሁንም ሳልሰለቻችሁ በፊት ተረቴን ልጀምር።

በዚህ አበሻ አገሩን እየተወ ወደውጭ መጉረፍ በጀመረበት ዘመን ነበር፣ ተዘራ ካሜሪካ መጥቶ የቀረው። ከበቀለ ጋር የተዋወቁትም የሴንት ሉዊስ ኮሌጅ ተማሪዎች ሆነው ነበር። ከትምህርት መልስ ከሌሎች ጉዋደኞቻቸው ጋር ሲሆኑ፣ ትዝታቸው ኢትዮጵያ፣ ምሳሌያቸው ኢትዮጵያ፣ ምኞታቸውም ኢትዮጵያ ነበረች - ተመልሰው ምን እንደሚሰሩ፣ ተመልሰው ምን እንደሚፈጥሩ። ከመሀከላቸው የግል ጥቅሙን ካገሩ የሚያስቀድም አንድም አልነበረም። ብቻ እንዳሁኑ ሁሉ የዚያም ዘመን ልጆች አገራቸውን እንዴት እንደሚረዱ የየግላቸው የሆነ እቅድ ነበራቸው።

«እኔ ስመለስ፣» ይላል ተዘራ ፣ «ጎንደር ትልቅ ሆቴል እከፍታለሁ። በቀለ ከሰቲት አርሰሽ የምታመጭውን ገንዘብ እኔጋ ነው የምታራግፈው።»

«ይሄማ ከበዝባዥ አባትህ በምን ትሻላለህ?» ይላል በቀለ።

«አይ በቂ ብዝበዛዋን እንኩዋን እንተዋት። የኔ አባት አይደለም እኮ ፫፻ሺ እግር በሀርዛፍ ያስተከለልኝ።» ይላል ተዘራ ደሞ፣ በቀለን የጎሪጥ እየተመለከተው። የበቀለ አባት፣

ተምሮ ሲመለስ ሽጦ የሚቁዋቁዋምበት በሀርዛፍ እንዳስተከሉለት፣ በቄ ሲያቀብጠው አንድ ቀን አውርቶ ነበርና።

«ኩበት ስትጠፈጥፍ ከመዋል ባዳነህ፣ የአገርህ አፈር እየታጠበ እንዳይሄድ በተከላከለ ፣ አባቴን ምን አርግ ትለዋለህ? ዛፉ የተተከለው ተራራማና ድንጋያማ ቦታ ነበር። በሀርዛፍ ባይተከለበት ኖሮ በዝናብ ከመታጠብ በቀር ምን ይሆን ነበር?»

ተዘራ ለዚህ ብዙም መልስ የለውም - መሬት የመንግስት ነው ተብሎ፣ ዛፍ የሚተክል ጠፍቶ፣ እንጀራ መጋገሪያ ቅጠል ብርቅ የሚሆንበት ዘመን እንደሚመጣ፣ ቤት የመንግስት ነው ተብሎ፣ ቤት ሰርቶ የሚያከራይ ጠፍቶ፣ አንድ ክፍል ውስጥ ፲ ሰው የሚታጎርበት ስርአት እንደሚሰለጥን የተገለፀለት ይመስላል።

«ምነው ባትቸኩል። ገንዘብ የማገኝበትን መንገድ እንጅ፣ ለምን እንደማውለው መች ነገርኩህ?»

«መች አጣሁት ተዘራ! ሌላ ሆቴል ባህርዳር ትከፍታለህ፣ ከዚያ አዲስ አበባ፣ ቀጥሎም ድሬዳዋ . . . »

«እንዲያ ማድረጌ አይቀርም። ፍላጎቴን ለማምዋላት የአንድ ሆቴል ትርፍ አይበቃኝም። አየህ በቀለ፣ የኢትዮጵያውያን አንዱ ችግራችን ቶሎ እንጠግባለን። አንድ ንግድ ጀምረን ከተሳካ፣ መልሰን መላልሰን ተመሳሳይ የሆነ ሌላ ንግድ በመክፈት ሀብታችንን ማካበት አናውቅበትም፣ እንዲሁ ያቺኑ ስንቆረጥም እናረጃለን።»

«አሁንም እንደምን ሀብታም እንደምትሆን እንጅ፣ ገንዘብህ እንዴት ለሰው እንደሚጠቅም አይደለም የምትነግረኝ።» አለ በቀለ የሽሙጫ ሳቅ እየሳቀ።

«ያንድ ሰው ሀብታም መሆን ራሱ ለሀገር ይጠቅማል። ሀብታም ምን ንፉግ ቢሆን ሰራተኛ መቅጠሩ አይቀርም። ገንዘብ ሲበዛ ሀብታሙ በእርሻና በኢንዱስትሪ ግንባታ ላይ ስለሚያውለው፣ አገሪትዋ ታድጋለች። ለምን መሰለህ አሜሪካኖች በእርሻና በእንዱስትሪ የመጠቁት? ስለዚህ አበሾች ሀብታም ስታዩ አይናችሁ ደም መልበሱ መቆም አለበት። ያንድ ሀገር ሀብት የዜጎችዋ ቅሪት ድምር እንጅ፣ በከርስዋ የያዘችው ማእድን አይደለም።»

ተዘራ መፅሀፍ ማንበብ ስለሚወድ የማርክስንና የሌኒን መፅሀፎች አንበልብሎአቸዋል። ዛሬ ግን የማርክስ ተከታይ መሆኑን ዘንግቶት ይሁን ወይ እውነተኛው የሰውነት ተፈጥሮው አገርሽቶበት፣ ወይም እንዲሁ በቀለን ለማበሳጨት፣ አዳም እስሚዝን ሆንዋል።

«ነገሩ ጥሩ ነው።» አለ በቀለ፣ «አሁን የነገርከኝ ሁሉ ግን ኩባንያህን ለማስፋፋት የምታደርገውን ጥረት ነው። ኩባንያህ የሚዳብረው ለህዝብ ጥቅም ሳይሆን ትርፍህን ለማካበት ነው። ደሀው ለፍቶ ጥሮ ላንተ የሚጥም ትርፍ ካላገኘህበት እርሻውም ያድራል፣ ፋብሪካውም ይዘጋል። እኔ ማወቅ የፈለግሁት ግን፣ በምታገኘው ንፁህ ትርፍ፣ ተጨማሪ ሀብት ለማካበት ሳይሆን፣ ከሌሎች የምትጠብቀው ክፍያ ሳይኖር፣ ደስታቸውን ለማየት ብቻ የምታሳየውን ደግነት ነው።»

«እኔ በራሴ የምሰራው፣ የግሌ ጉዳይ ነው። መጀመሪያ ግን፣ ለሰው ደስታ ሳይሆን ለራስ ጥቅም ብቻ የሚደረግ ሀብት የማካበት ጥረት ለሀገር ጠቃሚ መሆኑን እንድትረዳ እፈልጋለሁ። ያን ካመንክ ብቻ ነው ከንግድ አለም ወጥተን ወደ ግል ጥያቄ የምንሸጋገር።» ይለዋል ተዘራ።

«ይህንን ለማመን ችግር የለብኝም። አንተ ነህ እንጅ

የማርክስ ተከታይ ነኝ ብለህ የምትጨፍር እኔ አይደለሁም። እኔ ሀብታም መሆን እፈልጋለሁ። አንተ ያልከውንም ሁሉ አደርጋለሁ። ነገር ግን፣ ገንዘብ በቁሙ ደስታ አይሰጠኝም። ደስታየን የማገኘው ገንዘቤን በፋንታው ክፍያ ሳልጠብቅ ለወገኖቼ ሳጠፋው ብቻ ነው።»

«ነገሩ እንኩዋን እንደዚያ አይደለም።» ይላል ተዘራ፣ በቀለን አዳምጦ ሲጨርስ። «በየደረስክበት መመስገኑ፣ መደነቁ፣ መከበሩ፣ ክፍያ አይመስልህም እንጅ ክፍያ ነው።»

እንግዴህ ክርክሩ የጀመሩት መሆኑ ቀርቶ ወደ ሌላ አቅጣጫ ማምራቱ ነው። ብቻ ዞሮ ዞሮ ወሬው ሁሉ አገራቸው ስትበለፅግ ለማየት ያላቸውን ፍላጎት ያንፀባርቅ ነበር። ተዘራ ጎንደር ቢወለድም ያደገው አዲስአበባ ነበር። እሱም ዘመዶቹም ትግርኛ ይናገራሉ። ሆኖም፣ ተዘራ ጎንደሬ እንጅ ሀማሴን ነኝ ብሎ አያውቅም። እንዲያውም የኤርትራ መገንጠል ወሬ ሲነሳ፣ ከሌላው ቀድሞ መገንጠላቸውን የሚቃወም ተዘራ ነበር፤ ያውም እሳት ለብሶ፣ ያውም እሳት ጎርሶ።

ሳያስቡት ወቅቱ የደርግ ሆነ። ህዝቡ ሀብቱን ተቀማ። መቀማት የነበረባቸው ዘራፊዎች ነበሩ። ግን እፍኝ በማይሞሉ ሌቦች ሳቢያ እድሜውን ሙሉ የለፋው ነጋዴ ቤቱን፣ ሆዱን ቁዋጥሮ፣ አጠራቅሞ መሬት የገዛው ገበሬ መሬቱን ተነጠቀ። ይህም አድራጎት ግፍ እንጅ ሌላ ስም ሊሰጠው አይገባም። እንግዴህ አገር የመመለሱ ነገር ለጊዜው መቆየት ነበረት። በቀለም የመጀመሪያውን ዲግሪ አጠናቆ ታክሲውን እየሾፈረ ሁለተኛውን ተያያዘው።

«ለምን ብለህ ነው አሁን የምትማር? አገርህ በፋሽሽት እግር ስር ወድቃ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተገንጣዮች ሴራ ተጠምዳ፣ ምን አተርፋለሁ ብለህ ነው የምትማር?» ይላል ተዘራ።

ተዘራ ለሀገሩ የነበረውን ፍቅር ያደንቅ ነበርና፣ በቀለ ብዙም አይከራከርም። ብቻ ለወሬው ያህል፣ «ምን አርግ ትለኛለህ ተዘራ? ካገሬ የወጣሁት እማራለሁ ብየ ነው፤ ምን አርግ ትለኛለህ?» ይላል።

□

ኢህአፓ ስሙ ተጋኖ ይወራ የነበረበት ዘመን ነበርና፤ ተዘራ በሴንት ሉዊስ ዋና የኢህአፓ ደጋፊ ሆነ። በሁዋላ ግን ኢህአፓ እየደበዘዘ ሲሄድ ተዘራም አብሮ ደበዘዘ። በዚህ ምክንያት አንዳንድ ሰወች ተዘራን ያሙት ነበር። በቀለ ከሰማ ግን አያሳልፋቸውም።

«አንተ ምን ሰርተህል?» ይላል በቁጣ «ማንን ደግፈህል? ተዘራ የተቻለውን ሰርትዋል፣ ያ ብቻ ካንተ የተሻለ ኢትዮጵያዊ ያደርገዋል።»

የበቀለና የተዘራ ጉዋደኝነት ጠነከረ። ለሚያያቸው ወንድማማች እንጅ ጉዋደኛሞች ብቻ አይመስሉም ነበር። መቼም እድሜ እየገፋ ሲሄድ ሌሎች የህብረተሰብ ግዳጆች መፈፀም ነበረባቸውና፣ በቀለ ትዳር ያዘ፤ ልጆችም ወለደ። ከተዘራ ጋርም ጨርሶ ባይለያዩም በየቀኑ መተያየታቸው ቆመ።

የበቀለ ልጅ ክርስትና ለት፣ ተዘራ፣ አረጋ፣ ታየች እና ሌሎችም ከበቀለ ቤት ተሰብስበው፣ የፖለቲካ ወሬ ተጀመረ።

«ኢትዮጵያ ውስጥ የተደረጉና የሚደረጉ ጦርነቶች በሙሉ የውጭ እጅ አለበቸው። የሶማሌው ጦርነት የተደረገው፣ የካርተርን ፍላጎት ለማምዋላት ነበር። የኤርትራው፣ አረቦችን ለማስደሰትና ገንዘባቸውን ለመውሰድ ሲሆን፣ የትግሬውም እንዲሁ የውጭ ጌቶቻቸውን ፍላጎት

ለማምዋላት ይመስለኛል። ኮሚኒስት ነን ካሉ፣ ኢትዮጵያዊ ከሆኑ፣ ከደርግ ጋር ምን ያጣላቸዋል?» አለ አረጋ።

«ደርግ ይቅር።» አለች ታየች ተቀበለችና፣ «ከኢአህፓ ጋር የሚያዋጋ ምክንያት ከየት አገኙ?»

ጊዜው ደርግ የተዳከመበት፣ ትግሬን ጨርሶ ለቆ ወሎን የሚጠብቅበት ወቅት ነበር። ተዘራ ፊቱ የፈዝ ፈገግታ ለብሶ፣

«የነፃነት ትግል ሁሉ በጨቁዋኞች አይን ሲታይ፣ የባንዳ ድርጊት ይሆናል። የናንተም አስተያየት ከዚህ የተለየ አይደለም። ግን ይውላል ያድራል እንጅ ነፃነታችንን መጎናፀፋችን እንደሁ አይቀርም።» አለ።

«አዲሱ የኢህአፓ ፍልስፍና ነው ወይስ ተዘራ ጎንደሬነትሽን ሰረዝሽ?» አለ በቀለ እየሳቀ። በቀለ በልቡ ልብ የተዘራ አያቶች ከሀማሴን እንደመጡ ያውቅ ነበር። «ግን አንድን ሰው አማራ፣ ኦሮሞ ወይም ትግሬ የሚያደርገው ተወልዶ ያደገበት ባህል እንጅ ሰውነቱ የተሰራበት ቅንጣት አይደለም።» የሚለው እማኔ ተክታይ ነበርና፣ «ተዘራ ጎንደሬ ነኝ ካለ ጎንደሬ ነው።» የሚል አቁዋም ነበረው። ተዘራ ግን ጎንደሬነቱን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነቱንም ክድዋል። ለሻቢያም መዋጮ መክፈል ከጀመረም ሰንብትዋል።

ደርግ ወደቀና የወያኔ መንግስት ሲቁዋቁዋም፣ ተዘራ በ ሴንት ሉዊስ ዋና የሻቢያ ሰው ሆነ። የቆዩ የሻቢያ ደጋፊዎች እንኩዋን «ምን አይነት እስስት ነው!» ብለው ታዘቡት። በቀለማ አንድ ቀን ከመንገድ አይቶት ካልደበደብኩ ብሎ፣ አበራ ነው፤ «እባክህ ተወው፤ ይህ የሚረባ ሰው አይደለም። ነገ ወያኔወች ሲወድቁ ደግሞ የኦነግ አባል ይሆናል።» ብሎ ያስጣለው። ከዚያን ቀን

ጀምሮ ተዘራና በቀለ ተያይተው አያውቁም። እንዲውም ተዘራ አስመራ ኩባንያ ሊከፍት ሄዶ፣ አገሩ ተመንኖ የሚኖርበር እንጅ ተነግዶ የሚከበርበት ሆኖ ስላላገኘው፣ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ገብቶ አዲስ አበባ ይነግዳል እየተባለ ይወራል። በቀለ ግን ማየቱ ብቻ ሳይሆን ስሙን መስማቱ እንኩዋን ስላስጠላው፣ በወሬ መሀል ተዘራ ከተነሳ ክፍሉን ጥሎ ይወጣ ነበር።

በዚህ መሀል አበራ ደገፉ ወያኔን የሚቃወም ድርጅት በሴንት ሉዊስ አቁዋቁመ። በቀለም አባል ሆነ። በቀለ እንኩዋን፣

«ሴንት ሉዊስ ሆኖ ወያኔን መቃወም አይቻልም። ሲሆን ገብቶ መታገል፣ ያ ካልሆነ ደግሞ የሚታገሉትን አርበኞች በገንዘብ መርዳቱ ነው ጠቃሚ፤ ሌላው ግን ወሬ ማብዛት ነው።» ይል ነበር።

አበራ ግን፣ «የለም በቀለ፣ ይረባሉ የማትላቸው ትናንሽ ድርጊቶች ተደምረው ነው ድልን የሚያስገኙ።» ይለዋል። በቀለም አምኖበት ሳይሆን ከሰው ላለመለየት ሲል የሴንት ሉዊስ ሰዎች ተሰብስበው የሚያደርጉትን ሁሉ አብሮ ያደርግ ነበር።

ከጥቂት አመታት በሁዋላ፣ በቀለ እንደጠረጠረው ሁሉ፣ አሜሪካና አውሮፓ በሚደረገው ተቃውሞ ሳይሆን፣ ካገር ውስጥ በሚታገሉት አርበኞች ሀይል፣ በወያኔና በሻቢያ የተመሰለው የፈረንጆች የእጅ አዙር አገዛዝ ተፈነገለ። የአሜሪካው የስለላ ድርጅት፣ የእስራኤሉም መንግስት ሆኑ ሌሎች የአውሮጳ መንግስታት አዲሱን መንግስት ታዛዣቸው ለማድረግ፣ ያም ካልሆነ የአዲሱ መንግስት ባለሙዋል ለመሆን ሞክረው ነበር። ግን የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳምና፣ አዲሱ መንግስት፣ «ኢትዮጵያም ሆነች ጠቅላላው የጥቁር ህዝብ ነፃ ሊሆን የሚችለው ስራችን ያለ

ነጭ እርዳታ መከናወን የቻለ እንደሆን ብቻ ነው፡፡» የሚለውን መርሆ እንደሚከተል በግልፅ ስላወጀ፣ በእጅ አዙር እንጅ በቀጥታ ተዕእኖ ለማሳደር መሞከር ትተዋል፡፡

አዲሱን መንግስት ለማቁዋቁዋም ከተጋበዙት ሰዎች አንዱ አበራ ነበር፡፡ አበራን ለመሸኘት የተደረገ በአል ላይ፤ ግብግቡ አብቅቶ ሰው ወደቤቱ መበታተን ሲጀምር፣

«እግዴህ በቁ መጥተህ እንደምታየኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡» አለ አበራ፤

በቀለ ብቻ አይደለም ብዙ አበሾች አበራን በቅርቡ እንደሚጎበኙት ቃል ገቡ፡፡ የሴንት ሉዊሱ ማህበር የፖለቲካ ማህበርነቱ ቀርቶ ወደ ልማት ማህበርነት እንዲለወጥም የተስማሙት ያን ማታ ነበር፡፡

ባመቱ፣ በቀለ ባለቤቱን ይዞ፣ ልጆቹን አስከትሎ፣ በሉፍታንሳ ደያራ ወደ አገሩ ጉዞ ጀመረ፡፡ የኢትዮጵያን አየር መንገድ ወያኔወቹ ጨርሶ አጥፍተውታል፤ አዲሱ መንግስት እንደገና ለማቅዋቅዋም እየጣረ ነው፡፡ ግን ጊዜ ይፈጃል፣ መገንባት እንደማፍረስ ቀላል አይደለምና፡፡

«ዋ!» አለ በቀለ፤ በመስኮት የሰሀራን በረሀ እየተመለከተ፤ «ያን የመሰለ አየር መንገድ እንዳልነበረ አደረጉት፡፡»

«የተማረ ሰው እንደድሮው ብርቅ አይደለም፡፡ ስለዚህ አየር መንገዱንም ሆነ ሌላውን ሁሉ ለመንገባት የድሮውን ያህል ጊዜ አይፈጅም፡፡» አለችው ባለቤቱ፡፡

«ይሆን ይሆናል፡፡ ግን፣ የደያራው ዋጋ ከድሮው አስር እጥፍ ነው፡፡ ቤንዚኑ፣ ብሎኑ፤ አስፋልቱ፣ ቅባቱ፤ ምን አለ ያልተወደደ፣ ካቅማችን በላይ ያልሆነ፡፡» አለ በቀለ እንደመዝፈንም እየቃጣው፡፡ ክራር ቢኖረው ኖሮ . . .

ክራር መምታት ቢችል ኖሮ ... ምን ያደርጋል፤ የኛ አገር ነገር ... ውሀ ቅዳ፣ ውሀ መልስ።

ኢትዮጵያ ሲደርሱ፣ ዘመድ ደብረ-ዘይት አለም አቀፍ ድሬ-ደያራ ድረስ መጥቶ ተቀበላቸው። አንድ ሳምንት ያህል በየዘመዱ ቤት ሲጋበዙ፣ ሲበሉ ሲጠጡ ... ሲታመሙ ከረሙ። በሁለተኛው ሳምንት ግጥው ጋብ አለ፤ ሆዳቸውም ውሀውን ለመደው። በቀለ አበራና ሌሎች አዲስ አበባ የሚኖሩ ጉዋደኞቹን ማሰብ ጀመረ። በልቡ የሳምንት ፕሮግራሙን አወጣ። በልጅነቱ የበላባቸው ፓስቴ ቤቶች፣ የተማረባቸው ትምህርት ቤቶች፣ ያጠናባቸው የባህርዛፍ ጫኮች፣ የሰከረባቸው ጠጅ ቤቶች ... እነዚህን ሁሉ እየዞረ ለማየት ወሰነ።

«እነዚህ በየስርቻው የተወሸቁ የቆርቆሮ ቤቶች... ያቺ የማትታጠብ የጠቆረች የፓስቴ ቤት ፎጣ፣ በሲባጎ ታስራ ከእጅ መታጠቢያው በላይ የተንጠለጠለች ሳሙና ናፈቁኝ ስል ሰው ቢሰማ ጉድ ይላል።» አለ ለራሱ።

ግን ትዝታ ንፁህ መሆን የለበትም። ትዝታ ያለፈ የማይደገም ሁኔታ ስለሆነ፣ ከወደዱትም እንደነበር፣ ከጠሉትም እንደነበር ነው።

በቀለ እነዚያን የልጅነት አመታት ከምንም አብልጦ ስለሚወዳቸው ነግቶለት ከመርካቶ እስከካዛንችስ ያለውን መንደር እስኪያስስ እንቅልፍ አልወስደው አለ። አብዛኛውን ነገር ከ ፴ አመት በሁዋላ እንደተወው እንደማያገኘው ያውቅ ነበር። ብቻ ከመንገድ ዳር ቆሞ የሚያያቸውን ትናንሽ ልጆች «እዚህጋ የነበረችው የሳር ጎጆ፣ የዘውዲቱ ጠላ ቤት፣ የት ሄደች?» ብሎ ሲጠይቅ፤ ልጆቹ ደግሞ ተያይተው፣ «የማነው ፋራ!» ብለው ጥለውት ሲሄዱ ታየውና፣ ከት ብሎ ሳቀ።

«ምን ሆንክ በቀለ፣ ብቻህን ትስቅ ጀመር እንዴ?» አለችው ባለቤቱ - በቀለ ሲገላበጥ እስዋንም አላስተኛ ብልዋት ነበርና።

«የዘውዲቱ ጠላ ቤት ትዝ ብሎኝ ነው የሳቅሁት።»

«ይልቅስ ተኛ፤ ነገ ደግሞ አበራን መፈለግ እንዳለብህ እንዳትረሳ።» አለችው።

እውነትም ያበራን ነገር ረስቶታል። አበራ ያዲሱ መንግስት የይለፍ ፈቃድ ክፍል ሀላፊ በመሆኑ፣ ማግኘቱ ከባድ አይደለም።

«አበራ እሺ ካለኝ ነገ ፓስቴና ጠጅ ቤት ነው ይገርው የምዞር።» ብሎ አሰበ።

ሊነጋጋ ሲል እንቅልፍ ሸለብ አደረገው። ግን ደርሶባችሁ እንደሆነ፣ ሊነጋጋ ሲል የሚወስድ እንቅልፍ ቅዠት ይበዛበታል። በቀለም የዚህ አይነቱ ቅዠት ጀመረው። የወያኔ ወታደሮች በመኪና ሆነው ያባርሩታል፤ መንገዱ ሰፊ ነው። እንዲያውም 'አይ-70' ይመስለዋል። እንደበረረ ከመንገድ እወጣለሁ ሲል ከድልድዩ ምሶሶ ጋር ይጋጭና መኪናው ይቆማል። ወያኔወቹም እዛው ጥያቄ ይጀምሩታል።

«ኢትዮጵያ አትነጣጠልም ብለሀል አላልክም?»

«ብያለሁ።»

«ምኒልክ ታላቅ ንጉስ ነው ብለሀል አላልክም?»

«ብያለሁ።»

«የአሜሪካ የሰላም ልኡካን መምህራን ለኢትዮጵያ አያስፈልጉዋትም ብለህል አላልክም?»

«ዶክተር ታየ ይመስለኛል እንዲያ ያለው፤ ሆኖም እስማማለሁ።»

«ይሄንን ፍርድ ቤት መውሰድም የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ከገደል ላይ ወርውረው።»

«በኛ ከሚሳበብ አንድ ዱርዬ አማራ ወይም ኦሮሞ ፈልገን እናስገድለው»

ዱርዬዎች ከገደል ሊወረውሩ ሲጎትቱት፣ ብንን ይላል። የመኝታ ቤቱ መስኮት ተከፍቶ የጥዋት ፀሀይ ገብታ ፊቱን ታሞቀዋለች። እንደድሮው ቢሆን ብርድልብሱን ይወረውርና በሆዱ ተኝቶ ጀርባውን ፀሀይ ያስመታ ነበር። ዛሬ ግን እንቅልፍ ስላልተኛ ይሆናል፣ ፀሀይዋ አቃጠለችው። እንደቀፈፈው ካልጋው ተነሳና ገላውን ታጠበ። ተጣጥቦ ሲጨርስ ቁርስ ቀረበለት። እንደአሜሪካ rasain-bagel (የዘቢብ ሙልሙል) በቡና ውጤ መሄድ የለም። የበቀለ እናት፣ ጥዋት ተነስተው ቅንጬውን፣ ጨጨብሳውን፣ ግንፍልፍሉን ባይነት ባይነቱ አዘጋጅተዋል።

«እዛ ፈረንጅ አገር አሸር ባሸሩን ለምዶ፣ የኔን እጅ ረስቶታል - አሁንማ!» አሉ የበቀለ እናት። ለበቀለ ሳይሆን ለአስቴር ማውራታቸው ነበር። ይቅርታ፣ አስቴር የበቀለ ሚስት ናት።

«አላወቅሽም እንጅ፣» አለ በቀለ «ቁርሴ ጨጨብሳ፣ ምሳየ ጨጨብሳ፣ ራቴም ጨጨብሳ ቢሆንልኝ እወድ ነበር።»

«በል እንግዴህ በደንብ ብላ። ለራትህም ጨጨብሳ ይሰራልሀል። ልክ እንደአባቱ» አሉ የበቀለ እናት-

እንደመተከዝ ብለው «በላምበራስም ጨጨብሳ ይወዱ ነበር።»

ቁርሱን በልቶ ሲጨርስ፣ እንደልጅነቱ ሁሉ ሆዱን ፀሀይ ሊያስመታ ከግቢው ወጥቶ ግንቡ አጥር ላይ ተቀመጠ። አንድ ኒስትሮ ልጅ ይመጣና፣

«ጋሼ ላሳምር?» ይለዋል።

በቀለ እምቢም እሽም አላለም። ብቻ ጫማውን ከኒስትሮው እቃ ላይ አስቀመጠው። አሜሪካ ሆኖ ጫማው ተጠርጎ አያውቅም። አዲስ አበባ ግን፣ ፀሀይ ሲሞቁ፣ አውቶቢስ ሲጠብቁ፣ ወይም እንዲሁ ከንገድ ቆመው ወሬ ሲመለከቱ ጫማ ማስጠረግ የተለመደ ነገር ነውና፣ በቀን ቢያንስ ሶስቴ ያስጠርግ ነበር።

«ስምህ ማነው?» አለው ኒስትሮውን፣ በቀለ።

«ፀጋየ።»

«ትምህርስ አትማርም?» በሰኞ ምድር ጫማ ሲጠርግ እንደማይማር ተጠራጥሮ።

«አልማርም።»

«ለምን?» አለ በቀለ፣ ዋናው ጥያቄ ይሄ ነበር።

«ከተሰራ ፪ አመት የሆነውን ያባቴን ሱቅ፣ ወያኔዎች አላግባብ ነው የተሰራው ብለው አፈረሱት። አባቴም በንዴት ታሞ ከቤት ዋለ። አሁን አባቴን የምረዳው እኔ ብቻ ስለሆኩ መማር አልቻልኩም።» ነበር መልሱ።

በቀለ ክፉኛ አዘነ፣ ጥያቄ ማብዛቱ የዚያን የ ፲፩ ወይም ፲፪ አመት ልጅ የልብ ቁስል መነካካት ስለመሰለው ዝም አለ።

በቀለ እንዳዘነ መኪናውን አስነስቶ አበራን ለመጠየቅ ሄደ። ከአበራ መስሪያ ቤት ሲደርስ ቢሮውን ፈልጎ አንኩዋኩዋና ገባ። አበራም በቀለን ሲያየው ደነገጠ።

«ከየት መጣህ በቀለ?» አለ ከመቀመጫው ተነስቶ፣ ሁለት እጆቹን በሰፊው ዘርግቶ፣ ወደ በቀለ እየተራመደ። «መቼ መጣህ በቀለ?»

«አንድ ሳምንት ሆነኝ።»

«ምነው ብትደውልልኝ? - ካሜራካ ቢቀር እዚህ ከደረስክ በሁዋላ!»

«እንደዚህ ስትደነግጥ ለማየት ፈልጌ ነው።»

«አይ በቀለ!» አለ አበራ፣ አቅፎ ከሳመው በሁዋላ በእጆቹ ትከሻዎቹን ራቅ አድርጎ ይዞ፣ ፎቶግራፍ እንደሚመለከት ሁሉ የበቀለን ፊት እየመረመረ።

«አስቴርም መጥታለች?»

«አወን።»

«ሚጢጢሳ?»

«ሁለቱም ልጆች መጥተዋል። አሁን አድገው አታውቃቸውም።»

«ሴንት ሉዊስ ደህና?»

በቀለ የሴንት ሉዊስን ደህንነት ለማውራት ሲጀምር ስልክ ተደወለ። አበራ ስልኩን አነሳና መነጋገር ጀመረ። አነጋገሩ ከሚያከብረው ወይም ከሚፈራው ሰውጋ የሚያወራ ያስመስለው ነበር። ስልኩን ዘጋና፣

«በቀለ፣ ሌላ ቢሮ ለስራ ጉዳይ ጠሩኝ፣ ቶሎ እመለሳለሁና ቁጭ ብለህ ጠብቀኝ። ተላላኪው ቡና እንዲያመጣልህ እነግረዋለሁ።»

«እሺ አበራ፣» አለ በቀለ «ከ ፴ ደቂቃ በላይ ከቆየህ ነገ እመለሳለሁ።»

«የለም! ቢበዛ ፲ ደቂቃ ነው የምቆየው። ቁጭ በልና ጠብቀኝ፤ ምሳ አብረን ነው የምንበላው።»

አበራ ከሄደ በሁዋላ በቀለ ከመቀመጫው ላይ እንደመንጋለል አለና የክፍሉን ጣሪያና መብራት ተመለከተ። ጣልያን ሰርቶ ጥሎት የሄደ ቤት ስለነበረ ኮርኒሱ ሩቅ ነው። ባሁኑ ቤት አሰራር ሁለት ፎቅ ይወጣዋል። ከዚያ ከመቀመጫው ተነሳና ግድግዳውን፣ ጠረቤዛውን እና የመፅሀፍ መደርደሪያውን መረመረ፣ የተሰነጠቀ ግድግዳ ወይም ሳይጠረግ የቀረ ቁሻሻ የሚፈልግ ተቆጣጣሪ ይመስል ነበር። መደርደሪያውን ተጠግቶ መፅሀፎቹን መመልከት ጀመረ። የህግ መፅሀፍ ይበዛበታል፣ አልጣመውም። በመጨረሻም ከመስኮቱ ቆሞ ውጭውን ቁልቁል ማየት ጀመረ። መስሪያ ቤቱ ዳገትላይ ስለነበር፣ በስተቀኝ ጥቁር አንበሳ ሀኪም ቤት፣ የንግድ ባንክና፣ ብሄራዊ ትያትር ወለል ብለው ይታዩታል። ከፊት ለፊት እስከ መስቀል አደባባይ ያሉ ፎቆች አናታቸው ተቸምችምዋል። እሱ ከሄደ ስንት ህንፃ ተሰርትዋል! የሚያስታውሳቸው ቤቶች በጣት ይቆጠራሉ።

«አዲስአባ እንዴት አደገ!» አለ ጮክ ብሎ፣ በቀለ የግንፍሌ ውሀ ንፁህ ሆኖ የሚጠጣበትንና የቀበና ውሀ የሚዋኝበትን ጊዜ አስታወሰና፦

«አይ መሰልጠን፣ ማደግ፣ መሬት ሰማዩን ማቆሸሽ፣ አየር ውሀውን መበከል፣» አለ፤ አሁንም ክራር ጠፋ እንጅ እንደማንጎራጎር እየሞካከረው።

በመስኮት ውር ውር የሚሉትን መኪናወች እየተመለከተ፣ በልቡ ፴ አመታት ወደሁዋላ ተመለሰ። ከጉዋደኞቹ ጋር ከጎማ ውስጥ የወጣ ክብ ሽቦ እያንከባለሉ ወደ ቀበና ሲጉዋዙ ታየው። ቀበና ደክምዋቸውና እርብዋቸው ስለሚደርሱ መጀመሪያ ሾላ ይበላል። ጠገብ ሲሉ ድካሙ ሲለቃቸው ዋና ይጀመራል። የሚዋኙበት ቦታ ጥልቀቱ የታወቀ፣ ዘለው የሚገቡበት ቁዋጥኝ ድንጋይ ያለበት ቦታ ስለሆነ፣ ዋና የሚችሉት ከላይ ዘለው ይገባሉ። ውሀው ሲቀዘቅዛቸው ደግሞ ይወጡና ራቁታቸውን ፀሀይ ካበገነው ጥቁር፣ ልስልስ አለት ድንጋይ ላይ ይተኛሉ። ሲርባቸው ሾላ፣ ሲጠማቸው ቀበና፣ ዋናው ሲሰለቻቸው ደግሞ፣ ያችን የጎማ ሽቦ እያንከባለሉ ወደቤታቸው ሲመለሱ ታየው።

«ዋ!» አለ በቀለ «ሳናውቀው ነው እንጅ ለካስ ገነት ነበር የምንኖረው።» ትንሽ ዝም ብሎ ቆየና፣ «አይ ስልጣኔ!» አለ እንደገና። «የስልጣኔ ጥቅሙ ጠመንጃ ለመስራት ብቻ ነው። እሱም ቢሆን ሰለጠንን የሚሉት ስላላቸው፣ ላለመጠቃት ነው እንጅ ሌላ ፋይዳ የለውም። ስልጣኔ ስለፈጠራቸው መድሀኒቶች ያወራሉ። ስልጣኔ ያመጣቸውን በሽታወች ግን ይረስዋቸዋል። በስልጣኔ ሳቢያ የሰው እድሜ መርዘሙን ይለፍፋሉ፤ አለም መጣበብዋና የተፈጥሮ ሀብትዋ ማለቁ ግን አይታያቸውም። በመጨረሻው ግን መሰረታዊ የጥባቆን ህግ ስለሚያከብር ድል የተፈጥሮ ነው። የሀጢአት ዋጋው ሞት ነው፤ ስልጣኔም ሀጢአት ነውና፣ ዋጋው የተለየ ሊሆን አይችልም። ይህንን አጥተውት አይመስለኝም፣ ታሪካዊ ሀቅ ነውና። ነገሩ ያቺ ክቡር ሰራተኛ ፍጡር አለች ተብላ እንደምትታማው 'እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል' ይመስለኛል።»

«አሁን ይሄ ሁሉ ቀበና ውስጥ ለምን አልዋኘሁም ነው?» አለ ራሱን ሲገስፅ። የሀሳቡ እውነትነት ለልቡ ቢሰማውም፣ አገር አቁዋርጦ የመጣበትን ጊዜያዊ ደስታ ላለማበላሸት እየሞከረ።

አበራ የሄደበት ጉዳይ ከባድ መሆን አለበት። ከሄደ ፴ ደቂቃ አለፈው። ቡናውንም ማዘዙን እረስቶታል መሰለኝ አልመጣለትም። በመሀሉ ስልክ ተደወለ። በቀለ እንኩዋን ሊያነሳ አልፈለገም ነበር፣ ግን ስልኩ መጮሁን አላቆም ስላለ፣ ዝም ለማሰኘት ብቻ አነሳውና፥

«ሀሎ!» አለ።

«ታዲያስ አበራ» አለ ከስልኩ ውስጥ የሚመጣው ድምፅ። በቀለ አበራ እንዳልሆነ መናገር ፈልጎ ነበር፣ ግን ስልኩን የደወለው ሰውየ ፋታ አልሰጠው አለ።

«ለኤርትራኖቹ የሰራህላቸው የኢትዮጵያ ፓስፖርት ስህተት አለበት፤ ስለዚህ መለወጥ ይኖርበታል። ሁለት መቶ አዲስ ፓስፖርት ያስፈልገናል የስም ዝርዝርና ሌላውንም መረጃ ነገ እዚያው የተለመደው ቦታ ስንገናኝ እሰጥሀለሁ።»

በቀለ ስለደነገጠ፣ የሚመልሰውም ስላጣ ዝም እንዳለ ቀረ። በስልክ ውስጥ የሰማውን ድምፅ ግን ያውቀዋል። የተዘራ ነበር። ተዘራ ዝምታ ሲበዛበት ስለተጠራጠረ፣

«ማነህ አንተ? አበራ አይደለህም እንዴ?»

«የለም በቀለ ነኝ።» አለው። ተዘራ መሆኑን እንዳወቀ ግን አልነገረውም። ተዘራም ሌላ ቃል ሳይጨምር ስልኩን ዘጋው።

አበራ ሲመለስ፣ «ይቅርታ በቀለ፣ ካለቃየ ቢሮ ነበርኩ። ታውቀው የለ - አለቃህ ተናግሮ ሲጨርስ እንጅ አንተ ስትፈልግ ስብሰባው እንደማያልቅ።»

ቀልድም፣ ይቅርታም ድብልቅ ነበር አነጋገሩ። በቀለ ግን ለማስመሰል ቢሞክር እንኩዋን አልሳቅ አለው።

«ምነው በቀለ፣ ፬ ደቂቃ ዘግይቶ መምጣት ይህንን ያህል ያስኮርፋል እንዴ?» አለ - አሁንም ለመቀለድ እየሞከረ። በቀለ ግን እንደተኮሳተረ አይኖቹን ጨፈነና አየሩን በረጅሙ ስቦ ተነፈሰ - የበገነ ውስጣዊ ሰውነቱን ማቀዝቀዙ ይሆናል። አበራም ቀልዱን አቁሞ፣

«ምንሆንክ በቀለ፣ አመመህ እንዴ?» አለ።

«ተዘራ ደውሎ አነጋገረኝ።» አለ በቀለ «አንተ እያለህ እንዴት እሱ እዚህ አገር ይኖራል?»

«የለም በቀለ፤ ብዙ ሳትናገር በፊት ስለተዘራ የማጫውትህ ነገር አለ። ተዘራን አታውቀውም።» አለ አበራ። በቀለን ያስጨነቀው የተዘራ ስልክ መደወል እንደሆነ ካወቀ ወዲያ እንደገና ፈገግ ብሎ።

በቀለም ለመጀመሪያ ጊዜ ፈገግ አለ - አበራ ነገሩን ሲያቀለው አይቶ፣ ቀላልና ፍች ያለው እንቆቅልሽ ነው ብሎ በማመን።

ከመስሪያ ቤቱ አጠገብ፣ ወደ ተክለሀይማኖት የሚወስደው መንገድ ላይ አንድ የባህል ምግብ ቤት ነበርና፣ ተያይዘው ከዚያ ሄዱ። ምግብ ቤቱ ብዙ የመሶብ ጉዋዳዎች ነበሩት። አስተናጋጅዋም አንድ ውስጥ አስቀመጠቻቸው። ያዘዙት ምግብ እስኪመጣላቸው ደግሞ ጠጅ ቀረበላቸው። ያንን ፉት እያሉ ወሬ በሰፊው ተጀመረ።

አበራ ከበቀለ ልብ ውስጥ የሚብላላውን ነገር ስለሚያውቅ የተዘራን ጉዳይ አነሳ።

«ሴንት ሉዊስ ሆነን፣ ሻብያ በወያኔ እርዳታ ያሰበው እየተሳካለት ሲሄድ ስናይ፣ ተዘራ የሻብያ አባል እንዲሆን ወሰንን። ተዘራ የሻቢያ አበል የሆነው በኛ ውሳኔ እንጅ

በራሱ ፍላጎት አልነበረም። ተዘራ ያኔም ሆነ አሁን ንፁህ ኢትዮጵያዊ ነው። ከወያኔ የተላቀቅነው፣ አድንም ከተዘራ በምናገኘው መረጃ ነበር። አሁንም ኤርትራን ለመመለስ በምናደርገው ትግል፣ ተዘራ የሚጫወተው ሚና ወሳኝ ነው።» ብሎ ደመደመ።

በቀለም፣ «የኢትዮጵያ ፓስፖርት የሚሰጣቸውሳ ሰዎች ምንድን ናቸው?» ብሎ ጠየቀ- አበራ አጥጋቢ መልስ እንደሚሰጠው በማመን ፈገግ ብሎ።

አበራ ለጊዜው ደነገጠ። ተዘራ በስልክ ብዙ እንዳወራ ገባው። በመጨረሻም የበቀለ የዋህነት የታየው ለማስመሰል ከት ብሎ ሳቀና፣

«እነሱም ቢሆን የሚያኮሩ የውስጥ አርበኞች ናቸው። አንዳንዶቹን የምናመጣቸው የሻቢያው መንግስት ተከታትሎ ስለደረሰባቸው ነፍሳቸውን ለማዳን ብለን ነው። የተቀሩትን ደግሞ ኢትዮጵያ እንደልባቸው ለመግባት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። እነዚህ አርበኞች ኢትዮጵያዊ ካልሆኑ ማንኛችን ነን ኢትዮጵያዊ ነን ማለት የምንችል?» ነበር መልሱ።

በቀለም በጉዋደኞቹ ንፅህና ደስ ተሰኘ፤ ከጥቂት አመታት በፊትም ተዘራን ካልደበደብኩ ብሎ የተጋበዘው ትዝ ብሎት አፈረ።

ምሳ በሉና፣ ያን የማር ጠጅ እያንዶቀደቁ፣ አንዴ ሴንት ሉዊስ፣ ከዚያ አዲስ አበባ ከዚያ ደግሞ ዋሽንግቶን፣ አንዴ ፖለቲካ፣ ከዚያ ስነፅሁፍ እንደገና ሲንት ሉዊስ - እንዲሁ አንዱን ሲይዙ አንዱን ሲጥሉ አበራ ስራ የሚገባበት ሰአት ደረሰ። ተያያዙና ወደ መስሪያ ቤት ሲሄዱ፣ ብዙ በማውራታቸው ተዳክመው ይሆን፣ ሀሳብ ገብትዋቸው፣ ዝም አሉ። በቀለ እንደገና ስለተዘራ ማሰብ ጀመረ። ጉዋደኞቹን

ለማመን ከህሊናው ጋር ቢታገልም፣ ሊያስታርቃቸው ያልቻሉ አንዳንድ ጉዳዮች ከጭንቅላቱ አልወጣ አሉ።

«አሁን አበራ የነገረኝ ሚስጥር በጣም ከባድ ነው። ይህንን ያህል የአገር ሚስጥር ለመስማት ከታመንኩ፣ ሴንት ሉዊስ ሆነን እናካሂድ ነበር ያሉኝን የውስጥ አርበኝነት ለምን ደበቁኝ? ጉዋደኝነታችን ካሁን ይልቅ ያኔ ጠንካራ ነበር። እኔም ካሁኑ ይልቅ ያኔ ነበር በስራ ልረዳቸው የምችል። በዚያም ላይ ተዘራ በስህተት ካነጋገረኝ ወዲያ እንጅ ከዚያ በፊት አበራ ስለሱ አላነሳም።»

በቀለ፣ ቅድም አሜን ብሎ ተቀብሎት የነበረው የአበራ ምክንያት አልጥመው አለ። አበራም ከዝምታውና ከፊቱ መኮማተር በቀለ ምን እንደሚያስብ ለመገመት አላስቸገረውም።

«አይ በቀለ!» አለ አበራ «የማውቅህ መስሎኝ ነበር፤ ለካ አላውቅህም። ከማስብህ በላይ ተጠራጣሪ ነህና።»

«ምን አርግ ትለኛለህ አበራ፤ ነገሩ ሁሉ ግራ ሆነብኝ።»

«አታስብ በቀለ፤» አለው አበራ፣ «ዛሬ ማታ ተዘራ ቤት እወስድህና ያለፈውን ሁሉ አንስተን እንስቃለን።»

አበራ ቢሮ በራፍ ላይ ቆመው ትንሽ ካወሩ በሁዋላ፣ ከምሽቱ ፲፪ ሰአት ላይ አንበሳ ቡና ቤት ሊገናኙ ተቃጥረው አበራ ወደቢሮው ገባ። በቀለም መኪናውን አስነስቶ ቸርቸር ጎዳናን ወጣና በራስ መኮንን ድልድይ፣ ባአራት ኪሎ ዞሮ መስቀል አደባባይ ደረሰ። ጊዜ ማጥፋቱን እንጅ ወዴት እንደሚሄድ እንኩዋን አያውቀውም። ብቻ ሳምንቱን ሁሉ ያሰበበት ያደገበትን ቦታዎች እየዞረ የመመልከቱ ጉዳይ ተበሳሽበት።
«ምነው እንዲህ ተጠራጣሪ አድርጎ ፈጠረኝ?» አለ፤

ያስመራን መንገድ ተከትሎ ወደምስራቅ እየነዳ፡፡ «ምን አለ አበራ ብቻየን ከቢሮ ጥሎኝ ባይሄድ ኖሮ? የኔ ቢሮ አይደል፣ ፀሀፊ አይደለሁ፤ ምን አገባኝና ነው የሰው ስልክ ያነሳሁት?» አለና የመኪናውን መሪ በንዴት መታው፡፡

እጁን አመመው መሰለኝ፣ ከወሰደው የሀሳብ እንቅልፍ ነቃ፡፡ እንዴት እንደመጣ ትዝ አይለውም ከበስተቀኙ የእንግሊዝ ኤምባሲ፣ የሩሲያ ኤምባሲ ከዚያ ደግሞ የኮከበ-ፅባህ ትምህርት ቤት ተከታትለው አለፉ፡፡ የቀጠሮው ሰአት እየተቃረበ መጣ ቀጠሮውን ትቶ የዛሬን ቀን እንዳልነበረ ሁሉ ረስቶ ወደቤቱ ሊመለስ ፈልጎ ነበር፡፡ ግን የአበራንና የተዘራን ታሪክ መጨራሻውን ማየት ፈለገ፡፡

ለምን እንደሆን እንጃ፣ አበራ ለኢትዮጵያ ሳይሆን የሚሰራው ለኤርትራ መሆኑ ተሰማው፡፡ ተዘራ ለምን ለኤርትራ እንደሚሰራ ያውቃል፡፡ ተዘራ የሀማሴን ተወላጅ ነው፡፡ የአበራ ጉዳይ ግን አልገባው አለ፡፡

«ለገንዘብ ይሆን? አወን - ለገንዘብ መሆን አለበት፡፡» ብሎ አሰበና በሀዘን ተዋጠ፤ የፊት-በርን ቁልቁለት እየወረደ ነበር- «ከዚያ ሁሉ ስቃይ፣ ከዚያ ሁሉ ችግር ተገላገልሽ ስል አሁንም ሌቦች ተሰግስገውብሻል፡፡ 'ሰውን ማመን ቀብሮ ነው፡፡' ይላል አበሻ፡፡ እነተዘራን ማመን ግን ገሎ ነው፡፡» እንዲህ እየትብከነከነ አንበሳ ቡና ቤት ደረሰ፡፡

በቀለ ከአንበሳ ቡና ቤት ሲደርስ፣ አበራ አንድ ቡና በወተት አገባዶ ሁለተኛውን ጀምሮዋል፡፡

«ብዙ አስጠበቅኩህ መሰለኝ!» አለ በቀለ፡፡ ፊቱ ግን አበራን በማስጠበቁ ብዙም ቅር የተሰኘ አይመስልም ነበር፡፡

«የለም! አልጠበኩም፤ ፩-፲፩ ደቂቃ ቢሆነኝ ነው ከመጣሁ፡፡ ይልቅስ ተቀመጥ፣ ቡና ‥ ወይስ ሌላ ነገር ይምጣልህ፡፡»

«ምንም አልፈልግም አሁን።» አለ በቀለ፣ አሁንም ፈገግ ማለት ተስኖት።

ለወትሮው በቀለ እንኩዋንስ የድሮ ጉዋደኛውን አግኝቶ እዲሁም በሜዳ ሳቂታ ነበር። ግን ጥርጣሬ፣ ፍርሀትና ንዴት የመሳቂያ ጡንቻወቻችንን ሁሉ ይመርዝዋቸዋል መሰለኝ፣ እንኩዋንስ ከልብ ፈገግ ለማለት ይቅርና ማስመሰልም ተስኖታል።

«በል እንግዴህ ካልጠጣህ ወደ ተዘራ ቤት እንጉዋዝ፣ ከመስሪያ ቤት ደውየለት፣ በተለይ አንተን ለማየት በጉጉት ይጠብቃል።»

በቀለ መልስ አልሰጠም። ብቻ አበራን ሳይሆን የቡና መስሪያ መኪናውን ፍዝዝ ብሎ እያየ ፈገግ አለ። ፈገግታው ግን የደስታም፣ የይስሙላም አልነበረም - የ'ቱሪስት ብላ' አይነት እንጅ። አበራ እስካሁን ለመቀለድ፣ ለመሳቅ፣ እንደድሮው ሁሉ ለመጫወት ይሞክር ነበር። አሁን ግን የሱም የመሳቂታ ጡንቻዎች መታዘዛቸውን አቆሙ።

በቀለና አበራ ተያይዘው በአበራ መኪና ወደተዘራ ቤት ጉዞ ቀጠሉ። በቀለ አሁንም ሀሳቡን ቀይሮ ሊቀር ፈልጎ ነበር፣ ግን የአበራና የተዘራን ጉዳይ መጨረሻውን ማየት ፈለገ። እንደሚያመሽ ለቤት ተናግሮ ስለወጣ ብዙም አላሳሰበውም። በቀለ መኪናው ወደ ፖፖላሬ የሚሄድ መስሎት ነበር።
«ፖፖ-ላሬ አለ ጣልያን።» ብሎ በልቡ አሰበ። «የጣልያን ነብይ እንኩዋን አይተን አናውቅም፣ ፖፖላሬን የሰየመው ጣልያን ግን ነቢይ መሆን አለበት።»

ነገር ግን ሜክሲኮ አደባባይ ሲደርሱ ወደዚያ መታጠፋቸው ቀረና ወደ ድሮው አይሮፕላን ማረፊያ ጉዞ ቀጠሉ። አይሮፕላን ማረፊያውን ካለፉ በሁዋላ በቀለ የማያውቀው ሰፊ መንገድ ላይ ወደቀኝ ታጠፉ።

«ወደ ሆለታ የሚሄድ መንገድ ነው።» አለው አበራ፣ በቀለ ግራ እንደተጋባ ከፊቱ አንብቦ።

«ተዘራ እዚህ ነው የሚኖረው?» አለ - መንገዳቸውን ከጀመሩ ለመጀመሪያ ጊዜ መነጋገራቸው ነበር።

«አወን። ሆለታ አካባቢ ነው የሚኖረው። እንደድሮው እንዳይመስልህ አሁን ሆለታ አዲስ አበባ ከተማ ክልል ውስ ሊገባ ትንሽ ነው የቀረው።»

[1]ውነትም በወያኔ ጊዜ ከየባላገሩ በሰብ አስባቡ የተባረረው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ቤት የሰራው በዚያ መንገድ አካባቢ ስለነበረ እስከሆለታ ድረስ መረፌ ቢጥሉ መሬት አይወድቅም። በመጨረሻ ሆለታ ለመድረስ ፬ ኪሎ-ሜትር ሲቀራቸው ወደ ግራ የሚወስድ የአሸዋ መንገድ ላይ ታጠፉ። ጥቂት እንደተጉዋዙ የቤቶቹ ቁጥር እየሳሳ ከተማው ወደእርሻ እየተለወጠ መጣ። ጊዜው ነሀሴ ነበርና አዲስ የበቀለው ጤፍና ስንዴ የምሽት ፀሀይ አርፎበት አረንጉዋዴ ባህር መስልዋል። «እግዚአብሄር ይይልህ መንግስቱ።» አለ በቀለ ሳያውቀው ጮክ ብሎ። በቀለ አሜሪካ የመጣው፣ እርሻ ተምሮ ተመልሶ ያባቱን መሬት ሊያርስ ነበር።

ከዚያ የወይን እርሻ ጀመረ። አካባቢው ድሮም ወይን እንደሚመረትበት በቀለ ያውቅ ነበር፣ ይሄ ግን ሰፊና ዘመናው እርሻ ይመስላል። ከዚያ ደግሞ የወተት ላሞች የሚግጡበት በሽቦ የታጠረ ሜዳ መታየት ጀመረ። ወይኑም ላሞቹም ያንድ ሰው ወይም ያንድ ድርጅት ይመስላሉ። በመጨረሻም ከሩቅ የባህርዛፍ የሞላበት ኮረብታ መታየት ጀመረ። የአሸዋው መንገድ ከዚያ ጫካ ውስጥ ገብቶ የሚቆም ይመስላ። እውነትም ከጫካው ውስጥ ሲገቡ ሰፊ ግቢና በድንጋይ የተሰራ ባለአንድ ፎቅ ቤት አገኙ። ከቤቱ ፊት ለፊት አንድ መኪና ቆማለች፣ ሁለት የሚናከሱ ውሾች

ግቢ ውስጥ ይሮጣሉ፡፡ ውሾቹ የነአበራን መምጣት ሲመለከቱ ጆሮአቸውን ቀስረው ቆሙ፡፡ በቀለ የተዘራ ቤት ይሄ እንደሆነ ገባው፡፡ «አይ ኢትዮጵያ!» አለ በልቡ፡፡ «ጠላትሽን የምታሳድጊ፣ ጠላትሽን የምታስተምሪ፣ ጠላትሽን የምታከብሪ አገር!»

«በቀለ ከመኪና አትውረድ፤ ውሾቹ እኔን ስለሚያውቁኝ ወርጄ ልያዝልህ፡፡» አለ አበራ - የቤቱ በራፍ እንዲከፈትለት የመኪናውን ጥሩምባ እየነፋ፡፡

ከቤት ሲገቡ ተዘራ ተንደርድሮ መጥቶ በቀለን ሳመው፡፡ የመሳሳሙ ስነስርአት የተፈፀመው ግን የበቀለ እጆች ወደመሬት እንደተንዘረፈፉ ነበር፡፡ ተዘራም ነገሩ ስለገባው በሰፊው የገለጠጠው ጥርሱን ደመና እንደደረሰባት ፀሀይ አጠፋው፡፡ ተዘራ እንዲቀመጡ ጋበዛቸውና ተቀመጡ፡፡ የሚጠጣም አቀረበላቸው፤ በቀለ ግን ከገባ ጀምሮ አንድም ነገር አልቀመሰም፡፡ «ታሪካችሁን ንገሩኝና ወደ ቤቴ ልሂድበት፡፡» የሚል ይመስላል፡፡

ተዘራ ተነስቶ ወደ ጉዋዳ ገባ፡፡ አስተያየቱ አበራ እንዲከተለው የፈለገ ይመስላል፡፡ አበራም ስለገባው ተከትሎት ገባ፡፡ በቀለ ብቻውን ከዚያ ትልቅ ቤት ቀረ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰውነቱን ከበደው፡፡ ንዴቱም ወደ ፍርሀት ተለወጠ፡፡ አበራና ተዘራ ሲጨቃጨቁ ይሰማዋል፡፡ ምን እንደሚያወሩ ግን ማወቅ አልቻለም፡፡ ተነሳና እነሱ በገቡበት በር ገባ፤ ወጥቤቱ ነው፡፡ የወጥ ቤቱ የጉዋሮ በር ወደ ትልቅ በረንዳ ይመራል፡፡ እነተዘራ ግን ከዚያም የሉም፡፡ ከበረንዳው ወርደው ከሜዳው ላይ ቆመው ይጨቃጠቃሉ፡፡ የበረንዳው መብራት ስለበራ ቁልጭ ብለው ይታዩታል፡፡ የወጥ ቤቱ ግን ጨለማ ነበርና እሱን የሚያየው አልነበረም፡፡ አበራና ተዘራ በትግርኛ ነበር የሚያወሩት፡፡ በቀለ ጆሮውን ማመን አቃተው፡፡ ሴንት ሉዊስ ተኝቶ የሚያየው ህልም እንጅ እውነት አልመስለው አለ፡፡ እንዲያውም አንዳንዴ መጥፎ

ህልም ሲያይ እንደሚያደርገው ሁሉ ከእንቅልፉ ለመንቃት ሞከረ። ግን አልተሳካም። ለካስ አበራም የሀማሴን ሰው ኖርዋል።

የሚጨቃጨቁት በትግርኛ ብቻ አልነበረም፤ አንዳንዴ እንግሊዘኛ አንዳንዴም አማርኛ ይቀላቅላሉ።

«የምናደርገው ገብቶታል፤ ለፖሊስ ቢያመለክትስ?» አለ ተዘራ።

«ማን ያምነዋል ብለህ ነው - ስቀው ያባርሩታል።»

«ግን አሜሪካ ከተመለሰ በሁዋላ ለሰው ሁሉ ስለሚያወራው ከባለስልጣን ጆሮ መድረሱ አይቀርም። የኢትዮጵያ መንግስት ባይዘን፣ የኛወቹ ይገድሉናል።»

«ምን እናርግ ታዲያ?»

«ምንም ምርጫ የለንም። ነፍሳችንን ለማዳን ስለሆነ፣ በቀለን ዛሬውኑ ማስወገድ ይኖርብናል።»

በቀለ ቀስ ብሎ ወደሁዋላው ተመልሶ በዋናው በር ከቤቱ ወጣ። የአበራም የተዘራም መኪናዎች ተቆልፈዋል። ያለው ምርጫ በእግሩ መሮጥ ብቻ ነበር። ከግቢው ወጥቶ መንገዱን ይዞ የበላ የጠጣውን ሮጠ። ግን ኩዋስ ከተጫወተ ወይም ከሮጠ ብዙ ጊዜው ነበርና ልቡ ሊፈርስ ደረሰ። ማረፍ አሰኝቶት ነበር። የነፍስ ጉዳይ ነውና ሩጫውን ትቶ በፍጥነት መራመድ ጀመረ። በቀለ የፈራው ውሾቹን ነበር። ግን ቀደም ሲል ለሱው ሲባል ታስረው ነበርና ሊከተሉት አልቻሉም። በቀለ ከግቢ ወጥቶ ሲሮጥ ውሾቹ ጮኸው ነበር። ግን በሆነ ባልሆነው ስለሚጮሁ እነተዘራ የበቀለን መጥፋት አልጠረጠሩም። በመጨረሻም ጭቅጭቃቸውን ጨርሰው፣ በቀለን ገድለው ከወይኑ እርሻ ዳር ለመቅበር

ተስማተው ከቤት ሲገቡ በቀለን አጡት። መታጠቢያ ቤት ይሆናል ብለው ከዚያ ቢመለከቱም የለም።

አበራም «በቀለ! የት ሄድክ።» ብሎ ተጣራ።

«ሀድጊ!» አለ ተዘራ፣ አበራን ሲሳደብ። አበራ በናቱ በኩል ትንሽ አማራነት ነበረበትና። «ከኔ ጋር ስትጨቃጨቅ ነው ጥሎ የጠፋው። ይልቅስ ውሾቹን ልቀቃቸው። እነሱ ይደርሱበታል። እኛ በመኪና እንከተላቸዋለን።»

አበራ ውሾቹን ፈታቸው። እነሱም እየጮሁ መንገዱን ተከትለው በረሩ።

በቀለ የላሞቹን እርሻ ጨርሶ የወይኑን አጋምስዋል። የውሾቹ ጩኸት ስለተሰማው እነተዘራ እንደተከተሉት አወቀ። የሚከላከልበት መሳሪያ አልነበረውም። «ዋ! ልጆቼን ጥየ የውሻ እራት ሆኜ መቅረቴ ነው? » ብሎ አሰበ።

ጨረቃ ሙሉ አልነበረችም፣ ግን ብርሀንዋ አካባቢውን ለመለየት ያስችል ነበር። ውሾቹ እየገሰጉ ሲመጡ ታዩት። የሚሸሸበት ቦታ አልነበረውምና፣ ያጥሩን እንጨት ገንጥሎ ይዞ፣ የሞት ሞቱን ቆሞ ጠበቃቸው። የመጀመሪያው ውሻ እንደሮጠ ዘሎ ወደ በቀለ ተወረወረ። እንደ ቤዝ-ቦል ተጫዋች ሁሉ ዱላውን አስተካክሎ ጠበቀውና ግንባሩን ተረተው። አንድ የሲቃ ድምፅ ብቻ ነበር ያሰማው - ውሻው ከእግሩ ስር ወደቀ። ሁለተኛው ውሻ የጉዋደኛውን መሞት አይቶ ይሆን ወይም የበቀለን ዱላ፣ ትንሽ ራቅ ብሎ ቆመና የፊት እግሮቹን አንፈራጠ፣ የላይና የታች ከንፈሮቹን ገልጦ፣ ያንኮራፋ ጀመር። ደግነቱ በጨረቃ አይታይም እንጅ፤ እነዛ የተሳሉ ጥርሶችና ከከንፈሩ ጥግ የሚንጠባጠበው ለሀጭ ብቻ ሰውን በፍርሀት ለማንቀጥቀጥ በቂ ነበሩ። በቀለ ግን አሁንም ያለፍርሀት ዱላውን ይዞ ውሻውን ተጠጋው። ውሻውም ማንኮራፋቱን ትቶ፣

ጭራውን በእግሮቹ ስር ቆልፎ የፍርሀት ድምፅ እያሰማ ወደ ሁዋላው ሸሸ።

በቀለም ዱላውን አሽቀንጥሮ ወረወረና ዋናውን መገድ ተከትሎ ሩጫውን ቀጠለ። ዋናው መንገድ ለመድረስ ግን ቢያንስ የ ፭ ደቂቃ መንገድ ይቀረዋል - ያውም ከሮጠ። ትንሽ እንደሮጠ የመኪና መብራት ታየው። መንገዱን ተከትሎ ከመሮጥ በቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም። ቆየት ብሎ ደግሞ የግጭት ድምፅ ተሰማው።

«ከአጥር ወይም ከድንጋይ ጋር ተጋጭተው ይሆን?» ብሎ አሰበ።

ዞሮ ለማየት ግን አንገቱ አልታዘዝ አለው። ሩጫውን አቁምዋል። ጨረቃዋም፣ መንገዱም የመኪናውም መብራት አልታይ አሉት። የራሱም ሰውነት ያለበትን ማወቅ ተሳነው። አእምሮው የሚያስበው እየጠፋ እየደበዘዘ ሄደ። ነገሩ ገባውና፣ «ወይኔ በቀለ! ተበላሸሁ።» አለ። በአይነ ህሊናው ይታየው የነበረውም ብርሀን፣ ከመደብዘዝ ወደ ጨለማነት፣ ከጨለማነት ደግሞ ወደ ምንምነት ተቀየረ።

ካፍኳትዋ

ሠትሮም ጥዋት ነበር፣ ከእንቅልፌ የምነቃው። ዛሬም እንደልማዴ ከንጋቱ በ ፲፪ ሰአት ተነሳሁና ቴሌቪዥኔን ከፈትኩ። ቀኑ እሁድ፣ ሀምሌ ፳፰ ፲፱፻፺፮ አ.እ ሲሆን፣ ዘመኑ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ስለአገሩ መጥፎ እንጅ ጥሩ መስማት ያልቻለበት፣ እንባው በቁጭትና በሀዘን የሚፈስበት ነበር። ዛሬ ግን የተለየ ቀን ነው፤ ያበሻ እንባ የደስታው ምልክት ይሆናልና።

የቴሌቪዥኑ ተናጋሪዎች በስነፍጥረታዊ ጥናት በተደገፈ የአርዋርዋጥ ዘዴ በመጠቀም ድል ለማድረግ ከፊት ፈንጠር ብላ የምትታየውን ጀርመናዊት ያደንቃሉ። ብዙም ሳይርቁ የጃፓንዋ፣ የሩሲያዋ፣ የፖርቱጋልዋ ሩዋጭና ፋጡማ ሮባ ይከተልዋታል። መቅረፀ-ብርሀኑ (Camera) የሌሎቹን እንጅ የፋጡማን ፊት ብዙም አያሳየንም። «የጀርመንዋ 'ርዋጭ» አለ የኤን-ቢ-ሴው (NBC) አቀንቃኝ «እስከ ፲ ማይል ድረስ ቅድሚያዋን ቀስ-በቀስ በማካበት የሚከተላትን ቡድን በ ፭ ደቂቃ ትቀድመዋለች። ከዚያም የአትላንታ ፀሀይ እየበረታ ስለሚሄድ ሌሎቹ ርዋጮች ይዳከማሉና ሊደርሱባት አይችሉም። ይህ ከአሰልጣኝዋ ጋር ሆነው የወሰኑት ረቂቅ ብልሀት የሚሰራ ይመስለኛል።» አለ። ጀርመንዋ እነፋጡማን በ ፵፭ ሴኮንድ ቀደመቻቸው። አቀንቃኙም «ይሄውና!» አለ፣ የግምቱን ትክክለኛነት በኩራት ሲገልፅ።

የአየሩን ሙቀት የሚቆጣጠረው አላህ እንጅ ፈረንጆች አልነበሩምና፣ የአትላንታን ሙቀት የሚበርዝ ቀዝቃዛ ነፋስ ነፈሰ። ጀርመንዋን የሚከተላት ቡድን ቀደማት፣ ብዙም ሳይቆይ ፋጡማ ቡድኑን ቀድማ የብቸኛ ቡድን ፈጠረች። ታላቅዋም ጀርመን የገባችበት ጠፋ። ሆነም ቀረም የፋጡማ

ተቀናቃኞች ሩሲያና ጃፓን ሆኑ። ፋጡማ እንደ ጀርመንዋ ሁሉ ይደክማታል የሚል መላ-ምት ተጠነሰሰ፣ ግን ያም እንደጀርመኖቹ ጥበብ ሁሉ ፎረሸ። ፋጡማ የሚከተልዋትን ሩዋጮች በአንድ ደቂቃ ቀደመቻቸው። ይህም ልዩነት እየሰፋ እንጅ እየጠበበ እንደማይመጣ ታወቀ። እንዲያም ሆኖ የወርቁ ሜዳሊያ ጉዳይ አከተመ። መቅረፀ-ብርሀኑ ፋጡማን ብቻ ሳይሆን ታላቁን አበበ ቢቂላን መመልከት ጀመረ። ከፊቱ የቆመችውን የፋጡማን ፊት አቅርቦ ለማሳየት የተጀነነውን ያህል፣ ከሞት ባሻገር ያለውን አበበን፣ ከኢሀደግ ወህኒ የሚሰቃየውን ማሞ ወልዴን ለማየት አይነ-ጥላው ተገፈፈለት።

ተናጋሪዎቹ ስለኢትዮጵያ የሚያውቁት እምብዛም ስለነበረ መዋሸት ጀመሩ። «ኢትዮጵያውያን» አለ አንዱ፣ «ኢትዮጵያውያን፣ ያሜሪካ ልጆች የቤዝቦልን እስታቲስቲክ በቃላቸው እንደሚወርዱት ሁሉ፣ የረጅም ሩጫን ሬኮርዶች ያንበለብሉታል።» ሌላው ቀበል አደረገና «የሚሰለጥኑበት ሁኔታ ከባድ ስለሆነ የአትላንታውን ማራቶን እንደጨዋታ ነው የሚመመለቱት።» አለ። የመጀመሪያው ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን የሚሰለጥኑበት ሁኔታ ምስጢራዊ መሆኑን አስረዳ። ድል ይሉአችሁዋል እንዲህ ነው . . ነጮች የበታችነታቸውን ለማስረዳት ምክንያት መፍጠር ሲኖርባቸው።

ፋጡማ ሩጫውን ከጀመረች አንስቶ ስትስቅ አላየሁዋትም። ሆኖም የሀዘን፣ የጭንቀት ወይም የመድከም መልክ አይታይባትም። አንዳንዴ ውሀ የተነከረ እስፖንጅ ታነሳና ከንፈሮችዋን አርሳ ትጥለዋለች። ከዚያ ውጭ ግን በልብዋ ሌላ ነገር የምታስብ ትመስላለች። አልፎ አልፎ ዞር ብላ የሚከተልዋት እንዳሉ ትመለከታለች፣ እንዲያ የምታደርገው ከሀሳብዋ ስትነቃ ይሆናል። ምን እያሰበች እንደምትሮጥ ባውቅ እንዴት ደስ ባለኝ።

የኦሎምፒኩ ጨዋታ ከተፈፀመ በሁዋላ የአትላንታ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን፣ እስፖርተኞቹን አስተናግደው ነበር። የአትላንታውም ከንቲባ ቀኑን «የኢትዮጵያውያን እስፖርተኞች ቀን» ብለው ሰይመውታል። ባውቅ ኖሮ፣ አትላንታ ሄጄ ስትሮጥ ምን እያሰበች እንደምትሮጥ እጠይቃት ነበር · · ፊርማዋን በወረቀት ለማስቀረት የሚሻሙትን ህፃናት፣ አብረዋት ፎቶ ለመነሳት የሚጋፉትን ኢትዮጵያውያን ማለፍ ከቻልኩ ማለቴ ነው።

መንገዱ የጃፓን በንዲራ በያዙ ሰዎች ተሞልትዋል፣ ጃፓኖቹ የራሳቸው ልጅ ወደሁዋላ ብትቀርም ፋጡማን ከማበረታታት አልተቆጠቡም። ወደሁዋላ ብትዞርም የሚታይ ነገር አልነበርምና ፋጡማ መገላመጡን ካቆመች ቆይታለች። «እንደአገርዋ እንደኢትዮጵያ ሁሉ ብቻዋን ቀርታለች።» ብየ አሰብኩ። ይህንን አይነት ስሜት እኔ ብቻ ሳልሆን ሌሎችም እንደተሰማቸው እርግጠኛ ነኝ። ከሁለት ቀናት በሁዋላ፣ አቶ ታደለ ገብረ ህይወት ስሜታቸውን ሲገልፁ «ፋጡማ እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ ብቻዋን ቀረች» ብለው የፃፉትን አንብቤ ገረመኝ።

ከዋናው ሜዳ ለመድረስ ፫ ማይል ሲቀራት ከመንገዱ ዳር የቆሙ የኢትዮጵያን በንዲራ የሚያውለበልቡ ሰዎች አየች። ለመጀሪያ ጊዜ ፈገግ ስትል አየሁዋት። አይኖቼም እንባ መቁዋጠር ጀመሩ። ግን ታግየ ከመውረድ አቆምኩዋቸው። እስታዲየሙ ከሩቅ መታየት ጀመረ። የሩጫው ማብቂያ እየተቃረበ ሲሄድ የኢትዮጵያውያንም ቁጥር በዚያው መጠን ጨመረ። ፋጡማ ኢትዮጵያዊ ባየች ቁጥር ትስቅ ጀመር። መሳቅ ብቻ አይደለም እጅዋንም ታርገበግብላቸው ነበር። አንዳንዴማ ቆማ ልታነጋግራቸው የፈለገች ይመስላል። ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ሌላ የኢትዮጵያ በንዲራ አየች። በንዲራውን ተጠግታ ዳሰሰችውና ሳመችው። እኒያ በግድ የተያዙ እንባወቼም ፈነዱ።

የዚያን ቀን ሴንት ሉዊስ የሚባል ከተማ መሄድ ነበረብኝ። እንደመረቀንኩ መኪናየን አስነስቼ ጉዞ ጀመርኩ። ከቤቴ ብዙም ሳልርቅ አንድ ሴት ስትሮጥ አየሁና ለብቻየ ከት ብየ ሳቅሁ። «ተሮጠና ተሞተ» አልኩ በልቤ። የጠለላን ዘፈን ትንሽ ልለውጠውና፦

«አይን የተፈጠረው ሁሉን ለማየት ነው፣
አንችን አይቶ ሌላ አላይ አለ ምነው?»

የሚለው ግጥም ትርጉሙ የገባኝ ያን ለት ነበር። ፋጡማን ባየሁበት አይኔ ሌላ ሰው ሲሮጥ ማየት አልፈለግሁም። በጭንቅላቴ የቀረፅኩት ስእል ይበላሽብኛል የሚል ፍራቻ ሳይዘኝ አልቀረም። ቁርሴን አልበላሁም ነበርና ከአንድ የከባድ መኪና ሹፌሮች ምግብ ቤት አቆምኩ። መኪና የሚቆምበትን ሜዳ አቁዋርጬ ወደ ምግብ ቤቱ ስሄድ፣ አረማመዴ ከወትሮው ለየት ማለቱ ተሰማኝ። ትከሻየ እንደ አካል ገንቢወች ሁሉ በሰፊው ተለጥጥዋል። ኩታ አልያዝኩም እንጅ አፍንጫየ ላይ ጣል ሳላደርገው አልቀርም ነበር። አረማመዴ በዝግታና በጥንቃቄ ነበር። «የፀሀይ ነገስታት (Kings of the sun)» የሚለውን ሲኒማ አይታችሁት ከሆነ፣ አረማመዴ የዩል-ብሪነርን (Yul Brynner) አረማመድ ቁርጥ። የሚያዩኝ ሰወች ሁሉ፣ አገሬ ከፋጡማ ሮባ ጋር አንድ መሆኑን የሚያውቁ መሰለኝ። ለካስ ኩራትም ሆነ ሀፍረት ሌሎች ስለኛ የሚያስቡት ሳይሆን ራሳችንን የምንመለከትበት የህሊና መስተዋት ነው።

ረጅም መንገድ በመኪና መጉዋዝ እወዳለሁ። ለኔ ስሜቴን ወደ ቃላት የምለውጥበት ጊዜ ነው። ከቀረፅኩዋቸው የአእምሮ ስእሎች ተደጋግሞ የሚታየኝ፣ ፋጡማ በንዲራውን ዳስሳ የምትስመው ነበር። ስእሉ ሲጀምር አይናቹ እንባ ያቀራሉ፣ እጅዋን ስትስም የቀረፅኩት ስእል ሲታየኝ ደግሞ የተቁዋጠሩት እንባወቼ ይፈሳሉ። ይህ ስእል እየተደጋገመ ስለታየኝ ከስሜትነት «የኛ ይትዋ» ወደተሰኘ ግጥምነት ተለወጠ። የኛ ይትዋ ይሄው፦

የመንገዱን ጠርዝ ተጠግታ፣
እጇን በረጅሙ ዘርግታ፣
ዳሰሰችው በንዲራውን፣
የ'ናት ያባትዋን አለኝታ።
ከዚያም፣
ሳመቻቸው ጣቶችዋን፣
ፈገግታ ባዋባቸው ከንፈሮችዋ፣
ፋጡማ ሮባ፣
የኛ ልጅ የኛይትዋ።
አውቃዋለች ድሉ፣
እንደሆነ የስዋ፣
እንደቀረች ብቻዋን፣
ከሀገርዋ፣
ከበንዲራዋ ጋር ከወገንዋ፤
አውቃዋለች።

እኔም አውቄያለሁ፣
እንደቀረሁ ለብቻየ፣
ከፋጡማ ጋር፣
ከ'ንባየ።

የመጀመሪያ ሚሞሯ

የ ሚከተሉት አራት ግጥሞች የተፃፉት ለፓፓኋኋቱ የኢትዮጵያውያን ስብሰባ ሎስ አንጀለስ የሄድኩ ጊዜ ነበር። ከሎስ አንጀለስ ይልቅ ያጉዋጉዋኝ የአሜሪካን በረሀዎች በመኪና ለማቁዋረጥ ያወጣሁት እቅድ ነበር። ሆኖም ከሚዙሪ እስከ ሎስ አንጀለስ በመኪና ለመሄድ ያደረግሁት ዝግጅት በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሳካ ቀረና እስከ ላስ ቬጋስ በደያራ (አውሮብላ ማለቱ እኮ ነው!) መጉዋዝ ነበረብኝ። እቅዴ፣ በመጀመሪያ ግራንድ-ካንዮን እየተባለ የሚጠራውን ገደል ለማየት ነበርና ከድሬ-ደያራው (ይሄ ደሞ ምን መሆኑ ነው? ያየር ሜዳ?) እንደደረስኩ መኪና ፍለጋ ወደ አቪስ (AVIS) መንገድ ቀጠልኩ። ሆኖም፣ የላስ ቬጋስ አድባር እንድትቀበለኝ ብሬን ከትቼ የቁማሩን መጫዎቻ እጀታ የሳብኩት፣ ሻንጣየን እንኩዋን ሳልረከብ በፊት ነበር። የዛሬ ሀያ አምስት አመት አካባቢ፣ አዲስ አበባ የትም ቡና ቤት ብትገቡ የቁማር መኪና ከበራፉ አጠገብ ታገኙ ነበር። ላስ ቬጋስ እንደዚያ ነው። ድሬ-ደያራው፣ ቤንዚን ቤቱ፣ የምግብ ሱቁ፣ ሆቴሉ፣ ቁማር ብቻ ነው። ከተማው ቁማር፣ መንገዱ ቁማር፣ ባላገሩ ቁማር፣ ቁማር፣ ቁማር፣ ቁማር . . . .

አውራ ጎዳና ፮፫ን ወደ ደቡብ ይዛችሁ ከሄዳችሁ፣ መጀመሪያ የሁቨርን ግድብ ከዚያ ደግሞ አውራ ጎዳና ፵ን ታገኛላችሁ። ያ ደግሞ ወደ ግራንድ ካንዮን ያዘልቃችሁዋል። አውራ ጎዳና ፵ ከታወቀው ሩት-፷፮ ከሚባለው የድሮ መንገድ ጋር አንድ የሚሆንበት ቦታ ብዙ ነው። ስለዚህ አውራ ጎዳና ፵ የሩት-፷፮ ወራሽ ነው ሊባል ይገባዋል። እርግጥ የሩት-፷፮ ልጆች ብዙ ናቸው። አክላሆማ ስትደርሱ አውራ ጎዳና ፵፩፣ ሴንት ሉዊስ ስትገቡ ደግሞ ፶፭፣ እነዚህም የሩት-፷፮ ምትክ ናቸው።
የሁቨር ግድብ በስእል እንዳየሁት ትልቅ አልሆነብኝም።

ግን ግድቡን መሻገር ስጀምር፣ ለገንቢዎቹ መታሰቢያ እንዲሆን የቆመ ሀውልት በስተግራየ አየሁ። የመላእክቱ ፊት የገንቢዎቹ ኩራት ይነበብበታል። «የዛሬን አያድርገውና፣ እኛም ኩሩ ነበርን።» አሰኘኝ። ከዚያም የፀጋየ ገብረ መድህን ኦቴሎ ትዝ አለኝ።

> *ነበርን ማለት ክንቱ ነው፣ እኛም ባገራችን ሰው ነበርን፣ ያውም ክባሳባት ዘር በመወለዳችን፣ የተከበርን።*

ጀኖን ይገር ስጉዋዝ፣ እጅግ ድንጋይ የበዛበት፣ ለምለም ነገር ለመሀላ የማይታይበት፣ አፈሩ የተጋለጠ ድንጋዩ ያገጠጠ፣ እንኩዋን ሰው አውሬ ይኖራል ተብሎ የማይገመትበት አገር ገባሁ። አሜሪካ ከመጣሁ፣ ሳር ያልለበሰ የተጋለጠ አፈር በሰፊው ሳይ የመጀመሪያየ ነበር። የሚገርመው ግን፣ በዚህ የገሀነም አምሳያ ሰዎች መኖራቸው ሳይሆን፣ የሚቆፍሩትን ቆፍረው፣ የሚገነቡትን ገንብተው፣ ካብዛኛው የአለም ህዝብ የተሻለ ኑሮ መኖራቸው ነው። የኛማ ነገር አይነሳ። ያን የመሰለ አፈር ይዘን የምንራብ፣ አገር ጠርጎ የሚሄድ ክረምት እያለን የምንጠማ፣ ሀብታም ሆነን ለድህነት፣ አዋቂ ሆነን ለድንቁርና የተጋለጥን ፍጡሮች።

ከሌሎች ጋር እኩል መሆን የምንፈልገው፣ ሰርተን በማደግ ሳይሆን ሌሎች የሰሩትን በማጥፋት ነው። ከሌሎች የምንበልጠው ደግሞ እንዲሁ ሌሎች የሰሩትን በመቀማት ነው። መሰለን እንጅ፣ የሌሎችን መቀማት ሁላችንንም ያደኸየናል እንጅ አያሳድገንም።

በደርግ ዘመን፣ ከሆለታ የሚገኝ የአንድ ሆቴል ሰራተኞች፣ ባለቤቱ አድሀሪ ነው በማለት ሰውየው እድሜውን በሙሉ የለፋበትን፣ እነሱም ተቀጥረው የእለት እንጀራቸውን የሚያገኙበትን ሆቴል ወረሱት። መጠጡ ወረደ ተጠጣ። እህሉ ከጉዋዳ ወጣ ተበላ። አልጋው ተተኛበት፤ አንሶላው አረጀ፣ ተቀደደ። የቡና መኪናው ተሰበረ፣ የቤቱ አምፖል

ተቃጥሎ አለቀ። በምን ገንዘብ ይተካ? ከሸጡት እነሱው የጠጡት፣ እነሱው የበሉት ይበዛል። በመጨረሻም ሆቴሉ ተዘጋ። ሰራተኞቹም አንዱን ማሳ በልቶ እንጨረሰ አንበጣ ሁሉ ወደሚቀጥለው ተሻገሩ። ስንት ማሳ ወረሩ! የስንቱን ሰብል አበላሹ!

ይኸው የኛው ጉድ እየከነከነኝ አንዳንዴም የሁቨር ግድብ መላእክት እየታዩኝ አውራ ጎዳና ፵ ደረስኩ። ሰአቱ ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ሆንዋል። ግራንድ ካንዮን ደርሶ ለመመለስ ደግሞ ከ፬፻ ማይል በላይ መንዳት ይኖርብኛል። በበነጋው ሎስ አንጀለስ አንዳንድ ስብሰባዎች ላይ ላዳምጣቸው የምፈልግ ተናጋሪዎች ስለነበሩ የግራንድ ካንዮኑን ነገር በይደር ያዝኩና ፈረሴን ወደ ላስቬጋስ ጠመዘዝኩ። አሁንም በነዚያ የሁቨር ግድብ መላእክቶችጋ ስላለፍኩ ፊታቸውን በድጋሜ አየሁት። እንደበፊቱ ሁሉ ስራቸው ስራየ፣ ኩራታቸውም ኩራቴ እንዳልሆነ ተሰማኝ። ከአንድ ሳምንት በሁዋላ ለሶስተኛ ጊዜ እነዚህኑ መላእክት አያቸዋለሁ። ከመኪናየ ወርጄም ከመሀላቸው የተፃፈውን ሰሌዳ አነበዋለሁ። ከዚያም፣ እንደፈቃደ አዘዘ* ሁሉ እጮሀለሁ።

ጋዳሚት ሰነባቢች

በስተግራ፣
    የሁቨርን ግድብ ስታልፉ፣
ከላስ ቬጋስ ወደታች፣
    አዘቅዝቃችሁ ስትወርዱ፣
የግድቡን ገንቢዎች፣
    የመንፈስ ኩራት የሚገልፁ፣
ሁለት መላእክት ታያላችሁ፣
    ክንፋቸውን ወደሰማይ የዘረጉ።
ከመላእክቱ መሀል ያለው ሰሌዳ፣

* (ጩኸት - የፈቃደ አዘዘ የመጀመሪው የግጥም መፅሀፍ ነው)

ይላል፣ «ይህ በንዲራ፣
ከዚህ መሰቀሉ፣
ከዚህ መውለብለቡ፣
ምስክር ነው ለነዚያ፣
ምንም ከሌለው ምድር፣
ፍሬያማ ዛፍ ለሚያበቅሉ።።»

ሲያዝን ሲበሳጭ፣ እንዳሁኑ እንደኔ።።
«ጋዳሚት» ይል ነበር «ሰነባቢች» አጎቴ፣
እኔም «ጋዳሚት!» አልኩ «ሰነባቢች»
የሰው ስራ ማድነቅ ብቻ፣ ሆነብኝና ህይወቴ።።

የዚያን ቀን ማታ፣ ቴሌቪዥኑ ሁሉ የሚያወራው ስለ ሆንግ ኮንግ ለቻይና መመለስ ነበር።። «እኛስ ጅቡቲን ለ፮፬ አመታት አልነበረም እንዴ ያኮናተርነው? ምነው የኛ አልተመለሰልን?» ብየ ጠየቅሁ ራሴን ۔ ۔ መልሱን እንደማያውቅ ሁሉ።። ሌላ ጥያቄ ሌላ ጨኸት።።

ተመልከቱ

ምንኛ ውብ ነው፣
ሀያል መሆን፣ እውነትን መደንገግ፣
ከዚያም፣
እውነተኛውን መሾም፣ መሸለም፣
አባዩን መቆጣት፣
ቀጣፊውን መግረፍ፣ መቅጣት፣
ወይም እስከናካቴው መግደል፣
አንሰራርቶ፣ ጎልብቶ፣ በተራው
«እውነት የኔ ናት» እንዳይል።።
ምንኛ ውብ ነው ሀያል መሆን፣
ውበት ራስዋን መደንገግ፣
ቆንጆውን ማሞካሸት፣
የበላይነቱን ማሳመን፣
መልከ ጥፉን፣ ማኩዋሰስ፣

ከሰው ማህበር መገለል።።

ምንኛ ውብ ነው ጉልበት፣
የእውነት ሁሉ መሰረት፤
ምንኛ ውብ ነው።።

እንዲያ አይደለም የሚሉ ካሉ፣
ሀቁ፤
«አቦ ተውን!» በልዋቸው፣ «አትደብሩን፣
ይልቅስ ተመልከቱ ጅቡቲን፣
ተመልከቱ አስመራን፣
ተመልከቱ ሆንግ ኮንግን፣
ተመልከቱ።።

በልዋቸው ተመልከቱ፣
የጥንካሬን ውጤት፣
የሀያልነትን በረከት፣
ታላቂትዋን ቺና፣
ተመልከቱ።።

በበነጋው፣ ለማኝ ምን ሳይል ነው 'ሚባለው? ተነስቼ ወደ ሎስ አንጀለስ ጉዞ ቀጠልኩ።። ደግነቱ በረሀዎች ሌሊት ስለሚቀዘቅዙ ሙቀቱ እንደፈራሁት አልነበረም።። ወደ ሎስ አንጀለስ እየተቃረባችሁ ስትሄዱ የዛፉ ቁጥር እየጨመረ፣ ድንጋዩ ለዛፍ ቦታ እየለቀቀ ይሄዳል።። እንዲህም ሆኖ ሎስ አንጀለስ ራሱ በረሀ ነው።። ካውራ ጎዳና ዳር ያለ ሳር ውሀ ሲጠጣ ያየሁት ከዚያ ነው።። እዚህ ሚዙሪ፣ ችግራቸው ሳሩን ማጨድ እንጅ ማብቀሉ አይደለም።። መቼም ከኖሩበት ሁሉም አገር ነው ይባል የለ? በሚዙሪ መፎከር ጀመርኩ መሰለኝ?

የዚያን ቀን ስብሰባ ላይ በስም እንጅ በመልክ የማላውቃቸው ብዙ ሰዎች ነበሩ።። ፅሁፋቸው የበሰለ አስተሳሰባቸው የጠለቀ ነው ብየ ያመንኩባቸው ሰዎች፣ እድሜያቸው የገፋ

ፀጉራቸው የሸበተ ወይም ጨርሶ የከዳቸው ይመስለኝ ነበር። ለካስ ብልህነት በእድሜ አይጠቆምም። ካየሁዋቸው ሰዎች አንዱ ዶክተር ጌታቸው ሀይሌ ነበሩ። ዶክተር ጌታቸውን እንኩዋ ከልጅነቴ ጀምሬ የማደንቃቸው ሰው ስለነበሩ ምን እንደሚመስሉ አውቅ ነበር። በነገራችን ላይ ይሄ ዶክተር የሚል ማእረግ በቁዋንቁዋችን ቃል የለውም እንዴ? አንድ የአየርላንድ ተወላጅ የፃፈው መፅሀፍ ላይ፣ (ደራሲውም ሆነ ርእሱ ጠፍተው ብኛል) ዶፍተር የሚለው ቃል የመጣው ደፍተራ ከሚለው የግእዝ ቃል ነው። ትርጉሙም የተማረ አዋቂ ማለት ነው የሚል አንብቤ ነበር። ታዲያ ምናለ ምሁሮቻችን ደፍተራ ብለን ብንጠራቸው?

ለማንኛውም፣ ዶክተር ጌታቸው ለኢታር (Ethiopian Regester) የሚሆን አንድ ግጥም እንድፅፍ ጠየቁኝ። ግጥም እንኩዋን ከልብ የሚነፃፍል ስሜት ስለሆነ በፈለጉ ጊዜ መፃፉ ያስቸግራል። ግን የዶክተር ጌታቸው ጥያቄ ነበርና የዚያን ቀን ሌላ ነገር ማሰብ አልቻልኩም።

ደስ ይበላችሁ

መታሰር፣
በእግረ ሙቅ ብቻ አይደለም፤
መሄድ መራመድ መከልከል፤
መታሰር፣
በካቴና ብቻ አይደለም፤
እግርን መድማት፣
እጅን መቁሰል፤

ራስን መሸጥ፣ ለባርነት፣
ለባለጊዜ መንበርከክ፣
ጉልበት ላለው ማጎብደድ፤
ይህም መታሰር ነው፣

የወራዳዎች ወሀኒ፣
የነዚያ ትከሻቸው፣
እንደሚመች ላተላ ፣
ጥንት የተነገረላቸው።።

ለነዚህ ነው 'ሚገባ ማዘኑ፣
የእስር እስር ለታሰሩ፣
የሞትም ሞት ለሞቱ።።

ግን መራመድ የተሳናችሁ፣
ታስሮ በሰንሰለት፣ እግራችሁ፣
እልል በሉ፣ ፈንድቁ፣
ነፃ ነውና ህሊናችሁ፣
ንፁህ ነውና ትከሻችሁ፣
እልል በሉ።።

ደስ ይበለን፣ ደስ ይበላችሁ፣
እኛ ለናንተ ታላቅነት፣
እናንት ደግሞ ላገራችሁ።።
ደስ ይበለን፣ ደስ ይበላችሁ።።

ኩዋስ ሜዳ ብዙም አልሄድኩም፤ ፀሀዩ ሀይለኛ ነበርና።። በዚያም ላይ ከኩዋስ ሜዳ የምሄደው የአማርኛ መፅሀፎችን ለመግዛት ነበር።። ዘንድሮ መፅሀፍ የሚባል ነገር የለም።። ሆኖም የሀዋኒ ንጉሴን የግጥም መፅሀፍ አገኘሁ።። ሀዋኒ በ እንግሊዘኛም ሆነ በአማርኛም ግሩም ግጥሞች ትፅፋለች።። ያደገችው እዚህ አገር ስለሆነ ቁዋንቁዋን አለመርሳትዋ ራሱ የሚያስገርም ነው።። ምናልባት በወላጆችዋ ሰውነት የሚፈሰው፣ በሀገር ፍቅር የተቃጠለ ደም ሳይሆን አይቀርም ከሌሎች በእስዋ እድሜ ካሉ ኢትዮጵያውያን የለያት።። ከግጥሞችዋ አንዳንድ ዘለላ ልቀንጥስ።።

ሀሳብ*

ደገምኩ ተደጋገምኩ ለኢትዮጵያ ነው እያልኩ፣
አገር አለኝ ብየም በብእር አስቀመጥኩ፣
ለናንተስ አልነበር ፍሄ ያልሰማሁት፣
ለማይሰማው ጆሮ ፅፌ ያላነበብኩት፣
እኔም እንደሌላው አገሬን የራቅሁት።

ሰማይና ምድር*

ወደቅሁኝ ምድር ላይ ሰማይን ላነሳ፣
የምድርን ምላስ ተኝቼ ላገሳ፣
ምድርን ስወድስ ሰማይን ሳጥላላ፣
ምድር አባረረኝ ሰማይ ሆነኝ ጥላ።

በበነጋው ሳንዲያጎን ማየት ፈለግሁና የባህሩን ዳር ተከትየ ቁጥር ፩ የሚሉትን አውራ ጎዳና ይገፍ ወደደቡብ መንገድ ቀጠልኩ። የአበባዎቹ ማማር፣ የቤቶቹ አሰራር፣ የሳሩ ለምለመምነት ከውቅያኖስ ብራና ላይ የተሳሉ አስመስሎአቸዋል። ዋ! ይሄ የሚያጠጡት ውሀ ያለቀ ለት አልኩ። ያፍ አመል ሆኖ እንጅ ከፈለጉ የውቅያኖሱን ውሀ አሁንም ቢሆን ያለችግር እንደሚያጣሩት ልቤ ያውቀዋል።

ቁርሴን ልበላ ካንድ ቡና ቤት ገባሁ። ሳህኑንና ብርጭቆውን ስመለከት የሀብታሞች ቦታ ይመስላል። ደግነቱ አሜሪካ አስር ብር ከያዙ ንጉሱ የሚበላበት ቦታ መብላት ይቻላል። ያሁኑማ ንጉስ ማክዶናል የሚባል ቦታ ነው የሚበላው አሉ። ከዛ ቁርስ ለመብላት ፩ ዶላር እና ፵፭ ሳንቲሞች ይበቃሉ። እኔ ከተቀመጥኩበት በስተቀኝ አንድ አሮጊት (በእድሜ ጠና ያሉ ሴትዮ ማለት ነበረብኝ መሰለኝ) ከልጅዋ ጋር ተቀምጣለች። አሮጊትዋ የምትናገረው ፍክ ብላ ነው። እያንዳንዱን አረፍተ ነገር የምትጀምረው በስድብ ነው። ልጅትዋም ከመሳቅ በስተቀር እንኩዋን የመናደድ የማፈር መልክ አይታይባትም። በላተኛውም ምንም እንዳልሰማ

**ሀዋኒ ንጉሴ (Scents of Ethiopian Poetry 1997)*

ሁሉ አቀርቅር የራሱን ሳህን ይኮሮኩማል። አሮጊትዋ እጅዋን ባነሳች ቁጥር ሁለት ሶስት አሳላፊ ይሮጣል። እኔ እንዳሮጊትዋ ብሳደብ የሚደርስብኝን አሰብኩና በልቤ ሳቅሁ። የድሮ ተዋናይ ሳትሆን አትቀርም፤ ያውም ብር የተጫነች። መልክዋን ለማስታወስ ብፈልግ ግን አቃተኝ። የገረመኝ ግን ወሬዋ ነው። የምታወራው ስለ ዴቪድ-ኔቭን ነው፣ ከሞተ ፰ አመት ያለፈው ተዋናይ። አወራርዋ ግን ትናንት እንዳነጋገረችው አድርጋ ነበር። ልጅትዋም አሮጊትዋ ስትናገር በጥሞና ታዳምጣለች፣ አሮጊትዋ ስትስቅ ትስቃለች፣ አሮጊትዋ ስታሞግሳት ደግሞ ትሸኮረመማለች።

«አርፈህ ቁርስህን አትበላም! ሁለት ጠረቤዛ ዘለህ የሰው ወሬ ከምታዳምጥ» ልትሉኝ ከፈለጋችሁ በሉ፤ እኔ ግን ወሬው ጥሞኛል።

ልጅ ሆነን ወደፊት ስናድግ የምናደርገውን እናስባለን። ገና የኛ ባይሆንም እንዲሁ በምኞት የደስታ ባህር ውስጥ እንዋኛለን። ከተወሰነ እድሜ በሁዋላ፣ የኖርንበት እየረዘመ የቀረን ዘመን እያጠረ ሲሄድ ፊታችንን ወደ ሁዋላ እናዞራለን። አስፈሪ መልኩን ላለማየት ነው መሰለኝ ጀርባችንን ለሞት እንሰጠዋለን። ፊታችን ግን ያለፍንበትን ይመለከታል። ልጆች በምኞት ባህር እንደሚዋኙ ሁሉ፣ ሽማግሎችም በትዝታ ማእበል ይዋጣሉ። ለዚህ ነው ያሮጊትዋ ወሬ የሚጥመኝ። ምኞትዋ ተፈፅሞ እንደሆነ አልፋዋለች። ካልተሳካም ጀርባዋን ለምኞት ሰጥታለችና አይተያዩም። ያላት የቀራት፣ የምታየው የሚያያት ትዝታዋ ብቻ ነው።

«ስለራስህ ነው የምታወራው፣ ስላሮጊትዋ?» ሳትሉኝ በፊት መንገዴን ልቀጥል። ስለ ሎስ አንጀለስ እና ስለሳንድያጎ ብዙ ማውራት ይቻላል ግን ልተወው። እውነቱን ለመናገር፣ ሳን ፍራንሲስኮን፣ ሎስ አንጀለስንም ሆነ ሳንዲያጎን እስከዚህም አልወደድኩዋቸውም። እንደኮሎራዶ ተራራዎች፣

እንደ ኒውዮርክ ህንፃዎች፣ እንደ ኔቫዳ በረሀዎች፣ እንደ አሪዞና ቁዋጥኞች፣ እንደ ላሬዶ ለማኞች፣ እንደ ሜክሲኮ ቆነጃጅት በልብ አውታር ላይ የሚደረደር ትዝታ አይተውም።

ወደቤት ከመመለሴ በፊት ግራንድ ካንዮንን ማየት ስለነበረብኝ መንገዴን ከሌሊቱ ፰ ሰአት አካባቢ ጀመርኩ። አውራ ጎዳና ፲፩ን ተከትየ ከዛ ወደ ፵ መሸጋገር ነበረብኝ። ግን ተሳስቼ ፲ኛውን ጎዳና ይዤ ነጎድሁ።

መጀ - መሪያ - - ስን - ገ - ናኝ፣
'ወድህ ነበር፣ ብ - ለ - ሸኝ ነ - በር፣
. . . .
እ እ እ እ እ፣ . . እ እ እ ቼ
አን - ችን ወ - ደ - ድኩኝ ተሳ - ስቼ።

ተሳስቼ የሚለውን ቃል ስላየሁ የግርማ በየነ ዘፈን ትዝ ብሎኝ ልዘፍን ብሞክር ግጥሙ ጠፋኝ።

አንድ መቶ ሀምሳ ማይል በተሳሳተ መንገድ ከነዳሁ በሁዋላ እንቅልፌ መጣና ካንድ ሞቴል ተኛሁ። ስነቃ እንደለመድኩት ቁርሴን እየበላሁ ካርታ ስመለከት መንገድ ስቼ እንደመጣሁ ገባኝ። ደግነቱ በረሀውን አቁዋርጦ ግራንድ ካንዮን የሚሄድ መንገድ አየሁ። እንዲያውም «በረሀ ፍለጋ አይደል የመጣኸው? ይኸውልህ በረሀ!» አልኩ በልቤ። እርግጥ በረሀው በረሀ ነው። ነፋሱ ከእጅ ማድረቂያ መኪና ውስጥ የሚወጣ ይመስላል። በየመንገዱ የተለጠፈው ማስታወቂያ፣ «መኪናችሁ እንዳይግል፣ የአየር ማቀዝቀዣውን አትጠቀሙበት።» ይላል። በመጀመሪያ ምክራቸውን ተቀብየ ነበር። በሁዋላ ግን ጣልያን እጅ የገባች ዶሮ የሚሰማት ስለተሰማኝ፣ ማቀዝቀዣውን እስከአናቱ ከፈትኩት።
በመጀመሪያ በረሀው ምንም የሌለበት ጭው ያለ ሜዳ

ነበር። የመጀመሪያውን ተራራ አልፌ ቁልቁል ስወርድ ግን፣ እንዚያ በ ስእል ብቻ አያቸው የነበሩ እሳት ያላጠቆረው ገል የሚመስሉ ተራራዎች ብቅ አሉ። ሸለቆው ውስጥ ከተማ አለ። የአካባቢውን ቀለም እንዳያበላሹ ነው መሰለኝ፣ የከተማው ቤቶች፣ የመንገዱ የመብራት ምሶሶ እንኩዋ ሳይቀር ሸክላ ቀለም ተቀብተዋል። አንዳንዶቹ ጋራዎች ከአፈር ሳይሆን ከሚያማምሩ ሸክላማ ቁዋጥኞች እንደተሰሩ ያየሁት፣ ሸለቆውን ወደሁላ እየተውኩ የሚቀጥለውን ተራራ መውጣት ስጀምር ነበር። ጥሩ ሙዚቀኛ ሳይ ሙዚቀኛ፣ ፀሀፊ ሳይ ፀሀፊ፣ ገጣሚ ሳይ ገጣሚ፣ ሰአሊ ሳይ ሰአይ መሆን ያምረኛል። ጥሩ ድንጋይ ሳይ ግንበኛ መሆን እንደምፈልግ ግን ዛሬ ነው ያወቅሁት።

ላሊበላ

ትላልቅ ድንጋይ ባየሁ ቁጥር፣
እንደ እብነበረድ ያማረ፣
ያልተሰነጠቀ፣ ያልተፍረከረከ፣
«ይህንን መፈልፈል»
እላለሁ በልቤ «መጥረብ ነበር፣
ወደ ቡተስኪያን መቀየር።»
በረሀው ያሪዞና፣
መች የሚጠረብ እብን አጣና፣
አለት ሳይ የተሻለ፣
የሚያህል ጋራ፣
የሆነ ጋራ፣
ስፈለፍለው ባሳቤ፣
ስጠርበው ስቀርፀው፣
ይህንን ቅድስት ማርያም፣
ያንን ደግሞ ቅዱስ ጊዮርጊስ ስሰኘው።
በረሀው አለቀ ተበረዘ ሙቀቱ፣
ተለወጠ ወደዛፍ፣ አለቱ፣
እኔም ወደ ገበሬነቱ።

ተመልሶ መጣ በስተርጅና፣

ያ እውን የማይሆን ህልም፣ የግብርና፣
ደግኑቱ፣
ያልቅና ያሪዞና ሰገኑቱ፣
የኔቫዳ በረሀ ይጀምራል፣
ከነድንጋዩ ከነአለቱ።።
እኔም እጀምራለሁ ማነፅ፣
ላሊበላን የሚያስንቅ ቤተ መቅደስ።።

ይኖርብኝ ይሆን ዘር፣ የላሊበላ?
ጥረብ ጥረብ የሚያሰኝኝ ድንጋይ፣
ቆፍር ቆፍር ተራራ?

ግራንድ ካንዮን ራሱን አልወደድኩትም።። ወደዚያ የሚያመራው ሜዳ ግን ውብ ነው።።

ሳር የሸፈነው ለም ሜዳ፣
ላይን እስኪታክት ድረስ ይሄድና፣
በዝግታ ይነሳል ወደሰማይ፣ ደመናውን ሊነካ።።
ካሮጊትዋም የባሰ ነገር መጣ፣
የማይሆን፣ የማይታወን ምኞት፣
ያልነበረ፣ ያልተፈፀመ ትዝታ።።
እኔም መፃፉ ደከመኝ፣
ልተወው መሰለኝ እዚህጋ፣
ሆድ ሳይብሰኝ በፊት፣
በሰው አገር፣ በሰው ፀጋ።።

መጠሃፍ ያልጠገበ ጓኖ!

ቅኑ ቅዳሜ፣ ጊዜው ከጥዋቱ አንድ ሰአት ነበር። ከእንቅልፌ ከነቃሁ ግን ቆይቻለሁ። አቴ&ቴ (AT&T) ስልኬን ወደነሱ እንድቀይር ማባበያ መቶ ብር ልከውልኝ ስለነበር፣ ያን ቅዳሜ የት እንደምሄድ እርግጠኛ አልነበርኩም እንጅ ኮሎምብያ ላለመዋል ቆርጫለሁ። ሀሳባቸውን ሳይቀይሩ ወይ እኔ ሳልቀይር በፊት ያችን መቶ ብር መንዝሮ ማጥፋቱን ዛሬ ዋና ስራየ አርጌዋለሁ። ገንዘቡ እንኩዋን ከካንሳስ ሲቲ ወይም ከሴንት ሉዊስ ስለማያሳልፈኝ ምርጫየ ብዙ አልነበረም። በመጨረሻም ካንሳስ ሲቲን መረጥኩ። ፍላሚንጎ ትንሽ ቁማር፣ ጥቁር አባይ የቁዋንጣ ግንፍልፍ፣ ባርንስ እና ኖብል ደግሞ መፅሀፍ ሽመታ . . ኤዲያልኝ አዲያ! ቅዳሜ ይሉሻል ይሄ ነው።

በነገራችን ላይ ባርንስ እና ኖብል በመቀምር (Computer) አማካይነት በተዘረጋው የመገናኛ ድር (Web) ላይ መፅሀፍ መሸጥ ጀምሮአል። አንድ ቀን የመቀምሩን መጠቆሚያ ጠቅ አድርጌ ስለኢትዮጵያ የተፃፉ መፃህፍት ስመለከት 75 ብሬን አራግፈውኝ ወጣሁ። ካዘዝኩዋቸው ሶስት መፅሀፎች አንዱ የኦሮምኛ መዝገበ ቃላት ነበር። ያ ገና አልደረሰኝም። ከደረሱኝ አንዱ «ዝምታ ወርቅ አይደለም» ይላል። የእንግሊዘኛ መፅሀፍ ነው። የቀይ ባህር የማተሚያ ድርጅት እንዳሳተመው ባውቅ ኖሮ እንኩዋን አልገዛውም ነበር። ግን የድሩን መግለጫ በደንብ ሳልመለከት ቀርቼ ገዛሁት። ብዙዎቹ ምእራፎች የሻቢያን የኢትዮጵያ ጥላቻ በሚያስተጋቡ ምሁራን የተፃፉ ይመስላሉ። ከሻብያና ከኦነግ የጥላቻ ኩሬ ያልተቀዱ ፀሀፊዎችም አሉበትና እነዚያን አብሬ መደመር አልፈልግም። ዶክተር ሀይሉ ፉላስ፣ ዶክተር ፍቅሬ ቶለሳንና ዶክተር ጌታቸው ሀይሌን

ለምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ዶክተር ጌታቸው ብዙ ብቸኛ የሆኑ የኢትዮጵያ መፅሀፎች፣ ቤተ ክርስቲያኖች ሲቃጠሉ አብረው እንደወደሙ ሲገልፁ፣ ነገሩ ክፉኛ አሳዘነኝ። አሁንም ያሉት፣ ወይ ተተርጉመው ወይም ተገልብጠው አላለቁምና መፅሀፎቻችን ለዘለአለም የመጥፋታቸው ሁኔታ ገና አላከተመም።

ብዙዎቹ ፀሀፊዎች ግን፣ የወደፊቱን መንገድ ትተው ያለፈውን ስህተት የሚጨምቁ ናቸው። ያለፈውን የሚጨምቁት ለታሪክነቱ ሳይሆን ላሁኑ ስህተታቸው መበረገጥ እንዲሆናቸው ነው። ግራ አይኑ የቆሰለን ሰው ነገሮች እንዲስተካከሉ ተብሎ ቀኝ አይኑን አናቆስለውም ግራውን ለማዳን እንሞክራለን እንጅ። አንድ አንዴ እንዲህ አይነቱን ሰዎች ዘረኛ ብሎ መጥራቱ የማይገባቸውን ክብር መስጠት ይመስለኛል። ዘረኛ ማለት የዘሩን ጥቅም የሚጠብቅ፣ ለዘሩ የሚያስብ፣ ለዘሩ የሚያደላ ማለት ነው። እነዚህ ግን ዘራቸውን አሳልፈው ለሌላ ዘር ይሸጣሉና የዘራቸውን ጥቅም አያስጠብቁም። እንዲያም ስለሆነ ዘረኞች ሊባሉ አይገባቸውም። «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል።» የሚለውን መርሆም አይከተሉም። ስለዚህ በድንቁርናም አይታሙም። ብቻ ራሳቸው ሰርተው ከመብላት ይልቅ የጌታቸው ጉርሻና ትራፊ የሚጣፍጣቸው ይመስላሉ። ጅናቸው ላይ የተፃፈ፣ ጅናቸው ላይ የተከተበ የባርነት ሰንሰለት ሳይኖር አይቀርም እንጅ፣ ሰው እንዴት እንዲህ ባርነትን አጥብቆ ያፈቅራል!

እንግዴህ የወሬ ቁዋቴ ስለተከፈተ፣ ወደ ካንሳስ ሲቲ መንገድ መጀመሬ ሳይገባችሁ አልቀረም። ኮሎምቢያን ከካንሳስ ሲቲ የሚያገናኘውን ጎዳና አይ-ፏ (I-70) ይሉታል። ያንን ተከትለን ወደምእራብ ያቺ ማይሎች ከተጉዋዝን ካንሳስ ሲቲ እንደርሳለን። ዘፈን እንዳላዘፍንላችሁ የመኪናየ ቴፕ ተበላሽትዋል። «ወሬው ሰለቸን ዘፈን የለም እንዴ?» እንዳትሉ በቅድሚያ

ላስታውቅ ብየ ነው። በጣም ከሰለቻችሁ ግን ንገሩኝ፣ ምን አረጋለሁ፣ እራሴም ቢሆን እዘፍናለሁ።

ከኮሎምብያ አምስት ማይል እርቆ ቁርስ የምንበላበት የከባድ መኪና ማቆሚያ ቡና ቤት አለ። አቁሞ ቡና መጠጣት፣ ቤንዚን መቅዳት፣ ቅዳሜ ነውና የሎቶሪ ቲኬት መግዛት ልማድ ነበርና ከዚያ ገባሁ። ያገሩ ሰዎች ሚድ-ዌ ይሉታል። ቤንዚኔን ሞልቼ፣ ሎቶሪየን ገዝቼ፣ ቡናየን ጠጥቼ ብቅ ስል፣ ከበራፉ አጠገብ ኩርምት ብሎ የተቀመጠ አንድ ሰው አየሁ። ሰውነቱ የተጎዳ ባይመስልም፣ ፊቱ ከባድ ጭንቀት ይነበብበታል። ለወትሮው፣ ባዝን እንኩዋን እንደዚህ አይነቱን ሰዎች ዝም ብየ ነበር የማልፋቸው። ሰውየውን ግን ትኩር ብየ አየሁት። እርሱም ትኩር ብሎ ተመለከተኝ። ጭንቀቱ ከጭንቀቴ፣ ታሪኩም ከታሪኬ ጋር ግንኙነት ያለው መሰለኝ።

«ምን ሆነህል?» አልኩት። ጠጋ ብየ።

«እንኩዋን የሆንኩት ያለሁበት ግራ ገብቶኛል። አሜሪካ አገር መሆኔ ይሰማኛልና እባክህ ከቻልክ ከአንዱ አይሮፕላን ማረፊያ አድርሰኝ። ዋሽንግቶን ዲሲ ነው የምሄድ።» አለኝ።

ብዙ ከእስር ቤት ያመለጡ ወንጀለኞች የሰው መኪና ላይ እየወጡ፣ የመኪናውን ባለቤቶች እንደሚገድሉ ስለሚወራ፣ የማላውቀውን ሰው አላሳፍርም። ያን ቀን ግን ማን አይዞህ እንዳለኝ እንጃ፣ ካንሳስ ሲቲ አይሮፕላን ማረፊያ ላደርሰው ወሰንኩ። ከሚድ-ዌ ተነስተን ሳንነጋገር አምስት ማይል ያህል ተጉዋዝን። የሚዙሪን ወንዝ ስንሻገር ሰውየው በረጅሙ ተነፈሰና፣

«ኢትዮጵያዊ ነህ?» አለኝ።

«አወን ፣» አልኩ። «ግን እንዴት አወቅህ?»

«አውቃለሁ። ስራየ ኢትዮጵያውያንን ማጥናት ነበር። ኢትዮጵያዊነትህን ብቻ ሳይሆን አፍ የፈታህበትንም ቁዋንቁዋ ልነግርህ እችላለሁ።» አለኝ። እንደዚያ የተጨነቀ፣ ከሞት ጋር ቀጠሮ ያለው የሚመስል ሰው፣ ኢትዮጵያውያንን ምን ያህል እንደሚያውቀን መናገር ሲጀምር፣ ጭንቀቱ ላንድአፍታም ቢሆን ለቀቀው። ግን ጉራው ሲያበቃ፣ እርሱም ተመልሶ የጭንቀት ባህር ውስጥ ሰጠመ። ሌላ አምስት ማይሎች በዝምታ ከተጉዋዝን በሁዋላ ፀጥታው ስለከበደኝ፣ እኔ ደግሞ በተራየ፣

«አምህ እባላለሁ። ያንተ ስም ማነው?» አልኩት።

«ስለእርዳታህ አመሰግናለሁ። ውለታ ከፋይ ያድርገኝ።» አለ። ስሙን ሊነግረኝ እንዳልፈለገ ገባኝ።

«ምናልባት ባህታዊ ይሆን?» የሚል ጥርጣሬ አደረብኝ። ግን ዝምታው አሁንም ደስ አላለኝም ነበርና። «ለምንድን ነው ያለህበትን ማወቅ ያቃተህ? ታመህ ነበር?» ብየ ጠየቅሁ።

«የለም ወንድሜ፣» አለና ጀመረ፣ በደከመ ድምፅ። «ከሞት ባሻገር ነው የተመለስኩት። ዝምታየ፣ ታሪኬ የማይታመን በመሆኑ ነው። ዝምታ የሚያስጨንቅህ ከሆነ ግን አወራልህለሁ። ታምነኛለህ ብየ ግን አልገምትም።» አለኝ።

እኔም «ብዙ የማይታመኑ ነገሮች ሰምቻለሁ፤ አይቻለሁም። ስለዚህ ሞክረኝ።» አልኩት። መንገዱ ረጅም ስለሆነ እንጅ፣ ታሪኩን እንኩዋን አምነዋለሁ ብየ አልነበረም። በልቤ፣ «እነዚህ ከጠፈር የሚመጡ ፍጡሮች ወስደውኝ፣ ጭንቅላቴን አደንዝዘውኝ፣ እንዲህ ብለውኝ፣ እንዲህ አርገውኝ . . . » ሊለኝ ነው ብየ አሰብኩ። ግን በተፈጥሮየ

ጥሩ ቱሻ ስለምወድ ወሬው እንደሚያስደስተኝ አልተጠራጠርኩም።

በሰውየው ፊት ላይ የሚነበበው ጭንቀትና ፍርሀት ግን የፈጠራ አይመስልም። አባቶቻችን «ምነው ፃእረ ሞትን ያየህ ትመስላለህ?» የሚሉት አይነት ነበር።

«ትናንት · · » አለና፣ ቀኑ አጠራጠረው መሰለኝ፣ የጀመረውን አቁዋርጦ፣ «ዛሬ ቀኑ ስንት ነው?» አለኝ።

«አስራሁለት» አልኩ፣ «መስከረም አስራሁለት።።»

«አወ ትናንት፣» አለ «አዲስ አበባ ነበርኩ። አዲስ አበባ ስሄድ የማርፈው፣ ካሜሪካን ኤምባሲ ነው። ቀኑን ኢህአደግን የሚቃወሙ የአሜሪካ ጋዜጦችና መፅሄቶች ለፃፉዋቸው መጣጥፍት ማስተባበያ ሳረቅቅ ስለዋልኩ በጣም ደክሞኝ ነበር። በዚያም ላይ ራቴን በአራት ብርጭቆ ቪኖ ነበርና ያወራረድኩት እንቅልፍ ድብን አድርጎ ወሰደኝ። ከዚያ የገባሁበት ቅዠት አያድርስ! አሁንም መንቃቴን እርግጠኛ አይደለሁም። ህልሜ ግን እንደዚህ ረዝሞብኝ አያውቅም። የዛሬው ረዘመ።»

አልፎ አልፎ የኔርቭ በሽታ እንዳለበት ሁሉ እጅና እግሮቹን ያፈራግጣቸዋል። ለካ ከእንቅልፉ ለመንቃት የሚያደርገው ሙከራ ነበር። አንዳንዴ እኔንም ያጠራጥረኝ ጀመር። «እውነት ህልም ይሆን እንዴ?» አሰኘኝ። እኔ እንኩዋን ግድ የለኝም። ያች የስልክ መቶ ብር ትቀራለች እንጅ ሌላ ምን እሆናለሁ።

ሰውየው ወሬውን ቀጠለ። «የገባሁበት ቦታ ከዚህ በፊት አይቼው የማላውቀው ነበር። ቦታው በራፍ የለውም ግድግዳውን ጥሶ መግባት ይቻላል። መውጣት ግን፣ አንድ የቦታው ባለቤት ወይም ጠባቂ የሚመስል ሰው እጅህን

ይዞህ ካልወጣ አትችልም። አንዳንዴ ያ ሰው ብቅ ይልና ከመሀላችን አንዱን መርጠ ይዞት ይወጣል። እነዚያ ሰዎች ተመልሰው አይመጡም። ካንዳንዶቹ በስተቀር ብዙዎቹ ያለፍላጎታቸው ነበር የሚወጡት፣ እየጮሁ፣ እየተፈራገጡ፣ እየተጎተቱ።

ቢቸግረኝ፣ ካጠገቤ አንድ ኢትዮጵያዊ ተቀምጦ ነበርና ወደሱ ዞር ብየ "ይህ ቦታ ምንድን ነው?" አልኩት።

እርሱም ፈገግ ብሎ፣ "ገነትና ሲኦል የሚገቡ ሙታን የሚለዩበት ቦታ ነው።" አለኝ።

እኔ በእንደዚህ አይነቱ የሞኝ ተረት ስለማላምን በርግጥ ህልም መሆኑ ገባኝ። እየተፈራገጡና እየጮሁ ከሚወሰዱት በስተቀር የብዙዎቹ ፊት በደስታ የተሞላ ነበር። እነሱም እንደኔው ህልምነቱን ያወቁ መሰለኝ። እኔም ፈገግ ማለት ጀመርኩ፣ ጥዋት ቡና ላይ የማወራው ጥሩ ህልም አገኘሁ ብየ።

ካንዱ ግድግዳ ጥግ አንድ አሮጊት ተንበርክከው ይፀልያሉ። መልካቸውን የማውቃቸው መሰለኝ። አወን አውቃቸዋለሁ፣ እማሆይ ቴሬሳ ነበሩ። ከሳቸው በስተቀኝ ደግሞ አል-ፋያድ፣ ልእልት ዳያና እና ሾፌራቸው የጠፈ ወሬ ይዘዋል። "አይ የህልም ነገር!" አልኩ በልቤ። "ጋዜጣ ላይ ያነበብኩት፣ ቴሌቪዢን ላይ ያየሁት ሁሉ፣ እውነት እየመሰለ ከፊቴ ድንቅር ይል ጀመር።"

"ህልም እንኩዋን አይደለም ۔ ۔ " አለ፣ ኢትዮጵያዊው እንደ መተከዝ ብሎ፣ "እኔም ህልም መስሎኝ ነበር። ህልም እንኩዋን አይደለም።"

"በምን ሰማኝ!" ብየ አሰብኩ፣ "ስጉመተመት ሳላስበው ጮኬ ተናግሬ ይሆናል።"

"ምነው አዘንክ፡፡ ሀጢአትህ ከባድ ነው እንዴ?" አልኩት፡፡ እንዳፈዝኩበት ገብቶታል፡፡ ግን ፊቱ አልተለወጠም፡፡ ፈዝም ሆነ ጥላቻ ከማይደርሱበት አለም ውስጥ የገባ ይመስላል፡፡

"ሀጢአቴ እንኩዋን ከባድ አይመስለኝም" አለ "በዚያም ላይ ከእማሆይ ቴሬሳ ጋር መሞት ጥቅም አለው፡፡ በሳቸው ዋስትና ብቻ ይህ የምታየው ሰው ሁሉ መንግስተ ሰማያትን ይወርሳል፡፡" አለኝና ወደትካዜው ተመለሰ፡፡

እኔም ህልም መሆኑን ባልጠራጠር እንኩዋ፣ "እውነት ሞቼ ከሆነ እድለኛ ነኝ፡፡" ብየ አሰብኩ፡፡ "ምናልባት ክርስቲያኖች ብቻ ይሆኑ ከገነት የሚገቡ?" ብየ ደግሞ ተጠራጠርኩ፡፡ "ግን አል-ፋያድና ሌሎችም እስላሞች ፊታቸው በደስታ ተሞልቶ ይታዩኛል፡፡ ለድንገቱ፣ ክርስቲያን ነኝ ማለቱ ያዋጣኛል፡፡ በእግዚአብሄር ኑረታ ባላምንም እናትና አባቴ ክርስቲያን ነበሩ፡፡ እኔም ተጠምቄያለሁ፡፡ ታዲያ ክ ርስቲያንነት ሌላ ምን ቦታ ይፈጥራል!" አልኩ በልቤ፡፡

አጠገቤ የተቀመጠው ኢትዮጵያዊ በልቤ የማስበውን እንደሚያዳምጥ ሁሉ፣ "የሚያድንህ የፃድቃኖች ፀሎት ወይም የስራህና የቃልህ አለመቃረን ብቻ ነው፡፡" አለኝ፡፡ ነገሩ ትንሽ ግር አለኝ፡፡ ግን ህልም ስለሆነ ህሊናየ ራሴኑ ሲወቅሰኝ ይሆናል ብየ አሰብኩ፡፡ እንዲያ መሆን አለበት እንጅ ይሄ ተራ ኢትዮጵያዊ የማስበውን በምን ያውቃል?

ኢትዮጵያዊውም መልሶ፣ "ክርስቲያን፣ እስላም፣ ይሁዲ ‥ ወዘተ መሆን ከእግዚአብሄር መንግስት አያስገባህም፡፡ ይሁዲ ነኝ ካልክ፣ የአይሁድ መፃህፍት የሚሰብኩትና ስራህ መስማማት ይኖርባቸዋል፡፡ ዲሞክራሲን አሰራጫለሁ እያልክ ሌሎች ህዝቦችን በዘርና በሀይማኖት እየከፋፈልክ ለተገዥነትና ለጭቆና የምትዳርጋቸው ከሆነ፣ ቃልህና ስራህ አንድ አይደለምና መንግስተ ሰማያትን አትወርስም፡፡

'ሀይማኖት የግል ነው።' የሚለው ጥቅስ፣ የተናገረው ሰው ካሰበው የጠለቀ ሚስጥር አለው። ሀይማኖትህን የምትፈጥረው ራስህ ነህና የፈጠርከውን ሀይማኖት ማክበር ይኖርብሀል። ለማንኛውም አንተን የሚያሳስብህ ጉዳይ የለም። ታየዋለህ ከዚያ ጥግ፣ ከወዳጆችህ አንዱ፣ ካሽከሮችህ አንዱ ማለቱ ሳይሻል አይቀርም፤ አገሩን እና ወገኑን ለገንዘብ የሸጠልህ?" አለና ከነብር ቆዳ የተሰፋ ኮፍያ ያጠለቀ፣ በወርቅና በዝሆን ጥርስ ያሸበረቀ ከዘራ ይዞ የቆመ ሰው አሳየኝ። "እሱ እንኩዋን ከገሀነም እሳት ይድናል።" አለኝ።

"ይህ ኢትዮጵያዊ እኔ አላውቀውም እንጅ እርሱ በደንብ ያውቀኛል። በህልሜ ከሆነ ደግሞ የህሊናየ ወቃሽ እሱ መሆን አለበት። ግን ምን አጠፋሁ?" ብየ አሰብኩ። "የኑሮ ደረጃችን ከሌላው አለም የበለጠው ጠንክረን በመስራታችን ብቻ አይደለም። ሊሆንም አይችልም። አንድ ጆንያ ቡና ለማምረት ረጅም ጊዜ ለፈጀበት ገበሬ፣ ጆንያውን በሀምሳ ብር ገዝቼ፣ ቡናውን ባንድ ሰአት ውስጥ ቆልቼ፣ ወቅጬ፣ በቆርቆሮ አሽጌ፣ መልሼ በአምስት መቶ ብር እሸጥለታለሁ። እርሱም በአንድ ሰአት ስራ ያመት ጉልበቱን ይገብርልኛል። የራሱን ቡና ራሱ ከቆላ፣ ቡናውን ወቅጦ በቆርቆር አሽጎ ከሸጠልኝ፣ የኔ የኑሮ ደረጃ እየወረደ የገበሬው እየላቀ ይሄዳል። ስለዚህ የኢትዮጵያም ሆነ የአፍሪቃ ህዝብ ያመረተውን አብስሎ እንዳይሸጥ፣ በሰላም እንዳይኖር፣ እንዳያድግ እንዳይበለፀግ መጠበቁ፣ ብሄራዊ ግዴታየ ነው።" ብየ አሰብኩ። ኢትዮጵያዊውም እያንድአንድዋን አረፍተ ነገር እንዳዳመጠ ሁሉ ከትካዜው ቀና ብሎ፣

"ነገሩ እውነትህን ነው። በእግዚአብሄር ፊት ግን ከውሸት በስተቀር ሌላ ሀጢአት የለም። ውሸት ማለት ደግሞ ስህተት ማለት አይደለም፤ የእምነትህና የግብርህ አለመጣጣም እንጅ። የኢትዮጵያ ህዝብ መቆርቆዝ ላሜሪካ ህዝብ

የሚጠቅመው ከሆነ፣ ድርጊትህ ሀጢአት አይደለም። የኢትዮጵያን ህዝብ ከባርነት ወደ ዴሞክራሲ እያራመድኩት ነው ብሎ ማውራት ግን በሰውም ሆነ በእግዚአብሄር ፊት ነውር ነው።"

"ምን ማለትህ ነው?" ልል አስቤ ነበር። ግን ጥያቄየን ሳልናገር በፊት ስለሚመልስልኝ፣ ጊዜ ማጥፋት ነው ብየ ተውኩት። እንደጠረጠርኩት፣

"ለምሳሌ፣" አለኝ "እግዜር የለም ብትል፣ ነገሩ ተጨባጭ ማስረጃ የለውምና፣ አባባልህ ስህተት ሊሆን ይችላል እንጅ ውሸታም አያደርግህም።" እስካሁን የነገረኝ እንደገባኝ ለማወቅ ነው መሰለኝ ቀና ብሎ አትኩሮ ተመለከተኝ። እኔም ከአይኖቹ የሚፈልቀው የእውነት ጨረራ ስላስፈራኝ፣ አይኖቼን መጀመሪያ የሞቡቱን ከዘራ፣ ከዚያ የዳያናን እግሮች በመጨረሻም የእማሆይን ጀርባ ቃኘሁባቸውና ስመለስ ኢትዮጵያዊው እንደ በፊቱ ሁሉ አቀርቅሮ ንግግሩን ቀጠለ። "ነገር ግን" አለ፣ በረጅሙ ተንፍሶ፣ የግራ ክንዱን ከጉልበቱ አስደግፎ፣ ራስ ምታት እንደያዘው ሁሉ የግራ እጁን መዳፍ ተንተርሶ፣ "የእግዚአብሄርን አለመኖር እያመንክ፣ ምእመናኑን የሀይማኖታችሁ መሪ ነኝ ብለህ ብታታልል፣ ያ ውሸት ይሆናል። እምነትህና ግብርህ ይቃረናሉና።"

የማስበውን ከሚያውቅ ሰው ጋር መከራከር ብዙ አልወድም። በህይወቴ የለመድኩት፣ ሰዎች ሲያምኑኝ፣ ሲያከብሩኝና ልባቸውን ሲሰጡኝ ወግቻቸው ማለፍ ነበር። ስለዚህ ወሬው በኔ ላይ ማትኮሩ ቀርቶ ወደሱ እንዲዞር አሰብኩና፣ "መፅደቁን የሚያውቅ ሰው ለምን ይህን ያህል ይተክዛል?" ብየ ጠየቅሁ።

"ሀዘኔ፣ ስለምሄድበት ሳይሆን ስለመጣሁበት ነው። ቁጭቴም

ስላጠፋሁት አይደለም ስላላለማሁት እንጅ።" ብሎ የሚከተለውን እንደሚያውቅ ሁሉ ዝም አለ።

ይህን ጊዜ ካንዱ ግድግዳ ላይ በትልቁ ንጉስ ዳዊት በገናውን እየደረደረ ብቅ አለ። የሚያዜመው ግን ኢትዮጵያዊው ሊመልስልኝ ያሰበውን ይመስላል።

ሰው ተወልዶ፣ - ያድጋልና፣
አፈር ፈጭቶ፣ - ይኖራል፣
ዳዴ ብሎ፣ - ዳዴ ዳዴ፣
ይሞታል ተኖሮ፣ - ይህም ጊዜ፣
ህይወት ተብሎ፣ - ህይወት ሆኖ፣
ግን ምን ተሰርቶ፣ - ይታለፋል፣
ምን ተትቶ?

በመጨረሻም "ግን ምን ተሰርቶ፣ ይታለፋል፣ ምን ተትቶ?" የሚለውን ጥያቄ እየደጋመ ሲያዜም ንጉስ ዳዊት ከግድግዳው እየደበዘዘ ይጠፋል። ከዚያም፣ ምንም ያህል ሳይቆይ የገነትና የሲኦልን በሮች ሸፍነው የነበሩት ሁለት ግድግዳዎች ተከፈቱ። በስተቀኝ ሰይጣኖች ይታያሉ። ግማሹ ከሲኦል በር ቆመዋል። ከውስጥ ደግሞ ጩኸትና ዋይታ ይሰማል። የገነት ውጋጋን ከሚያሳያቸው የሲኦል ዘበኞች በስተቀር ግን ሌላ የሚታይ ነገር የለም። ድቅድቅ ያለ ጨለማ ነው።

እማሆይ ከፀሎታቸው ተነሱና ራሳቸውን በሲኦል በርና በሙታኑ መሀል አቆሙ። "ከነዚህ ልጆቼ አንዳቸውም ከዚህ የጨለማ አዘቅት ከመጣላቸው በፊት እኔን ጣሉኝ የሚሉ ይመስላሉ።"

"ፍቅር ማለት ይቅርታ ነው።" የሚለውን እምነታቸውን ከሞት በሁዋላ እንኩዋን ያከብሩታል። ኢትዮጵያዊው "ቃልህና ግብርህ አንድ መሆን አለበት።" ያለኝ በእማሆይ

ሰውነት ላይ ይነበብ ነበር። በግራ ከገነት መግቢያ ላይ መላእክት ቆመዋል። ቅዳሴ ከሩቁ ይሰማል። እጣንም ይሸተኛል። ኢትዮጵያ ውስጥ የጎበኘሁዋቸውን ገዳሞች አስታወሰኝ። እማሆይ የሲኦልን በር ስለዘጉት ሙታኑ በሙሉ የሚራመዱት ወደ ገነት ነበር፤ አትገቡም ብሎ የከለላቸውም አልነበረም። እማሆይ፣ በምድር ይጎሳቆሉ እንጅ፣ በሰማይ መላእክት እንኩዋን አይጋፉዋቸውም።

እያንዳንዱ ምውት ያ ንጉስ ዳዊት የዘመረበትን ግድግዳ ሲያልፍ ሀጢአቱ ተፅፎ ይታየዋል። ሀጢአቱን መመልከት ያቃተው ሞቡቱ እንኩዋ የገነትን በራፍ አልፎ ገባ። የኔ ተራ ነበር። ቅዳሴው ደመቀ። ከበሮው ድልቅ ድልቅ ይል ጀመር። እጣኑ ሽታው ብቻ ሳይሆን ጭሱም የገነትን በር አልፎ መታየት ጀመረ። ስፈራ ስቸር ቀና ብየ የሀጢአቴን ግድግዳ ተመለከትኩ። ከየገዳሙ የሰረቅሁዋቸው መስቀሎች፣ በርካሽ የዘረፍኩዋቸው መፃህፍት፣ እነመለስ የሸለሙኝ ጥንታዊ ስእሎች፣ ከየገደሉ ተወርውረው ያለቁት መነኮሳት፣ ከስራ ተባረው ልጆቻቸው በረሀብ የሚንጫጩ ቤተ ሰቦች፣ ኢህአደግን በማድነቅ የፃፍኩዋቸው ውሸቶች፣ ያደረግሁዋቸው ዲስኩሮች፣ ያ ውሸትን ከማያውቅ የሀጢአት ግድግዳ ላይ መደርደር ጀመሩ። እንደ ሞቡቱ ሁሉ እኔም ግድግዳውን መመልከት አልቻልኩም። እንዲያም ሆኖ መሬት መሬቱን እያየሁ ወደ ገነት መራመዴን አላቁዋረጥኩም። ግን ጉዞየን አንዱ ግርግዳ አቆመው። ቀና ብየ ተመለከትኩ። ገነትም ሲኦልም አይታዩም። እኔና አስተናጋጁ ብቻ ነበርን በነዚያ በሚያስፈሩ ግድግዳዎች ተከበን የቀረነው።

"ምን ተፈጠረ?" አልኩት።

"ጊዜያቸው ሳይደር በስህተት የሚጠሩ ብዙዎች ናቸው።" አለኝ አስተናጋጁ። "አንተም ከነዚህ አንዱ ነህና ወደ መሬት መመለስ አለብህ።"

በማሆይ ቴሬሳ ምክንያት ገነት ልገባ የነበርኩ ሰው ከነሀጢአቴ ወደ መሬት ተጣልኩ። ነገሩ ህልም ሆኖ ብነቃ እንኩዋ ከጭንቀቴ የምላቀቅ አይመስለኝም። በውሸት ከመራቀቄ የተነሳ፣ ራሴን እንኩዋን ማታላል ጀምሬ ነበር። ውሸታም ለራሱ መዋሸት ካልቻለ ሸክሙ እየከበደ ይሄዳል። ያ ነው የሚያስጨንቀኝ። ምናልባት ከሲኦል ገብቼ ይሆን?»

አይሮፕላን ማረፊያ ደረስንና፣ ሰውየው ከመኪናየ ወረደ። መልኩ በመፅሄት ላይ ታትሞ ያየሁት መሰለኝ። ግን ባውቀው፣ ባላውቀው፣ ምን ይፈይዳል። እሱ የሚያገለግለው አገሩን፣ ሰው አገርህን ለምን አገለገልክ ተብሎ አይጠየቅም። መጠየቅ ያለብንስ እኛ! ምን ሰራችሁ ተብለን፣ ላገራችሁ። መጠየቅ ያለብንስ እኛ።

ካንሳስ ሲቲ ላደርግ ያቀድኩት ሁሉ አስጠላኝ። ካይሮፕላን ማረፊያው፣ ካንሳሳስ ሲቲ ሳይደርስ ወደ ኮሎምቢያ የሚመለስ መንገድ ነበርና እሱን ተከትየ ወደ ቤቴ ጉዞ ጀመርኩ። የንጉስ ዳዊት በገና ግን ከጭንቅላቴ አልጠፋ አለ። እኔም፡

ምን ተሰርቶ፣ - ይታለፋል - ምን ተትቶ?

ማለት ጀመርኩ፣ በልቤ። ከዚያም በገናው ሲደረደር ይታየኝ ጀመር።

ጣቶቹ የንጉሱ፣
የበገናውን አውታሮች ሲነቅሱ፣
ያ ሳያበቃ ተርገብግቦ፣
ሌላው ይነዝራል ድርብ ሆኖ፣
ጣት ያልነካው አውታር እንኩዋ፣
ወዳጅ ዘመዴን ብሎ፣
ይሸበራል እንደሌላው፣
ይሸበራል አድሞ።

የበገናው መቃኖች፣
የሚቃኝበት ቁልፎቹ፣
ቆዳው የተለበደበት፣
ገበታው የበታቹ፣
እኒህ ሁሉ ይነዝራሉ፣
ተመስለው ባውታሩ።።

እንዱ አውታር ለብቻው፣
የማይወጣውን ውብ ቃና፣
በህብር ሲያስተጋቡ፣ በደመራ፣
ድምፅነቱ ቀርቶ፣ ምግብነቱ ለጆሮ፣
ታየኝ ባይኔ ቁልጭ ብሎ፣
ታየኝ ላይኔ ገሀድ ሆኖ።።

ከዚያም ይሰማኛል ንጉሱ፣
በደከመ ድምፅ ሲያዜም ከሩቁ፣
ይሰማኛል።።

ምን ተሰርቶ፣ - ይታለፋል - ምን ተትቶ?
ምን ተሰርቶ።።

ያዒ ቁጥ

ሠልደ ማርያም፣ የክርስትና ስሙ ነው። ሌላ ስም አልተሰጠውም። ሆኖም ከክርስትና አባቱ ወይም ከነፍስ አባቱ በስተቀር ወልደ ማርያም ብሎ የሚጠራው የለም። ወልዴ ነው፣ ሁሉም የሚለው። የቅርብ ጉዋደኞቹማ «ወልዲሽ» ብለው ያቆላምጡታል። ስሙን ሲፈርም ወይም ፎርም ሲሞላ፣ «ወልደ ማርያም» ብሎ ነበርና የሚፅፈው፣ ራሱም ቢሆን «ወልዴ»ን እንደ ቅፅል እንጅ እንደስም አልተቀበለውም።

ወልዴ፣ በገንዘብ ሚኒስቴር የመዝገብ ክፍል ተራ ፀሀፊ ነው። ከዩኒቨርስቴ የተመረቀ የኤሌትሪክ መሀንዲስ ቢሆንም፣ በተማረው ትምህርት ለመቀጠር ጎሳው ስለማይፈቅድለት፣ በተራ ፀሀፊነት መወሰን ነበረበት። ይህም ተመስገን ነው፤ ያለዚያማ፣ የስድስት ወር ልጁንና ከእርሻ ሚኒስቴር ስራዋ ያለምክንያት የተባረረችውን ሚስቱን ምን ይመግባቸው ነበር?

ወልዴ ግን፣ አራቱን መደብ የሚችል የገሸው ጎሳ አባል የተገኘ ለት፣ ከስራው እንደሚባረር ያውቅ ነበርና መስጋቱና መጨነቁ አልቀረም። አንዳዴም ቢሆን ከጭንቀቱ ለመላቀቅ፣ ወይም እንዲሁ ሰውነቱን ለማደንዘዝ፣ ከስራ ሲመለስ አንድ ሁለት ብርሌ መወርወር ለመደ። ደሞዙ እንኩዋን፣ የቤት ወጭ ሲነሳላት ብዙም አትተርፍም። ግን እያሰለሰ ሁለት ብርሌ ለመጎተት፣ የደሞዝ ሰሞን ደግሞ እየንተንገዳገደ ቤቱ ለመግባት ትበቃዋለች።

ዛሬ ልደታ ናት፤ ወልዴ ከውሻ መርዝ ጠጅን ሲኮመኩም አምሽቶ ብቅ ይላል። ወሬ ይዞ 'ረስቶት ነበር እንጅ፣ ፌኛው ሊተረተር ደርሰዋል። ከጠጅ ቤቱ ፊት ያለውን የቆርቆሮ

አጥር ተጠጋና፣ ሽንቱ እንዳይሸተው ነው መሰለኝ ፊቱን ወደሁዋላው አዙሮ፣ ቡዋንቡዋውን ከፈተ።።

ወልዴ፣ ጠጅ ብቻ መልመድ ሳይሆን፣ ተስፋ ማድረግም አቁምዋል።። መጭው እየጨለመ ሲሄድ፣ በአንዳሩ ያለፈው ጊዜ ብሩህ እየሆነ ይታየው ጀመር።። ስለዚህ እንኩዋን መጭውን ዘመን ያለበትንም ተጨባጭ ጊዜ ጠላ።። የሚያምረው፣ የሚጥመው፣ የሚያደንቀው ነገር አጣ።። እንዲያም ሆኖ፣ ወልዴ ድሮን አድናቂ ሆነ።። ወልዴ ብለው ከሚጠሩት ይልቅ «ድሮ ቀረ» እያሉ የሚያላግጡበት በዙ።።

ወልዴ እንዲያ ተዝናንቶ ሲሸና፣ ከሁዋላው የፅዳት ዘበኛ ከተፍ አለበት።።

ዘበኛ፣ ምነው ከመንገድ ይሸናሉ፣ ጌታየ፣
ትልቅ ሰው አይደሉም እንዴ?

አንቱታው የፈዝ እንጅ የአክብሮት አልነበረም።።

ወልዴ፣ ሽንት?
የምን ሽንት?
ሽንት ድሮ ቀረ፣

ስምንት ብርሌ በአንድ ብር ከልሰን፣
ስንሸና እንዳሁኑ ካጥር ተጠግተን፣
የተከፈተ ይመስል ግድቡ የቆቃ፣
ወይ የግፊቱን ክብደት ውሀውን የገፈርሳ፣
ቡዋንቡዋው አልችል ብሎ ድንገት የፈነዳ፣
ይመስል ነበር ሲንጣለል፣
ይመስል ነበር ሲንፉዋፉዋ።።

ወይ ብሬ፣ ወይ ብሬ፣
ስም ሆና ትቅርብኝ፣
ያች ሁለት ብርሌ።።

ሽንት ይበሉት ደግሞ፣
ያንጠባጠብኩትን አምጭ፣
ያንጠባጠብኩት ታግየ፡፡

ሽንት!
ሽንትስ ድሮ ቀረ ባባ ጠቅል ጊዜ፡፡

ዘበኛ፡ ድሮን ከድሮ ጋር ያውሩ፣
ድሮ ከሆኑ፣ ድሮን ከሚያውቁ፣
አሁን ግን ክፈሉ አምስት ብር፣
ጊዜ አናጥፉ በሜዳ፣
ያልኩት መሆኑ ላይቀር፡፡

ወልዴ አምስት ብሩን ይከፍላል ብሎ ስላሰበ፣ ዘበኛው አሁንም አንቱታውን አልተወም፡፡

ወልዴ፡ ብር?
የምን ብር?
ይህን ብር ትለዋለህ? የስኩዋር መጠቅለያ፣
ግርማ ሞገስ የጎደለው፣ ያጋሰስ መደለያ፡፡
ብር ድሮ ቀረ፣

ባውንዱን መዝገፍ፣
ሞልቼ እስክፈስ ጠጥቼ፣
አላፊ አግዳሚውን፣
ከበር መልስ አጠጥቼ፣
ተዘፍኖልኝ ተሞግሼ፣
ከጠጅ ቤት ስወጣ፣
እንዳባ መስጠት ታጅቤ፣
ካጥር ቆም ስል፣
እንዲሁ እንደልማዴ፣
ሊያግዘኝ ይሁን እንጃ ወይ ተጨንቆ፣
ይሰለፋል አብሮኝ ህዝቤ፣
የተጋራ ከባውንዴ፣
የደረሰው ከበር መልሴ፡፡

ባንድነት ስንሸና፣
በህብረት፣
በኩራት፣
ደጋ የዘነበ ይመስል ነበር፣
ሲጥለቀለቅ ሰፈሩ፣
ህዝብ ሲረበሽ፣
ሲራኮት።

ይሄ ብር አይደም፣
ይልቅስ አምጣ ሌላ ወሬ፣
ብር ድሮ ቀረ፣ ባባ ጠቅል ጊዜ።

አለና ብዙ ስላወራ ነው መሰለኝ ትንፋሹ ቁርጥ፣ ቁርጥ አለበት። ከዚያም በረጅሙ እተነፍሳለሁ ሲል፣ ሳሉ ተቀሰቀሰበት። ዘበኛው፣ ወልዴ ክፉኛ ሲስል የታመመ መሰለውና፣ እንደማዘንም ሞካክሮት ነበር። ሁላ ግን ለክፉ እንደማይሰጠው ሲረዳ፣ አንቱታውን ሁሉ እርግፍ አድርጎ ትቶ ወልዴን ይዘረጥጠው ጀመር።

ዘበኛ፡ ምነው አንተ ሰካራም፣
ቢቀርብህ መናፈቁ፣
ያን የተረሳ ስርአት፣
የነቀልነውን ከስሩ።
ይልቅስ ክፈል እዳህን፣
አሳድረው ለነገ፣
ይህንን ሳል ቀኬህን።

ወልዴ፡ ሳል?
የምን ሳል?
አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል።
ቀረ መሳል ድሮ፣
ቀኽያም ትለኛለህ፣
ይህ ከሳል ተቆጥሮ?

ሲያስተጋባ ድምፁ፣
እኛ ስንስል ድሮ፣

የተኛ ጎረምሳ፣
ሁለት ደጃፍ አልፎ፣
ጉድ መጣብኝ ብሎ፣
ደንግጦ፣ ደንብሮ፣
ይነሳ ነበር፣ ባኖ።

ዛሬ ያ ሁሉ ቀርቶ፣
ደህና ሳል እንኩዋን ነፈገን፣
አኩርፎ ይሁን እንጃ፣
እግዜሩም ተቆጥቶ።

ድሮ ቀረ ሳል ወንድሜ፣
ባባ ጠቅል ዘመን፣
ባባ ጠቅል እድሜ፣
ድሮ ቀረ።

ዘበኛ፡ በል እንግዴህ ቅደም፣
እንሂድ ወደጣቢያ፣
የድሮን ታሪክ አውራሳቸው፣
ለሚገለብጡህ ከዚያ።

ወልዴ፡ ግልበጣ?
የምን ግልበጣ?
ግልበጣ ድሮ ቀረ፣
.
.
.

የድሮን ግልበጣ ሲያደንቅ ፖሊሶቹ እያመናጨቁ ካንድ ክፍል ውስጥ ይወረውሩታል። መውጣቱ እንኩዋን አይቀርም -- ያችን አምስት ብር ከፍሎ ይወጣል። ግን መውጣት ያልቻለው ከትዝታው አለም ነበር።

ለምን ከትዝታው አለም ይውጣ?
አዲሱ የሱ ላይሆን፣ የነበረውን ለምን ይጣ?
ያለው ነፃነት ይሄው ነው፣

የማይነጥቁት የቀረው፣
ደስታ የመንፈስ ባህሪ ነውና፣
አእምሮ የሚቀርፀው።።
አምስቱ መቃኛዎች ብቻ አይደሉም፣
መገንቢያው የደስታ፣
ስድስተኛው ይበልጣል፣
ጎተራው የትዝታ።።
ማሰብ፣
ማሰብ፣
የድሮውን ለመጥራት፣
ወይ አዲስ ትእይንት ለመፍጠር፤
ያ ነው የደስታ መሰረቱ፣
ይመስለናል እንጅ፣
ሌላው ሁሉ ነው ከንቱ።።

የማያ ልጀች ኪጣ

የትጋ ልጆምር . . . ?

መንገዱ አገር አቁዋራጩ-ፀጅ (I-35) ነበር፤ አቅጣጫው ደግሞ ወደደቡብ . . ። ከቤቴ ስወጣ ዘግኜ ያመጣሁዋቸው ክሮች፣ የባህታ፣ የመስፍን ሀይሌ፣ የግርማ ነጋሽና ያለማየሁ እሸቴ ነበሩ። እንደወትሮው አይብዙ እንጅ፣ የጥላሁን ዘፈኖችና የሙላቱ አስታጥቄ ሙዚቃዎችም ነበሩበት። ማኮይ ታነር፣ ናት-ኪንግ-ኮልና ዴቭ ብሩቤክም አልቀሩም። ከመንገድ ደግሞ የተሸመ ምትኩን አዲስ ክር ስለገዛሁ የሙዚቃ ስንቄ የተሙዋላ ነበር።

መቼም፣ «የጥላሁንን ድምፅ የሚወዳደር ጥንትም አልነበር ወደፊትም አይፈጠር።» ብለው የሚያምኑ ብዙዎች ናቸው። እኔ ግን የግርማ ነጋሽን ድምፅ ስሰማ ይህንን አስተሳሰብ መደገፉ ትንሽ ያስቸግረኛል። «ግርማ ነጋሽ» ይላል የመንደራችን አሉባልታ፣ «ኮንጎ የዘመተ ታላቅ ወንድም ነበረው። ወንድሙ ከኮንጎ ሲመለስ፣ ግርማ ነጋሽን በቀዳማዊ ሀይለስላሴ ቴአትር ተቀጥሮ ሲዘፍን ያገኘውና በንዴት እብድ ይሆናል። ግርማም በዚህ ምክንያት መዝፈኑን አቆመ።» ያሉባልታ ነገር ውነትም ውሸትም ሊሆን ይችላል። ግን፣ ምክንያቱ ምንም ቢሆን ክትለቱ እውነት ነው። ዘፈን በማቆሙ ግርማ ይጎዳ ይጠቀም አላውቅም። እኛ ግን፣ ያን የመሰለ ድምፅ ሰምተን ሳንጠግበው ተቁዋረጠብን።

ግርማ ከዘፈናቸው ዘፈኖች የማስታውሳቸው አምስት አይሞሉም። ያለኝ ግን አንድ ብቻ ነው፤ የኔ ሀሳብ የሚለው።

የኔ ሀሳብ፣ ባንቺ ፍቅር ተመርዞ፣
ቢያስጨንቀኝ፣ ፍፁም ልቤን አስተክዞ፣
ተጎዳሁኝ ባንች ፍቅር ተይገፍ፤
አሀ! ሀ! ሀ! ሀአ! . . . . .
ቁጭ ብየ ቀረሁልሽ ተክገፍ፣
አሀ! ሀ! ሀ! ሀአ! . . . . .
ሀሳብ ብቻ በልቤ ውስጥ ተመርኩገፍ፣
ሰቀቀኔ ሀሳቤ አንችው ነሽ፣
እንባየ እንደውሀ ፈሰሰልሽ፣
በትዝታሽ ታስሬ ስንገላታ፣
አልረባሁም፣ ፍፁም ልቤ ተረታ፤
ነይ ወደኔ የኔ ሀሳብ ወደኔ፣
አንችው ሁነሻልና ሰቀቀኔ።።

ግርማ ሲጨርስ ባህታ ይጀምራል።።

ደርበሽ ደራርበሽ ለብሰሽው የፍቅርን ብልኮ፣
አንችም እንደሌሎቹ ካልሆንሽ አትጠይም እኮ፤
አንችም እንደሌላ እንዳትሆኝ፣
የፍቅርን ጠባይ ካሁን አጥኝ፣
ዘወትር ይነሽማል ልቤ እንደከበሮ፣
ይሮጥ መስሎኝ ፍቅርሽ ከጊዜ ጋር አብሮ።።

ባህታ በፈለገው ቁዋንቁዋ ቢዘፍን፣ በሙዚቃው ከመደሰት በስተቀር ሌላ የሚያስብ አልነበረም።። አሁን ግን የባህታ ስም ሲነሳ ከሙዚቃው ውበት በፊት ትግሬነቱ ይታየናል።። ምን አይነት የበሰበሰ ዘመን መጣ!!

መንገዴን ስጀምር ሀሳቤ የተበታተነ ነበር።። አንዴ ስለዘፈን፣ ቀጥሎ አገራችን ስላለችበት ሁኔታ፣ ከዚያ ስለካንሳስ ሜዳዎች፣ ጎንበስ ቀና ስለሚሉት የኦክሎሀማ ቤንዚን ማውጫ መኪናዎች።። እንዲያም ሆኖ፣ የተበታተነው ሀሳቤ ዞሮዞሮ አንድ ቦታ ያርፍ ነበር።።

«የአእምሮ ነፃነት ይመረጣል ወይስ የስጋ (የአካል)?»

«ወያኔ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የሚጠቀምበት ዘዴ ወታደራዊ ብቻ ነው?»
«የትግልስ አይነቱ ስንት ነው?»
«እኔ ልሳተፍበት የምችለውስ ትግል የቱ ነው?»
«ይህስ ትግል እንዴት ቢካሄድ ውጤቱ ያምራል?»

ስለዚህ ሳስብ የመጀመሪያየ አይደለም። ዛሬ ግን ከጭንቅላት ወደወረቀት ሊተላለፍ አምሮታል መሰለኝ እየደጋገመ ይታየኝ ጀመር። በመሀሉ ግን የሙላቱ አስታጥቄ ሙዚቃ ጀመረና ከሀሳብ እንቅልፌ ብንን አልኩ። የሙዚቃውን ስም አላውቀውም። ግን ተሾመ ምትኩ፣ «የዘመድ የባዳ» እያለ የሚያዜመውን ይመስላል። ይህ ዜማ፣ በሙዚቃ መሀይምን ለሆንን ሰዎች ለመግለፅ የሚያስቸግር ጠባይ አለው። ግርማ ሀይሉ ግን፣ እንዲህ አይነቱ ዜማ ሲያጋጥመው፣ «ስማው ማርሽ ሲለውጥ!» ይላል። እውነትም፣ እነዚህ ሙዚቃዎች ማርሽ እንደተለወጠለት መኪና ሁሉ ዝም ብለው ይቆዩና፣ ባዲስ ጉልበት፣ ባዲስ ድምፅ፣ ባዲስ ፍጥነት ይጀምራሉ።

ዳር ዳር የምለው ስለ ሙላቱ የተፃፈ ግጥም ላስነብባችሁ ፈልጌ ነው። ሙላቱ ሲነሳ ለወትሮው የጃዝ ሙዚቃዎቹ፣ በተለይም «ምነው ወዳጄ ምነው» የሚለው ነበር ትዝ የሚለኝ። አሁን ግን ስዊትዘርላንድ በተደረገው የወያኔ የባህል በአል ላይ አጋፋሪ ሆኖ መክረሙን ሰምቼ፣ ያ ነው ከፊቴ ድቅን የሚለው። የተነሳሁበት ዋናው አላማየ ይህ ባይሆንም፣ ከዚህ የተሻለ አጋጣሚ ስለማይኖር ግጥሙ ይሸውላችሁ።

<u>ምነው ወዳጄ ምነው?</u>

ስንልህ ጋሼ ጋሻችን፣
ስንልህ አያ መመኪያችን፣
የባህላችን ጠባቂ፣
የጠመመውን አራቂ፣
ምነው ጠማህ ከጠበሉ?

አስፈርቶህ ይሆን፣ የወያኔው ቄስ፣ መስቀሉ?
ምነው ወዳጄ ምነው?

እንዲህ የሚያስፈራ መስቀሉ፣ የሚከረፋ ጠበሉ፣
ሊሆን አይችልም ካህን፣ ዲያቢሎስ እንጅ ኃጌሉ።
ታዲያ ጠበል ከመቅመስ የከረፋ፣
የፍርሀት መስቀል ከመሳለም፣ ጥዋት ማታ፣
አይሻልም ነበር መኖሩ፣
ከደዌህ ጋር ከችግሩ?
ምነው ወዳጄ ምነው?

ኦክሎሀማን ጨርሼ ቴክሳስን ስጀምር ሀሳቤ መበታተኑን አቆመ። ሀራምባና ቆቦ ማሰብ ከመጀመሬ በፊት ያሰብኩትን ላጫውታችሁ።

ወያኔ በኢትዮጵያውያን ላይ የሚያካሂደው ጦርነት ሶስት መልክ አለው።

፩. ወታደራዊ
፪. ምጣኔ-ሀብታዊ
፫. ባህላዊ

የመጀመሪያው ሁለቱ ጦርነቶች ግልፅ ናቸው። ሶስተኛውንም ቢሆን፣ ዶክተር ማሞ ሙጨና ዶክተር ጌታቸው ሀይሌ በተከታታይ በጥቅምትና በህዳር የኢታር (EtR Oct/Nov 1996) እትሞች ላይ የአማርኛን ቁዋንቁዋ በተመለከተ ባቀረቡዋቸው ፅሁፎች ውስጥ ገልፀውታል።

፩. ወታደራዊ ጥቃትን ለመቁዋቁዋም መፍትሄው የትጥቅ ትግል ብቻ ነው። ለኔ የትጥቅ ትግል ሁለት ክፍል አለው። መዋጋት፤ ወይም ለሚዋጉ ትጥቅና ስንቅ ማቀበል። ፖለቲካዊ ፈርጅ አለው ብለው የሚያምኑም አሉ። ግን የአሜሪካን የሽንጎ አማካሪዎችና ርእሰ-ብሄሮች በመማጠን ነፃነታችንን እናገኛለን ብሎ ማሰብ፣

አንድም የችግራችንን መነሾ፣ ያለዚያም የነፃነትን ትርጉም አለማወቅ ነው።

፪. «ብረት አንግቦ መዞር ያሸናፊነት ምልክት አይደለም። ያገሪትዋን የምጣኔ ሀብት በቁጥጥሩ ስር ያዋለ፣ ፖለቲካውንም በቁጥጥሩ ስር ማዋል ይችላል።» የሚሉም አሉ። ለዚሁም ምሳሌ የአሜሪካን አይሁዶችና እስያውያንን ይጠቅሳሉ። ይህም ቢሆን ትክክል አይመስለኝም። አሜሪካ፣ መንግስቱን ከሶ ለመርታት የሚያስችል ጠንካራ ህግ የሰፈነበት አገር ነው። በአንፃሩ ወያኔ የማይፈቅድላቸው ግለሰቦች የንግዱን አለም ቢይዙ፣ ሀብታቸውን ይዘርፋል፣ ግለሰቦቹንም ያስራል፣ ይገድላል። ተበደልኩ ብሎ የሚጮህ ነጋዴ ቢኖርም፣ አጥፍተህል ብሎ በወያኔ ላይ የሚፈርድ ዳኛ፣ ወይም ፍርዱን የሚያስፈፅም ሀይል የለም። ስለዚህ ባሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ፣ እነግዳለሁ፣ አርሳለሁ ወይም ፈብሪካ አቆማለሁ ማለት፣ ወያኔን ቆሜ አብልቼ ገበታ ሲነሳ ትራፊውን እበላለሁ ማለት ካልሆነ በቀር ሌላ ትርጉም የለውም።

፫. **የባህል ጦርነት፦**
የዛሬ ፷፯ አመት አካባቢ ይመስለኛል የ ፲፪ኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ። ዶክተር ጌታቸው ሀይሌን የአማርኛ አስተማሪያችን፣ አቶ ሀይማኖት ጋብዝዋቸው መጥተው ንግግር አድገረውልን ነበር። ያደረጉትን ንግግር አብዛኛውን እረስቸዋለሁ። ሆኖም፣ ያልረሳሁት ወደፊትም የማልረሳው አንድ እውነት አስቀርቻለሁ።

«አባቶቻችን!» አሉ ዶክተር ጌታቸው፣ «አባቶቻችን የተዋጉት፣ አባቶቻችን የሞቱት፣ ሀይማኖታቸውን፣ ቁዋንቁዋቸውን፣ ባህላቸውን ለማስከበር እንጅ ላለመገዛት አልነበረም። መገዛትማ አሁንስ እንገዛ የል?»

ለኔ እንደገባኝ፣ ከስጋ (ከአካል) ነፃነት ይልቅ የአእምሮ ነፃነት ይበልጣል ማለታቸው ነበር። ወያኔዎች ትግርኛን የኢትዮጵያ ዋንኛው ቁዋንቁዋ፣ የትግሬን ባህል ደግሞ እንዲሁ የኢትዮጵያ ባህል ለማድረግ ቢመኙ ኖሮ፣ እስከዚህ ባልተጨነቅሁ ነበር። ትግርኛ የኢትዮጵያ ቁዋንቁዋ ነው። የትግሬም ባህል የኢትዮጵያ ባህል ነው። በዚያም ላይ የትግሬ ባህል ከሌሎች የኢትዮጵያ ባህሎች ጋር ተደባልቆ ይጠፋል እንጅ፣ ሌሎችን አጥፍቶ ብቻውን መቆም አይችልም። ይህ አይሆንም የሚል ሰው ካለ፣ አማርኛንና የአማራን ባህል ይመልከት። ዶክተር ማሞና ዶክተር ጌታቸውም፣ አማርኛ የአማሮች ሳይሆን የኢትዮጵያውያን ሁሉ ቁዋንቁዋ ነው ብለው የፃፉትም ለዚሁ ነበር። ዶክተር ፍቅሬ ቶለሳም፣ «የኦሮሞ አስተዋፅኦ ለኢትዮጵያ ስልጣኔ (ER March 1993)» በሚል ርእስ፣ ባቀረቡት ፅሁፍ፣ አማርኛ ከኦሮምኛ የተዋሰው ቃላት ብቻ ሳይሆን የአረፍተ ነገር አሰካክ (ሰዋስው) ጭምር እነደሆነ አስረድተውናል። ይህም አማርኛ የአማሮች ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያ ቁዋንቁዋ መሆኑን በድጋሜ ይመሰክራል።

አሁን አማርኛ ብለን የምንጠራው መደበኛ ቁዋንቁዋ፣ እንኩዋንስ የመጀመሪያዎቹን የአማርኛ ተናጋሪዎች ይቅርና ያሁኖቹንም ጎንደሬዎች ግር የሚላቸው ይመስለኛል። ለምሳሌ፡ «በፀሀይ እምብርትና በአንድ ፈለካ እምብርት መሀከል ያለው እርቀት የሚወስነው ምህዋር፣ የግልብጥ ላማዊን ህግ ያከብራል።» ብል የትኛው የጎጃም ገበሬ ነው፡ «የለም ተሳስተሀል፣ ርቀቱ የሚለካው ከፀሀይ እምብርት ሳይሆን ከ ፀሀይና ከ ፈለካው የጋራ ስበታዊ እምብርት ጀምሮ ነው።» የሚለኝ? ከወለጋ የመጣ ተማሪ ግን፣ ምናልባት ካንድ ሁለት ጥያቄዎች በሁዋላ ለማለት የፈለግሁት ይገባዋል።

የሚሳዝነው ግን ወያኔ ብሄራዊ ቁዋንቁዋችንን በራሱ ሳይሆን በቅኝ ገዥዎች ቁዋንቁዋ ለመተካት የሚያደርገው ጥረት

ነው። ከወያኔ ጋር ከሚደረገው ትግል ሁሉ ይሄኛው ቀዳሚ መሆን አለበት። የትጥቅ ትግል መደረግ የለበትም ማለቴ አይደለም። ገዳም የገባን መነኩሳት አይደለንምና ስጋችንንም ማስገዛት የለብንም። ግን፣ የመገዛት ቅደም ተከተል ይውጣ ከተባለ፣ ከስጋ ነፃነት በፊት የአእምሮ ነፃነት መቅደም ይኖርበታል። ነፃ አእምሮ በባርያ ሰውነት ውስጥ መኖር ሲችል፣ አእምሮውን ያስገዛ ነፃ አካል ግን ትርጉም የሌለው ሀረግ ነው።

የአእምሮ ነፃነት ራሱ ሰፊ ትርጉምና መገለጫ ይኖረዋል። እኔ ግን ነገሩን ልመለከተው የፈለግሁት በጠባቡ ነው። እንዲያ ማድረጉ ስለችግሩ ብቻ ሳይሆን ስለ መፍትሄውም እንዳወራ ይረዳኛልና። ከአእምሮ ባርነት መገለጫዎች አንዱ፣ በቅኝ ገዥዎች ቁዋንቁዋ መማር ነው። የወያኔ መንግስት፣ በቀዳማዊ ሀይለስላሴም ጊዜ ሆነ በደርግ ዘመን ከዚህ አሳፋሪ ባርነት ለመላቀቅ የተደረገውን ጥረት የተገኘውንም ድል ወደ ሁዋላ ለመመለስ እየታገለ ነው። በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ልንዋጋቸው ከምንችላቸው ጦርነቶች በቀላሉ ልናሸንፈው የምንችለው ቢኖር ይኸኛው ነው።

አሁንም ለምሳሌነት ከትምህርት አይነቶች ሁሉ ስነ-ፍጥረትን እንውሰድ። ይህንን ማድረጌም ያለምክንያት አይደለም። ታሪክ፣ መልክአ-ምድር እና ስነ-ልቡናን የመሳሰሉ የትምህርት አይነቶችን ኢትዮጵያዊ ለማድረግ ቁዋንቁዋውን መለወጥ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ታሪክ፣ የኢትዮጵያን መልክአ-ምድር የኢትዮጵያውያንን ስነ-ልቡና መመርመር ያስፈልጋል። ስነ-ፍጥረት ግን እንዲያ አይደለም። ስነ-ፍጥረት ሰዎች ሳይሆኑ የተፈጥሮ ቅንጣቶች የሚከተልዋቸው ህግጋት ጥናት ነው። እነዚህ ህግጋት ደግሞ ከሰው አስቀድሞ ነበሩ፣ ከሰው በሁዋላም ይኖራሉ። ስለዚህ ስነ-ፍጥረትን ኢትዮጵያዊ ለማድረግ የቁዋንቁዋ ለውጥ ብቻ ይበቃል።
«አማርኛ ይህንን ለውጥ ለመቀበል ብቃት አለው ወይ?»

ብለው የሚጠይቁ አይጠፉም። እንዲህ አይነቱ ሰዎች ጥያቄ ማቅረባቸው አይደለም። ስሜታቸውን በጥያቄ መልክ የሚደረድሩት፣ «ብቃት የለውም።» ለማለት ድፍረት ስለሚያንሳቸው ብቻ ነው። በተጨማሪም ያአዋቂነታቸው ምልክት ይኸው የባርነት ቁዋንቁዋቸው ስለሆነ እንዲነካባቸው አይፈልጉም። መልሱን ግን፣ ከሚያወሩት ሳይሆን፣ የዳርዊንን (The Origion of Species) «የብቸኛ ዝርያዎች መንስኤ» በሚል ስያሜ ወደ አማርኛ የመለሰውን የዶክተር ሰለሞን ይርጋን አስተያየት እንስማ።

«ጃፓኖች» ይላል፤ ዶክተር ሰለሞን፤ «ስነ-ፍጥረትን ወደ ቁዋንቁዋቸው የመለሱ ጊዜ፣ ጃፓንኛ የነበረበት ደረጃ ካሁኑ አማርኛ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ሁዋላ ቀር ነበር።» ረሳሁት እንጅ፣ ሁዋላ ቀርነቱን ለማስረዳት አንድ ሁለት ምሳሌዎችንም ደርድሮልኝ ነበር።

በዚያም ላይ ኢትዮጵያውያን የታደልን ነን። «እንዴት?» ማለት ደግ ነው። አንድ ሳይሆን ከሰማንያ የማያንሱ ቁዋንቁዋዎች አሉን። ካንዱ የጠፋው ቃል ከሌላው ሊገኝ ይችላል። ወይም ተራ ትርጉማቸው አንድ የሆኑን ቃላት ስነፍጥረታዊ ወይም ኢትዮጵያዊ ትርጉማቸውን ማለያየት እንችላለን። ለምሳሌ ፈረንጆች (Force, Power, Energy) የሚሉዋቸውን ፊዚካዊ ግንዛቤዎች፣ በአማርኛ ጉልበት፣ አቅምና ሀይል ብለን ልንተረጉማቸው እንችል ይሆናል። እነዚህ ትርጉሞች ካልጣሙን ደግሞ፣ የኦሮሞኛውን ሀይል (Force) የጉራጌኛውን ሀይል (Power) የአማርኛውን ሀይል ደግሞ (Energy) ብለን ስነ-ፍጥረታዊ ትርጉም ልንሰጣቸው እንችላለን። ሌላ ምሳሌ ለመስጠት እግረ መንገዴንም ከጎጃሙ ገበሬ ጋር የጀመርኩትን ወሬ ለመደምደም፡ «የግልብጥ ላማዊ ህግ» ማለት ፈረንጆች 'The inverse square law' የሚሉት ነው። «ላማ» የሚለው ቃል በኦሮምኛ ሁለት ቁጥር ማለት ሲሆን፣ ስነ-ፍጥረታዊ ትርጉሙ ግን አንድ ምጥን በራሱ መባዛቱን ያመለክታል።

ባጠቃላይ የኦሮምኛ ቁጥሮች ስነ-ፍጥረታዊ ትርጉማቸው ያንድን ምጥን እይል ወይም ቁንጮ ማሳየት ይሆናል። እይል ወይም ቁንጮ ማለት ደግሞ (Power) ወይም (Exponent) ማለት ነው። ይኽ ሁሉ «ኢትዮጵያውያን የታደልን ነን።» ያልኩትን ለመደገፍ እንጅ፣ ስራው የኛ ሳይሆን የቁዋንቁዋና የስነ-ፍጥረት ሊቃውንት ነው። የኛ ፋንታ ምሁራኑ በቁዋንቁዋችን እንዲፅፉ ማበረታታት ይመስለኛል።

«የያዘውን የወረወረ ፈሪ አይባልም።» ይባል የለ? እኔም ያሰብኩዋትን ልወርውርና ወደዘፈኔ ልመለስ። በዚያም ላይ አሁን ያሜሪካን ድንበር አልፌ ሜክሲኮ ውስጥ ስለሆንኩ፣ የመኪናየን ፍጥነት መቆጣጠር ይኖርብኛል። ሰው እንዴት ፷ ኪሜ/ሰአት ይጉዋዛል? ከ፸ ማይል/ሰአት ያነሰ እኮ ነው! እኔ ደግሞ ትምህርት ቤት አካባቢ ያለሁ መስሎኝ ካሁን ካሁን ፍጥነቱ ይጨምራል እያልኩ ስጠብቅ እቆይና፣ «ከ፷ ኪሜ/ሰአት ፍንክች ትልና ዋ!!» የሚል ምልክት ብቅ ይልብኛል። የው እንግዴህ የኔ ነገር የተነሳሁበትን አላማ ትቼ ሌላ ወሬ ቀጠለኩ ..... ወደ ጀመርኩት ጉዳይ ልመለስ።

የስነ-ፍጥረትን ትምህርት ከቅኝ ገዥዎች ቁንቁዋ ለማላቀቅ እስካሁን ሶስት የተለያዩ ዘዴዎች ታስበውኛል። ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ዘዴዎች ይልቅ ሶስተኛው የተሻለ መስሎ ይታየኛል። ግን እንደኔ የምታስቡ ሰዎች ካላችሁ ችግሬን እንድትረዱልኝ፣ ወይም የተሻለ መንገድ ካለ እንድታስተምሩኝ ሶስቱንም ዘዴዎች እዘረዝራቸዋለሁ።

<u>አንደኛው ዘዴ፡</u>

- ☐ 200 ኢትዮጵያውያን ባመት እያንዳንዳቸው $200.00 ያዋጣሉ 280,000 ብር
- ☐ የመፃፍ ችሎታ ያላቸው ምሁሮችና ሌሎች ባለሙያዎች እንደሚከተለው ይቀጠራሉ
  - 1 የቁዋንቁዋ ሊቅ 24,000 ብር
  - 1 የፊዚካ ሊቅ 24,000 ብር
  - 1 የቅመማ ሊቅ 24,000 ብር
  - 1 የስነ-ህይወት ሊቅ 24,000 ብር
  - 1 የሂሳብ ሊቅ 24,000 ብር
  - 2 ፀሀፊዎች 24,000 ብር
  - 1 ሰአሊ 12,000 ብር

 ተጨማሪ ወጭ

2 መቀምሮች(Computers + Printers)	35,000 ብር
1 ቢሮ (ኪራይና ሌሎችም አስፈላጊ ወጭዎች)	36,000 ብር
መዕህፍ ማሳተሚያ	40,000 ብር

 ድምር 267,000 ብር

የዚህ ዘዴ ችግሩ፣ ሁሉ ነገር በግልፅ መሰራት ስላለበት ፀሀፊዎቹ ለወያኔ ጥቃት ምቹ ይሆናሉ።።

<u>ሁለተኛው ዘዴ፡</u>

 200 ኢትዮጵያውያን ባመት እያንዳንዳቸው $ 200.00 ያዋጣሉ 280,000 ብር
 ለመጀመሪያው አመት፡ 4 የትምህርት አይነቶች ይመረጣሉ።።
እነዚሁም የሁለተኛ ደረጃ ፊዚካ፡ቅመማ፡ስነ-ህይወትና ሂሳብ ይሆናሉ።።
ዝርዝር ይዞታቸው ለኢትዮጵያውያን የስነ-ፍጥረት መምህራንና ሊቃውንት
በሚደርሱ መፅሄቶችና በተባባሪ ድርጅቶች በኩል ይሰራጫሉ።።
ፀሀፊዎቹም እነዚህን መዕህፎች በግላቸው ፅፈው ለውድድር ያቀርባሉ።።
 8 ዳኞች ይመረጡና ከያንዳንዱ የትምህርት አይነት 3፡ በጠቅላላው 12
አሸናፊዎች ይመርጣሉ።።
 ለያንዳንዱ ትምህርት አሸናፊዎች 1ኛ ሽልማት 24,000 ብር፡ 2ኛ 12,00 ብር
3ኛው ደግሞ 6,000 ብር ይሆናል።።
 ዝርዝር ወጭ

ለ 12 አሸናፊዎች ሽልማት	168,000 ብር
ፅሁፎቹን ለማተሚያ ቤት ዝግጁ ለማድረግ	24,000 ብር
ለሰአሊ	12,000 ብር
ዳኞች 10 ቀናት ቢሰበሰቡ (የውሎ አበል)	16,000 ብር
መዕህፍ ማሳተሚያ	40,000 ብር

 ድምር 260,000 ብር

የዚህ ዘዴ ችግሩ፣ ማሸነፍ አለማሸነፉን ሳያውቅ አንድ አመት የሚፈጅ ስራ ተቀምጦ የሚሰራ ሰው ማግኘቱ ከባድ መሆኑ ነው።።

<u>ሶስተኛው ዘዴ፣</u>

200 ኢትዮጵያውያን ባመት እያንዳንዳቸው $ 200.00 ያዋጣሉ 280,000 ብር
 ለመጀመሪያው አመት፡ 4 የትምህርት አይነቶች ይመረጣሉ።።
እነዚሁም የሁለተኛ ደረጃ ፊዚካ፡ቅመማ፡ስነ-ህይወትና ሂሳብ ይሆናሉ።።
ከያንዳንዱ ትምህርት 10 ጥልቀታቸው ተመጣጣኝ የሆኑ ምእራፎች
በጠቅላላው 40 ምእራፎች ይመረጡና ዝርዝር ይዞታቸው ለኢትዮጵያውያን
የስነ-ፍጥረት መምህራንና ሊቃውንት በሚደርሱ መፅሄቶችና በተባባሪ
ድርጅቶች በኩል ይሰራጫሉ።። ፀሀፊዎችም እነዚህን ምእራፎች ፅፈው
ለውድድር ያቀርባሉ።። ከነዚህ ምእራፎች አንዱን ለመፃፍ፣ በቀን 2 ወይም 3
ሰአት ጎጠፋበት ሰው ከ ሁለት እስከ አራት ሳምንት ቢፈጅ ነውና ከድካም
አንፃር ሲታይ ከባድ ስራ አይደለም።።

- 8 ዳኞች ይመረጡና ከያንዳንዱ ምእራፍ ተወዳዳሪዎች 1 አሸናፊ ይመርጣሉ። በተጨማሪም ከያንድአንዱ የትምህርት አይነት አሸናፊ የሆኑትን 10 ሰዎች በችሎታ ደረጃ ይደረድሩአቸዋል።

- አርባዎቹ አሸናፊዎች እያንዳንዳቸው 2ሺ ብር ይሸለማሉ። ከያንዳንዱ ትምህርት አንደኛ የሆኑት 4 ሰዎች ደግሞ ዋንኞዎቹን መፅሀፎች እንዲፅፉ ይቀጠራሉ።

- ዝርዝር ወጭ

40 አሸናፊዎች ሽልማት	80,000 ብር
1 የፊዚካ ሊቅ	24,000 ብር
1 የቅመማ ሊቅ	24,000 ብር
1 የስነ-ህይወት ሊቅ	24,000 ብር
1 የሂሳብ ሊቅ	24,000 ብር
ፅሁፎቹን ለማተሚያ ቤት ዝግጁ ለማድረግ	24,000 ብር
ለሰአሊ ..	12,000 ብር
ዳኞች 10 ቀናት ቢሰበሰቡ (የውሎ አበል)	16,000 ብር
መፅሀፍ ማሳተሚያ	40,000 ብር

- ድምር 268,000 ብር

የዚህ ዘዴ ጥሩነቱ ፀሀፊዎቹ በግል ስለሚሰሩ የወያኔ መንግስት ሊያቆማቸው አይችልም። በተጨማሪም 40ዎቹን አሸናፊዎችና፣ በየጊዜው፣ «ችሎታው አለንና ስማችን ከመዝገብ ይያዝልን።» ብለው ፅሁፎቻቸውን ለዳኞች የሚያቀርቡትን ሰዎች ስም ዝርዝር ስለምንይዝ፣ መፅሀፍ ለማፃፍ በፈለግን ቁጥር ከነዚህ ሰዎች አንዳቸውን መርጠን መቅጠሩ ብቻ በቂ ይሆናል።

ማህበሩ ለአምስት አመታት እንኩዋን ቢቆይ፣ ይህንን አሳፋሪ ባህል ከመሰረቱ ያናጋዋል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ አንድ መፅሀፍ እንኩዋን ማፃፍ ቢችል፣ ወደፊት ለሚነሱ ተመሳሳይ ድርጅቶች አርአያ ይሆናል።

ሳልጠቅሰው ያለፍኩት አንድ ጉዳይ አለ። ካሁን አስቀድሞ፣ በግልም ሆነ በመንግስት ደረጃ ተመሳሳይ ስራ ለመስራት ጥረት ተደርግዋል። ከዚህ በፊት ተፅፈው ሳይታተሙ የቀሩ፣ ጥራታቸውና ደረጃቸው ደግሞ ማህበሩ ከሚወስነው ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ መፅሀፎች ካሉ፣ አዲስ ከማፃፍ ይልቅ እነዚያን ማሳተሙ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።

ቱስዙዘት፤ ቱስዙዘት! ኽካካችዙ ቱስዙዘት!

እንግዴህ ያሰብኩትን ወረወርኩ፤ ዘፈኔን ልጀምር መሰለኝ። ወደቤቴ ለመመለስ ከሜክሲኮ ወደ አሜሪካ የሚያስገባው የድንበር ከተማ ደርሻለሁ። ገናን ከዘመዶቹ ጋር ለማሳለፍ ወደ ሜክሲኮ የተጉዋዘው ህዝብ መመለሱ ነው መሰለኝ፣ መኪናየን አስፈትሼ ድንበሩን ለማለፍ ፫ ሰአት ወሰደብኝ። አቤት የለማኙ አበዛዝ!! ለማኞቹ አለባበሳቸው ከመንገድ ከማያቸው የሜክሲኮ ሰዎች ይለያል። መልካቸው ጠቆር ያለ፣ ሰውነታቸው ቀጭን፣ ቁመታቸውም ያጠረ ነው። መጥቆራቸውና መክሳታቸው የችግር ብቻ አልነበረም፤ ከዘር የወረሱት ጅን ጠባይም እንጅ። ነገሩ ግን አሳዘነኝ። ሀዘኑ ለነሱ ብቻ ሳይሆን ለራሴም ጭምር ነበር።

ያ ሁሉ ክብር ቀርቶ፣
ያ ሁሉ ኩራት ተንኮታኩቶ፣
ባገራቸው፣ በወንዛቸው፣
መለመን ይሁን እጣቸው?

የንጉሶቻቸው ታላቅነት፣
የከዋክብት አቃቢዎቻቸው ጥልቅ እውቀት፣
የመሀንዲሶቹ ትእግስት፣
የሰአሊዎቹ የውበት ስልት፣
አፈር በላው፣ በሰበሰ፣
    የማያ ስልጣኔ፣
ልጆቹን ዳርጎ ለምፅዋት፣
    ልጆቹን አርጎ የኔ ቢጤ?

ያየሁ መሰለኝ ቆሜ፣
የራሴን እድል አትኩሬ፣
ባህሌ ቁዋንቁዋየ ጠፍቶ፣
የቀረኝ ኩራት ተሙዋጦ አልቆ፣
ከመንገድ ዳር ተገትሬ፣
ስለእማምላክ ስል አለሜ።

ታየኝ ሲያልፉ ተመግድቀው፤
«ሰርቶ አይበላም እንዴ?» ተሰኝተው፤
ታየኝ መድረሻዋ የሀገሬ፣
ማጡ ረመጡ፣ መውደቂያው የወገኔ።

ከመኪናየ ወርጄ፣
እጆቼን ወደ ሰማይ ዘርግቼ፣
«ጋባላዊ!!»* ብየ መጮህ አማረኝ፣
ግን ተውኩት ሰው ፈርቼ።

ስጋቸው ባርያ ሆነ፣
ለስጉኛው ለርዝራዡ፣
ባህል ቁዋንቁዋቸው ተወረረ፣
አእምሮአቸውንም አልያዙ።
የጥንት የናታቸው ጅን፣ የሚለያቸው ከሌላ፣
መሆኑ ቀርትዋል ምልክት፣ የማያ ልጆች መኩሪያ፤
እንዲያ ይሆን፣ የኛም እድል?
እንዲያ ይሆን፣ የኛም እጣ?

ናጅብ ማህፉዝ፣ የመንደሩ ልጆች (Nagiub Mahfouse, Childern Of The Alley)
ጋባላዊ የመንደሩ ሁሉ አባት ነው። ሰዎች ሲጨንቃቸው፣ ወይም ሆድ ሲብሳቸው ፊታቸውን ወደ አያታቸው ግቢ ያዞሩና «ጋባላዊ!!» ብለው ይጮሀሉ።

ያጣችኝ መጽሐፍ*

ኒኛ ትውልድ ስለመፅሀፉ ሄኖክ የሰማው በቅርብ ነው። እኔ ያየሁት ባጋጣሚ ነበር። «ኢትዮጵያ» የሚለውን ቃል፣ የመፈለጊያ ዘር አድርጌ ለቤተ-መፅሀፍታችን መቀምር ሳቀብለው፣ ከዘረዘረልኝ ርእሶች አንዱ፣ «የግእዙ መፅሀፉ ሄኖክ ስነ-ከዋክብታዊ ምእራፎች» የሚል የሂሳባዊ-ፊዚካ መፅሄት ነበር።

ዛሬ ደግሞ፣ የስነ-ከዋክብታዊ ምእራፎቹን ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም የማንበብ ፍላጎት አደረብኝ። ከምክንያቶቹ አንዱ፣ አየለ በከሬን «ግእዝ - አፍሪቃዊ የአፃፃፍ ዘዴ - ታሪኩና ስርአቱ።» ተሰኝቶ የፃፈውን የእንግሊዘኛ መፅሀፍ ማንበቤ ነበር።

መፅሀፉ፣ ሁሉም ነገር የወጣው ከኢትዮጵያ፣ የእውቀት ምንጭ አፍሪቃ፣ ታሪክም ከጥቁር ህዝብ አብራክ የተገኘ ነው የሚለውን ፍልስፍና ስለሚከተል እጅግም አልወደድኩትም። የፅሁፉን መሰረታዊ ሀሳብ ጠልቼው አይደለም፤ ግን በጥናትና በሀቅ ላይ ሳይሆን በስሜት ላይ የተንጠለጠለ አስተሳሰብ ነውና ለዚያ ነው ብዙም ያላጠገበኝ። ለነገሩማ ደረቴን ነፍቼ የእውቀት ሁሉ ምንጭ እኛ ነን ለማለት የሚያስችለኝ እውነት ባገኝ ለምን

በ 1991 ወይም በ1992 አም፣ ከፕሮፌሰር ንጉሴ አየለ ጋር ባንድ አጋጣሚ ተገናኝተን ስናወራ በህይወት የሌሉ አባቶቻችንን እና እናቶቻችንን በህይወት ካሉ ኢትዮጵያውያን ጋር አገናኝተን የምናወያይበት ልበ ወለዳዊ መድረክ ብናዘጋጅ እንዴት ጥሩ ነበር፣ የሚል ሀሳብ ተነሳ። ያንን ሀሳብ በመከተል ለምሳሌነት ያባቶች መደብ የሚለውን ተረት ፃፍኩ። ፅሁፉንም ለብዙ ኢትዮጵያውያን ፀሀፊዎች ልከን በእይታቱ የራሳቸውን አስተሳሰብ እንዲፅፉልን ጠይቀን ነበር። ተረቱንም ጥሪውንም በEthiopian Register አሳትመነውም ነበር። ሆኖም መልስ የሚሰጠን ባለማግኘታችን እቅዱ ሳይሳካ ቀረ። ፅሁፉ ተጥሎ እንዳይቀር በማሰብ ይህንን መፅሀፌን ስከልስ አስገብቼዋለሁ።

ይከፋኛል። በተጨማሪም፣ ከቀይ ባህር አሳታሚ ድርጅት፣ ስለኢትዮጵያ መልካም ነገር ያዘለ ፅሁፍ ይወጣል የሚል እምነት የለኝም። ዋናው አላማው በየገፁ «ኤርትራና ኢትዮጵያ» እያሉ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር በእኩልነት መድረክ ላይ የሚያስቀመጡ መፅሀፎችን ማሳተም ይመስለኛልና።

ሄኖክ ራሱ፣ ፀሀይ እየተባለ የሚጠራውን ትልቁን ብርሀን፣ ከአራተኛው በር ተነስቶ እስከስድስተኛው በር የሚያደርገውን ጉዞ ሲያስረዳ፣ «ከስድስተኛው በር የቀኑ እርዝመት የሌሊቱን እርዝመት እጥፍ ይሆናል።» ይለናል። እንዲያውም የሌሊቱና የቀኑ ውድር 6፡12 እንደሚሆን ቁልጭ አድርጎ በሂሳባዊ መልኩ አስቀምጦታል። ይህ ሁኔታ ሊፈጠር የሚችለው የመሬት ማገር(Latitude) 49 ዲግሪ ሲሆን ብቻ ነው። ይህንን ተከትለን ወደ መሬት ደቡብ ዋልታ ብንጉዋዝ፣ ብዙም ሰው የሚኖርበት መሬት አናገኝም። ስለዚህ ሄኖክ ይህንን የመሬትና የፀሀይ መስተጋብር የተመለከተው በሰሜኑ ግማደ-ሉል እንዲያውም በጥቁር ባህር አካባቢ ሳይሆን አይቀርም ያሰኘናል። ሄኖክ ሰአት የሚቆጥርበት መሳሪያ ስህተት ነበረበት ብንል እንኩዋን፣ ከቱርክ ወይም ከሶርያ ወደደቡብ ልናወርደው አንችልም።

እርግጥ ሄኖክ ኢትዮጵያዊ አልነበረም ማለት አልችልም። ምናልባት ለትምህርት ወይም ለንግድ ወደ ሰሜን ተጉዞ እኛ በሰው አገር ቀልጠን እንደቀረነው ሁሉ፣ እሱም የኛው አይነት እድል አጋጥሞት ይሆናል። አይንን ጨፍኖ ሄኖክ ኢትዮጵያዊ ነበር ማለት ግን፣ ስነ-ፍጥረታዊ መሰረት ያልያዘ ስሜታዊ አባባል ነው።

እንዲም ስለሆነ፣ መፅሀፉን የምወደው ነገር አላገኘሁበትም ማለት አይደለም። ነጮች የጥቁር የሆነውን ነገር ሁሉ እንደሚያጣጥሉ፣ በምሬት ሲገልፅ ልቤን ነክቶኛል። በተለይ

መፅሀፈ ሄኖክን በተመለከተ የፃፉትን አስተያዬት እኔም ባይኔ ያየሁት ስለሆነ፣ ምሬቱ ምሬቴ ነው።።

ምናልባት ልጆች ሆነን ፓስቴ ሳይገዛልኝ አልቀረምና፣ አየለ በከሬን ለቀቅ ላድርገውና ወደተረቴ ልመለስ።።

የአማርኛ መፅሀፈ ቅዱሴን አነሳሁና ሄኖክን ገለጥኩ።። ቀኑ ደመና የሸፈነው፣ «እኝ እኝ ብላ» የምንለው ዝናብ አይነት የሚያካፋበት ቀን ነበር።። ጥሎብኝ፣ ያገሬን ክረምት እየመሰለኝ፣ እንዲያ አይነቱን አየር እወደዋለሁ።። ከካፊያም ይበልጥ አገሬን የሚያስታውሰኝ ሲወርድ የምሰማው፣ ነጎድጉዋድ ያጀበው ዶፍ ነበር።። ያ ከልተገኘ ግን ካፊያውም ቢሆን ጥሩ ነው።። አገር ቢሆን ኖሮ በዚህ አይነቱ አየር ብዙ የሚሰራ ነገር ነበር፤ ግን ከሰው አገር ምን ማድረግ ይቻላል - መፅሀፍ ከማንበብ በስተቀር።። ለነገሩ ጉንፋን ብጤ ይዞኝ፣ መድሀኒት ውጬ ተሸፋፍኜ ለመተኛት ሞክሬ ነበር።። ግን እንቅልፍ አልወስድ ስላለኝ ነበር መፅሀፈ ሄኖክን ለማንበብ ቆርጬ የተነሳሁበት ሌላው ምክንያቴ።። የእንቅልፍ ነገር መፅሀፍ ሲያነሱ ይመጣል፣ መፅሀፉን ሲያጥፉት ደግሞ ይጠፋልና፣ ብዙም ሳላነብ እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ አለ።። «እንቅልፍ ይዞኝ ጭልጥ አለ።።» ማለቱ ይቀለኛል።። አለዚያ፣ ህልሙን ራእይ፣ ተረቱን ደግሞ ታሪክ ያልኩ ያስመስልብኛል።።

ድብልቅልቅ ሲል አየሩ፣ ነጎድጉዋዱ ሲያጉዋራ፤
መብረቁ ሲወረወር፣ ሰማዩ እንደቀን ሲያበራ፤
ወይ የተተረተረ ሲመስል፣ የእግዜርን ቁጣ ሊተፋ፣
ሲደበድበ ዝናቡ፣ የቤቱን ቆርቆሮ ጣሪያ፣
ውብ እንደሆነ ድምፁ፣ የሚጥም ላበሻ ጆሮ፣
መች ያውቃሉ እነዚህ፣ አይነ ልቡናቸው ታውሮ።።
መች ያውቃሉ እነዚህ፣ ደስታን በገንዘብ የሚለኩ፣
በቅራቅንቦ መንኩራኩር፣ በየምናምንቴው ሁሉ፣
መች ያውቃሉ።።

ለማነው ፊቱን አዙሮ ግጥም የሚያነበው እያልኩ ሲገርመኝ፣ ሰውየው ዞር ቢል እራሴው ነኝ። በዚያ ደነገጥኩና ከእንቅልፌ ብንን አልኩ። መፅሀፉን በጀ እንደያዝኩት ነበርና ማንበቤን ቀጠልኩ።

«እናንት ለሰው ትለምኑ እንጅ፣ ሰው ለናንተ ሊለምንላችሁ አይገባም ነበር።» ይላል መ.ሄ 4፡70

እውነት የታሪክ ሁሉ መጀመሪያ፣ የጥበብም ሁሉ መፍለቅያ ከሆንን፣ ሌሎች የኛን እጅ አይተው እንጅ፣ እኛ የሌሎችን አይተን መኖር አልነበረብንም። መፅሀፉ፣ ስለኛ ስለኢትዮጵያውያን የሚያወራ መሰለኝ።

«እርስ በራሳቸው ተቀራደው ወደሚጠፉበት ቦታ አስወጥተህ ስደዳቸው፣ የዘመን እርዝመት የላቸውምና እነርሱ ራሳቸው በሰይፍ ተቀራደው ያልቃሉ።» መ.ሄ 3፡12

ለሁለተኛ ጊዜ እንቅልፍ ወሰደኝ። ባንድ ከፍተኛ ኮረብታ ላይ ብዙ ሰዎች ቆመው ይጮሀሉ። ከፊታቸው ካለ ሌላ ኮረብታ ላይ ደግሞ፣ እንደ ፀሀይ የምታበራ ሴትዮ፣ በአረንጉዋዴ ቢጫና ቀይ ያሸበረቀ ቀሚስና ኩታ ለብሳ ተቀምጣለች። እንደ ሄኖክ ሁሉ፣ «ምንድን ናቸው እነዚህ የሚጮሁ? ያቺስ ማናት፣ የምታበራ?» ብዬ ጠየቅሁ። መልአኩ ሩፋኤል አጠገቤ አልነበረምና፣ ጥያቄየን ማ ይመልስልኝ። ከጭዋሂዎቹ አንዱ በሰማይ እየተንሳፈፈ መጣና አጠገቤ ሲደርስ ቆመ። ሰውየው አንተ ሳይሆን አንቱ የምላቸው ነበሩ። ከዚህ በፊት አይቻቸዋለሁ፤ ግን ልጅ ሆኑብኝ።

«በዚህ ስጋ የለም።» አሉኝ፤ ፕሮፌሰር አስራት። «ሁሉም ነገር መንፈስ ነው። ስጋ የምንለብሰው ጎብኝዎች እንዲያዩን ስንፈልግ ብቻ ነው። እኔም የጎልማሳነት ዘመኖቼን በጣም

እወዳቸው ስለነበር፣ ስጋ መልበስ ካለብኝ የልጅነት ስጋዬን እመርጣለሁ።» ከዚያም «ጥያቄህን ስለሰማን ነው ይህንን የመንፈስ አለም እንዳስነበኝህ የተላኩት። ጭዋሂዎቹ ኢትዮጵያውያን ነን። ያች የምታበራ ሴትዮም፣ የኢትዮጵያ አምላክ ናት። ከደብረ ቅዱስ የወረዳችሁት በገዛ ሀጢአታችሁ ነው ብላ ስለተቀየመች፣ ጨኸታችን አይሰማትም። እንደሚወራው አጤ ሚኒልክን አነጋግራቸው ነበር ይባላል። "እዚህ መጮህ ብቻ ዋጋ አይኖረውም፣ ጥፋታችሁን ማረም፣ ሀገራችሁንም መልሳችሁ ደብረ ቅዱስ ማድረግ፣ በምድር ያሉ፣ ስጋ የለበሱ ወገኖቻችሁ ፋንታ ነው። ስራ ካልታከለበት ጨኸት ብቻውን አይጠቅምም ብላቸዋለች።" ይባላል። አጤ ሚኒልክም፣ በየሳምንቱ፣ አዋቂዎችን እየሰበሰቡ፣ "ኢትዮጵያ ምን ብታደርግ ጥፋትዋ ይታረማል? ደብረ ቅዱስነትዋስ እንዴት ይመለስላታል?" እያሉ ሲጠይቁ ይሄው መቶ አመት ሊሞላቸው ነው። ዛሬም፣ ያን የተለመደ ጥያቄያቸውን የሚያቀርቡበት ቀን ስለሆነ፣ ከዚያ እወስድህለሁ።» አሉኝ።

ከሁዋላችን የቀሩት ኢትዮጵያውያን ጨኸታቸው ቀጠሉ፣ የኢትዮጵያም አምላክ ግድ የለሽነትዋን።

«የምታየው ሁሉ እንደምታየው አይምሰልህ። ተራራው አፈር፣ ሰው ደግሞ ስጋ የለበሰው ላንተ እንጅ፣ ተፈጥሮው እንዲያ ሆኖ አይደለም። ተፈጥሮውን ማስረዳትም አይቻልም። ለምን አሁን አልታየኝም ብለህም አትጨነቅ። የሰው ልጅ ሁሉ የመጨረሻ ቤቱ ይኸው ነውና ትደርስበታለህ። የምመኝልህ ነገር ቢኖር፣ ጊዜህን የምታጠፋው ካበሻ መጮሂያ ሳይሆን ከአባቶች መደብ እንዲሆንልህ ነው።» አሉኝ፣ ፕሮፌሰር አስራት።

እኔም፣ «ያባቶች መደብ ምንድን ነው?» ብየ ጠየቅሁ።

«ያማ አጤ ሚኒልክ አዋቂዎችን እየሰበሰቡ ምክር

የሚጠይቁበት ቦታ ነው። ወደዚያው ነውና የምንሄድ፣ ታየዋለህ።» አሉኝ።

ወደአባቶች መደብ ለመድረስ የምናልፍበት አገር ተራራማ ነበር። ሰማዩን ደመና ሸፍኖታል። ሲያካፋም ይሰማኛል። ዝናቡ ግን እኛን አይነካንም ነበር። መሬቱ አረንጉዋዴና ለምለም ነው። አልፎ አልፎ ጢስ የሚጠሰባቸው፣ የኮባ ዛፍ የከበባቸው ጎጆ ቤቶች፣ ይታዩኛል። ከየጎጆው ቡሄ ነው መሰለኝ ድፎ ዳቦ ሲጋገር ይሸተኛል። አልፎ አልፎ ኮረብታዎቹ ገለጥ ሲሉ ከብቶች የሚግጡበት፣ ፈረሶች የሚፈነጩበት ሜዳ አያለሁ።

«እዚህም እንደምድር ሁሉ ታርሶና ተቆፍሮ ነው ወይ የሚኖረው?» ብዬ ጠየቅሁ።

ፕሮፌሰር አስራት ፈገግ አሉና «የለም ሚስጥሩ ሌላ ነው።» አሉ። «እኛ የምንለብሰውን ስጋ እንደምንመርጥ ሁሉ፣ አንተም የምታልፍበትን አገር ትመርጣለህ። ይህ የምታየው አንተ የምትወደው እንጅ እውን አይደለም።»

እንዲያ የምወደውን ሁሉ እየፈጠርኩ ስንጉዋዝ ሳላስበው ከአባቶች መደብ ደረስን። የአባቶች መደብ በድንጋያማ ኮረብታ የተከበበ ትንሽ ሸለቆ ነው። ዙሪያው በክቡ የተሰራ ረጅም መደብ አለ። ምንም የሚያምር ነገር የለበትም። እኩዋን ዛፍ ሳር አይታይበትም። እንዲሁ ከጥንት ሰወች የተረፈ ፍራሽ ይመስላል። መደቡ መሀከል አንድ ሰው ቆምዋል። መደቡን ግን የተመጠበት ሰው አልነበረም።

«ይህ የምታየው ሰውዬ ያጤ ሚንሊክን ጥያቄ ለመመለስ ከምድር ተጋብዞ የመጣ ነው። አባቶቻችንና እናቶቻችንም ከመደቡ ተቀምጠዋል። ገና ስጋ አልለበሱምና አታያቸውም። ባህል ሆኖ አጤ ሚኒልክ ጥያቄያቸውን ከጠየቁ በሁዋላ ነው ስጋ የሚለብሱት።» አሉ ፕሮፌሰር አስራት።

ትንሽም ሳይቆይ ሸለቆው እንደ ትያትር መድረክ ሁሉ ጨለመ። መደቡ ያለበት አካባቢ ግን ቁልጭ ብሎ ይታያል። ከበስተሰሜን እነደጎድጉዋድ የሚያስተጋባ ድምፅ ተሰማ።

«እንኩዋን ደህና መጣህ ልጄ!» አሉ አጤ ሚኒልክ። መጀመሪያ የሚናገሩት እሳቸው ናቸው ብዬ እንጅ ገና ሰው አለየሁም። ከዚያም ሻሹን ግጥም አርጎ ያሰረ፣ ጥቁር ካባ የለበሰ ሰው ከበስተሰሜን ያለው መደብ ላይ ተቀምጦ አየሁ። መሀሪው ንጉስ እንደሆነ በመንፈሱም ሆነ በስጋው ያስታውቃል። ማን ሊሆን ይችላል ሌላ፣ እምዬ ምኒልክ እንጅ።

አጤ ሚኒልክ ከመደቡ ተነሱና ቆሙ። «ኢትዮጵያ ምን ብታደርግ ጥፋትዋ ይታረማል? ደብረ ቅዱስነትዋስ እንዴት ይመለስላታል?» አሉና ተመልሰው ከመደባቸው ተቀመጡ። የመደቡን ዙሪያ የኢትዮጵያ እናቶችና አባቶች ሞሉት። መልካቸውን የማውቃቸው፣ ስማቸውን ብቻ የሰማሁት፣ እንኩዋን መልካቸውን ላስታውስ ስማቸውን ለመጥራት እንኩዋን የሚያዳግተኝ ሰዎች ነበሩበት።

መህል የቆመውም ሰው ጥያቄው ለሱ መሆኑን ስለሚያውቅ ንግግሩን ጀመረ።

«የተከበራችሁ እናቶችና አባቶች። ተናጋሪን ከሚያስጨንቁት ነገሮች አንዱ ንግግሩን እንዴት እንደሚጀምር ነው። መፅሀፍ ቅዱስ፣ "በመጀመሪያ እግዚአብሄር ሰማይና ምድርን ፈጠረ። ምድርም ባዶ ነበረች። አንዳችም አልነበረባትም።" ብሎ ይጀምራል። ፍፁምነቱ የሚታመንለት የእግዚአብሄር ቃል እንኩዋን መጀመሪያን ከመጀመሪያው መጀመር አልቻለም። ዛሬ ልናገር የፈለግሁት ስለግል መብትና ስለጋራ መብት ነው። ሆኖም፣ የመብትም ጉዳይ እንደእግዚአብሄር ቃል ሁሉ

በፍፁም እውነት ላይ ሳይሆን በእምነት ላይ የቆመ ነውና፣ እኔም ነገሬን ከስሩ ሳይሆን በእምነት ከመሀሉ እጀምራለሁ። ከስሩ መጀመር ብፈልግም አልችልም። ያ እንኩዋን ለኔ ለመለኮትም ተስኖታል።»

አጤ ሚኒልክም «የለም ልጄ፣ የምድሩን ጠየቅንህ እንጅ የሰማዩንማ መቼ አጣነው። ካንተ ይልቅ እኛ ኖረንበት የለ!» እንደ መሳቅ ብለው ፊታቸውን ወደራስ ነበና አዞሩና፣ «እውነቴንም አይደል፣ ነበና?» አሉ።

«አዬ ጃነሆይ፣ ይሄ ምን ኑሮ ነው፣ ደግነቱ እነሱም ሞት እንጅ ኑሮ ብለው አልጠሩትም። ኑሮም ነው ቢሉኝ ኑሮ ብዬ አልቀበለውም። ጎራዴዬን መዝገር፣ የጠላቴን አንገት የማላበርበት ኑሮ ምን ኑሮ ነው።» አሉና ራስ ነበና በሀዘን መሬት መሬቱን ይመለከቱ ጀመር።

«ወንድሜ ነበና» አሉ፣ ራስ አሉላ ቀበል አርገው፣ «ምነው የባህር በራችንን አብረን ጠብቀን ቢሆን ኖሮ! አሁን ይሄ የባንዳ ልጅ ሁሉ አገራችን ኢትዮጵያ ላይ ጥሬ አሩን አያራም ነበር።»

አጤ ሚኒልክ ጉባኤው መስመሩን ሊስት ነው ብለው ስላሰቡ፣ ፊታቸውን ወደ ተናጋሪው አዙረው፣ «ቀጥል ልጄ፣ እኔ ነኝ ያቁዋረጥኩህ፣ እኔ ነኝ ጥፋተኛ።» አሉ።

ተናጋሪውም ቀጠለ።

«መብት ምድን ነው?
"የመናገር መብት አለኝ።" እንላለን። ስለዚህ መናገር መብት ነው።
"ሰው ራሱን የመግደል መብት የለውም።" እንላለን። ስለዚህ የተከለከለ መብት ነው እንጅ፣ ራስን መግደልም መብት ነው። ራስን ለማዳን፣ ንብረትን ለመጠበቅ፣ በአብዛኛው

ህብረተ ሰብ ውስጥ ሌሎችን መግደልም የግል መብት ነው፡፡ ስለዚህ መብት ምንድን ነው?

መብት፣ ማንኛውም ፍጡር በገዛ ፍላጎቱ ሊፈፅመው የሚችለው ድርጊት ነው፡፡

ለምንድን ነው መብትን ማጥናት ወይም መደንገግ ያስፈለገን?

በመሰረቱ የጋራ መብታችንን ለመጠበቅ ነው፡፡ የጋራ መብታችንንም ለመጠበቅ ማህበራችን ጠንካራና ለጠላት ያልተመቸ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ የማህበራችን አባሎች በእኩልነት መታየት አለባቸው፡፡ ወይም መብታቸው እኩል መሆን አለበት፡፡ ያለዚያ በማህበራችን ውስጥ ሌሎች ንኡስ ማህበሮች ይፈጠራሉ፡፡ ሁለት ማህበሮች በመፈራራት አብረው ይኖራሉ እንጅ፣ በመሰረቱ ጠላቶች ናቸው፡፡ ግለሰቦችም ቢሆኑ እርስ በራሳቸው በመፈራራት ወይም የጋራ ጠላታቸውን በመፍራት አብረው ይኖራሉ እንጅ በተፈጥሮ ጠላቶች ናቸው፡፡ ሆኖም በአንድ ማህበር አባሎች መሀል ያለው ቃል ኪዳን በቀላሉ የሚሰበር አይደለም፡፡ የዚህም ምክንያቱ ቀላል ነው፡፡ አንድ ግለሰብ ለብቻው የመኖር አቅም የለውም፡፡ ማህበር ግን ከሌሎች ተለይቶ ይቆማል፣ ወይም መቆም አለመቻሉን ለመገንዘብ ጊዜ ይፈጅበታል፡፡

እንግዴህ፣ ጠንካራ ማህበር ለመፍጠር፣ የማህበሩ አባሎች የግል መብት እኩል መሆን አለበት፡፡

የማህበሩ አባሎች የጋራ መብትሳ?

የማህበሩ አባሎች የጋራ መብትም ለየግለሰቡ ወይም ሰው ካልሆኑ ለየግለ-ፍጥረቱ የሚደርሰው እንዲሁ በእኩልነት ነው፡፡ ምክንያቱም የጋራ መብት የሚከሰተው ማህበሩ

ከሌሎች ማህበራት ጋር በሚያደርገው ግንኙነት እንጅ በአንድ ማህበር ግለ-ሰቦች ወይም ግለ-ፍጡሮች መሀል አይደለም።

ለምሳሌ አንድን በግ አርደን የምንበላው ያ በግ ስላስቀየመን አይደለም፤ በግ ስለሆነ ብቻ ነው። እያንዳንዱ በግ፣ በጥፋቱ ወይም የሰውን መብት በመግፈፉ አይደለም የሚሰቃየው። የሰው ማህበር የበግን ማህበር የጋራ መብት በመግፈፉ እንጅ።»

አለቃ ገብረሀና ጋቢያቸውን በትከሻቸው ላይ ወርወር አደረጉና፣ ጭራቸውን አንድ ሁለቴ አወዛወዙ። ለትዝታው ያህል ጭራ ይይዛሉ እንጅ ባካባቢው ዝንብም ሆነ ዝንብ የሚስብ ምግብ የለም። «ጃነሆይ!» አሉ አለቃ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው። «ምኑን አመጡብን ዛሬ ደግሞ? በግ አትብሉ ነው የሚለን? አጋሰስ አትጫኑ ነው የሚለን?»

አቶ ጳውሎስ ኞኞ አለቃን በደንብ አጥንትዋቸዋል። ተናግረው ሳይጨርሱ ለማለት የሚፈልጉት ሁሉ ይገባዋል። አንዳንዴ ሊያበሳጫቸው ሲፈልግ፣ ያሰቡትን ሳይናገሩ እሱ ቀድሞ ይናገረውና ያስቅባቸዋል። ዛሬም፣ ተናጋሪው ስለአጋሰስ ሳያወራ አጋሰስን አብረው መደባለቃቸው ለተንኮል እንደሆነ ገባውና፣ «አለቃ!» አለ ጳውሎስ «ዝም አይሉትም፣ ለዘመዶቹ መከራከሩ ይሆናላ!»

«ኤዲያ!» አሉ አለቃ፣ ጳውሎስ ለማለት የፈለጉትን እንደቀማቸው አውቀው። «ለማንኛውም እዚህ ጮማ የለጠጅ የለ። ይኸው የበግና የበሬ መብት ሳከብር መቶ አመት ሊሞላኝ ነው። እኔም እንደጎበና ምድሩ እንጅ ሰማዩ አልተስማማኝም።»

አጤ ሚኒልክ ጳውሎስ ኞኞን ይወዱታል። ሁሌ በስተግራቸው ነው የሚያስቀምጡት። ቀልዱም

ይጥማቸዋል፣ ምክሩም ይስማማቸዋል፡፡ «አይ የልጅ አዋቂ!» ይላሉ፣ ሚኒልክ ጳውሎስን ሲያደንቁ፡፡ «ግማሹ አረመኔ ነው ሲለኝ፣ ሌላው ደግሞ ሀውልቴን ሊያፈርስ ሲታገል፣ ስሜ እንዳይጠፋ በመዝገብ ጥፈው ካስቀመጡት ልጆቼ እኮ አንዱ እሱ ነው፡፡» ይላሉ፡፡

በአለቃና በጳውሎስ ተረብ አባቶች ሁሉ ትንሽ ከሳቁ በሁዋላ እንግዳው ንግግሩን ቀጠለ፡፡

«ምናልባትም የበግ ምሳሌ ከክብራችን በታች መስሎ ከታየን፣ የሰው ማግኘቱም ቀላል ነው፡፡ ሆኖም የሚከተለውን እንመልከት፡፡ የራስሴላስ መስፍነ ኢትዮጵያ ታሪክ ተብሎ በሲራክ ወልደ ስላሴ ሀሩይ ከተተረጎመው መፅሀፍ ገፆች ባንዱ የሚከተለውን ምንባብ እናገኛለን፡፡

> *በተራራው ግንባር ላይ ሲሄድ በዝናቡ ምክንያት ጥንቸሎች ወደየቅጠሉ ስር ለመጠለል ሲሉ ትተውት የሄዱትን በሰየፉ የተቆፈረ ጉድጓድ አዩ፡፡ ኢምላክም አለ፤ «አውሬና እንስሳ በልማድ የሚአደርጉትን በመመልከት ሰው ያገኘው ብዙ ጥበብ አለ፤ ማለት ከጥንት የመጣ ነገር ነው፡፡ ስለዚህ፤ እኛም ከነዚህ ጥንቸሎች መማርን ከውርደት አንቁጠረው፤ እንደነሱ ተራራውን በሰየፉ ነድለን ለመውጣት እንችል ይሆናልና፡፡»*

ስለዚህ ከእንሰሳት መማርም ነውር አይደለም ብለው የሚያምኑ ብዙዎች ናቸው፡፡ ወደ ሰው ምሳሌ እንመለስና፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ወንዶችን የሚሰልቡ ጎሳዎች ነበሩ፡፡ ሰዎቹ ከራሳቸው ማህበር ወይም ጎሳ ያለ ግለሰብ አይሰልቡም፣ የሌላ ጎሳ አባል እንጅ፡፡ ተሰላቢው በግል ያጠፋው ነገር የለም፡፡ እንዲሰለብ የተፈረደበት ማህበር አባል በመሆኑ ብቻ ነው ይህ አሰቃቂ ግፍ የሚፈፀመበት፡፡

ስለዚህ የጋራ መብት ጥቅሙ፣ ማህበሩ ደካማ ከሆነ፣ ከሌሎች ጥቃት ለመጠበቅ፣ ጠንከር ሲል ደግሞ ሌሎች ማህበራትን ለማጥቃት ወይም የሌሎችን የግል መብት ለመግፈፍ ነው። እንግዴህ የአንድ ማህበር አባላት ንኡስ ማህበር ከፈጠሩ ዋነኛው ማህበር ፈረሰ ወይም የመፍረሱ ሂደት ተጀመረ ማለት ነው። ምክንያቱም ንኡስ ማህበሩ የተፈጠረው ሌሎችን በግል ሳይሆን በጅምላ ለመጨቆን ስለፈለገ ነውና።

ማህበሮች መኖር የለባቸውም። የአንድን ማህበር አባሎች የግል መብትም መንጠቅ የለብንም ማለቴ አይደለም። መኖር ስላለብን መብላትም ይኖርብናልና የበግና የሰላጣ መብት አንጠብቅም። በዚያም ላይ፣ በግና ሰላጣ መብታቸውን የማያስከብሩ ደካሞች ስለሆኑ፣ የጋራ መብታቸውን ለመግፈፍ የሚያስፈራን ነገር አይኖርም።»

«እንዲያ ነው እንጅ!» አሉ አለቃ ገብረሀና፣ ፊታቸውን ወደ ጳውሎስ መልሰው በቁጣ እየተመለከቱት።

«ሰው ብለን የምጠራውም ማህበር፣ እንደምናስበው እውነተኛ ማህበር አይደለም። ጥቂርን ሰው ባቅራቢያቸው ያገኙት ዛፍ ላይ ሰቅለው፣ ያለምንም የህሊና ጭንቀት ቤታቸው ገብተው፣ የሜዳ አህያ ዘሩ ሊጠፋ ነው ብለው ስቅስቅ ብለው የሚያለቅሱ ቁጥራቸው ብዙ ነው። ስለዚህ የመብት ጉዳይ የእውነት ወይም የሀሰት፣ የትክክለኛነት ወይም የመሳሳት አይደለም። ህይወታችንን ለማርዘም፣ ደስታችንን ለማብዛት፣ በምናደርገው ጥረት ማህበራችን ምን መምሰል አለበት? ምን ብናደርግ ማህበራችን ጠንካራ ይሆናል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ነው።

ተፈጥሮ ራሱ፣ አለምን ህይወት ባላቸውና በግኡዛን፣ በእፅዋትና በእንሰሳት፣ ከዚያም ሰው፣ በግ፣ አንበሳ እያለ ስለከፈለው፣ ከሰው በስተቀር የማህበራችን አባል የሚሆን ሌላ ፍጡር እንደሌለ ግልፅ ነው። በሰው መህልም ቢሆን

እንዲሁ የተፈጥሮ ልዩነት አለ። በተለይ ጥቁሮች ለብዙ ዘመናት የሰው ማህበር አባል ለመሆን ጥረናል። አልተሳካም። እንደከብት ሸጠውናል። እንደአጋሰስ ጭነውናል። መርከባቸውን ቀዝፈናል፣ ቤተ-መቅደሳቸውን ገንብተናል፤ ጥጣቸውን ለቅመናል፣ ምግባቸውንም ቀቅለናል። ልዩነታችን ጊዜ ወይም ትምህርት የሚሽረው አይደለም። ስለዚህ ማህበራችን ልዩ ነው።

ራስሴላስን እንደገና ልጥቀስላችሁ። ሆኖም መፅሀፉ በሲራክ ወልደ ህሩይ ተተረጎመ እንጅ፣ ፀሀፊው እንግሊዛዊው ፕሮፌሰር ሳሙኤል ጆንሰን ነበር። ይህንን መገንዘቡ የነጮችን ትምክህት ለመረዳት ይጠቅማል። ፕሮፌሰር ጆንሰን በኢምላክ ተመስሎ የአውሮጳውያንን የበላይነት ሲያስረዳ እንዲህ ይላል።

> *ልዑል ሆይ፣ እነሱ ከኛ የበለጠ ኃይል ያገኙት ከኛ የበለጠ ብልሆች ስለሆኑ ነው። ሰው እንሰሳን እንደሚገዛ መቸውንም ቢሆን እውቀት ድንቁርናን ይገዛል። የነሱ እውቀት ከኛ እውቀት የበለጠ የሆነበት ምክንያት ግን የማይመረመረው የታላቁ ጌታ ፈቃድ ነው ከማለት በተቀር ሌላ ምክንያት እንደሚሰጠው አላውቅም።*

ፕሮፌሰር ጆንሰን ምናልባት በጥላቻ ደም ካልተበከሉት የአውሮጳ ሊቃውንት አንዱ ሳይሆን አይቀርም። ሆኖም ከሱ አስተሳሰብ ተነስቶ ጥላቻ ሀይማኖታቸው የሆኑት አውሮጳውያን ምን እንደያስቡ መገመቱ አያዳግትም። ስለዚህ፣ ለኔ እንደሚታየኝ ማህበራችን የጥቁር ሰዎች ማህበር መሆን አለበት። በመህከላችን ጊዜ የማይሽረው ልዩነት የለምና፣ አላማችን ማተኮር ያለበት በዚያ አቅጣጫ ነው።

ይህንን የጥቁር ህዝብ ማህበር ለማቆም ጠላቶቻችን ያበጁልን መሰናክል ብዙ ነውና፣ እጅግ ከባድ ነው። ስለዚህ

ከምንችለው ተጀምሮ ቀስ በቀስ መገንባት ይኖርበታል። በመጀመሪያ በግለ ሰቦች መሀከል መቃቃር ሳይፈጠር ኢትዮጵያችን የታፈረችና የተፈራች አገር የምትሆንበትን ብልሀት መርምረን ማግኘት ያስፈልገናል።

ማህበር የሚለውን ቃል እስካሁን የተጠቀምኩበት ሳይደነግግ ስለሆነ እንደሚከተለው እደነግገዋለሁ። ማህበር በተለያየ ጊዜና ሁኔታ ብዙ ትርጉም ሊኖረው ይችላል፤ አለውም። እኔ ግን "በዛሬው ጉባኤ ላይ ማህበር ስል ምን ማለቴ ነው?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንጅ ማህበር ለሚለው ቃል ቀዋሚ ትርጉም ለመስጠት አይደለም። እግዴህ ማህበር ስል የሌላ ስብስብ አባላትን የግል መብት የማያከብር ስብስብ ማለቴ ነው።

ሀገር ብለን የምንጠራቸው የሰዎች ስብስቦች ገሚሱ ይህንን ድንጋጌ ይከተላሉ። ለምሳሌ አሜሪካን ብንመለከት፣ የራሱ ዜጎች የግል መብት ከሞላ ጎደል እኩል ነው። ዴሞክራሲ የሰፈነበት ስርአት ነውም ይባላል። ነገር ግን ከሌሎች ሀገሮች ጋር የሚያደርገው ግንኙነት አምባ ገነናዊ ነው። የሌሎች ሀገሮች ዜጎችን የግል መብት እንኩዋን ከፈስ ከቁቅም አይቆጠረው።

ወደ እኛው ሀገር ልመለስና፤ ቅድም የምንጀምረው ከእምነት ነው ብዬ ነበርና፣ በሚከተሉት መሰረታዊ እምነቶች እንስማማ።

ድንጋጌ፡ አሁን ኢትዮጵያ ብለን የምንጠራውን ምድር ያበሻ አገር፣ ህዝቡንም አበሻ እንበለው።

ህግ፡ 1. ያበሻ ምድር ለያንዳንዱ አበሻ እኩል ይደርሰዋል።

2. እያንዳዱ አበሻ የሌላውን መብት እስካልነካ ድረስ፣ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን የግል መብት አለው። የግል መብቱን፣ለተወሰነ ጊዜ ለሌሎች አሳልፎ መስጠትም መብቱ ነው።

3. የሌላውን መብት ያለፈቃዱ የገፈፈ አበሻ፣ መብቱን ያለፈቃዱ ይገፈፋል። »

«ታዲያ እነዚህን ህግጋት በግብር ለመግለፅ አስቸጋሪ አይመስልህም?» አሉ አጤ ቴዎድሮስ። አጤ ቴዎድርስ እስካሁን በጥሞና ያዳምጡ ነበር። የተቀመጡትም በስተምእራብ ያለው መደብ ላይ ነበር። በግራቸው ነብር፣ በቀኛቸው ደግሞ አንበሳ አስቀምጠዋል። እርሳቸውም እንደዙፋን መደገፊያ ሁሉ እጆቻቸውን ጣል አድርገውባቸዋል።

«አወን ጃነሆይ» አለ ተናጋሪው፣ «በጣም አስቸጋሪ ነው። ቢሆንም እውነት ያለችው ከነዚህ ህግጋት ጋር ነውና፣ ህይወታችን ትርጉም የሚያገኘው ወደዚያ ለመድረስ በምናደርገው ጥረት መሆን ይገባዋል።

ምሳሌ ልስጥዎ፣ አንድን ሜትር በትክክል ለመለካት የሚችል ሰውም ሆነ መሳሪያ በምድር ላይ የለም። በኩል (Universe) ውስጥ መኖሩንም እጠራጠራለሁ። ግን በትክክል መለካት አይቻልም ብለን፣ ወርዱ አንድ ሜትር የሆነን ሳንቃ፣ ሁለት ሜትር የሚሰፋ መቃን ላይ ለመግጠም አንታገልም፣ የመቃኑና የሳንቃው ስፋት የመለካት ችሎታችን እስከፈቀደ ድረስ እኩል እንዲሆኑ እንጥራለን እንጅ። የተሻለ የመለኪያ መሳሪያ ስናገኝ ደግሞ፣ ስህተታችንን ለማረም የማንም ፈቃድ አያስፈልገንም፤ ስህተትን እያረሙ ወደ እውነት መራመድ የተፈጥሮ ሂደት ነውና።

እዚህ ላይ፣ የእውነትን ምንነት መጠየቅም ይቻለል። ነገር ግን አባቶቼ፣ እናቶቼ አስፈላጊ መስሎ ከታያችሁና ሌላ እድል ከሰጣችሁኝ የእውነትንና የውበትን ምንነት ለሌላ ጊዜ ባስተላልፈው እወዳለሁ። ለጊዜው ግን፣ የሁሉም ነገር መሰረቱ እምነት ወይም ውበት ነው ብንልም፣ እውነት

በቀላሉ የማይፋለስ እምነት ነው ብንል ይበቃል፡፡»

«ገብቶኛል ልጄ፤ ገብቶኛል፡፡» አሉ አጤ ቴዎድሮስ፡፡ «አሁን ለመፍታት የምንጥረው የኢትዮጵያን ችግር ነው፡፡ የኢትዮጵያን ችግር የመፍቻው እውነት ደግሞ ያን ያህል የረቀቀ አይመስለኝምና፣ የምትለው ገብቶኛል፡፡ ቀጥል፡፡»

ተናጋሪውም ቀጠለ፡፡

«እንግዴህ ኢትዮጵያን ከግለሰብ ጀምሮ መገንባቱ፣ ለእውነት የቀረበ ቢሆንም፣ አጤ ቴዎድሮስ እንዳሉት፣ ተግባራዊ ለማድረግ ባለንበት ዘመንና ሁኔታ ያስቸግራል፡፡ በዚያም ላይ ግለሰብ ለብቻው መኖር አይችልምና እንዲያ ማድረጉ አስፈላጊም አይደለም፡፡ ስለዚህ ንኡስ ማህበር ተፈጥሮ የግለሰቦች መብት የማይነጠቅበት፣ ነገር ግን ማህበሩ ራሱን ችሎ በነፃነት ሊኖር የሚችልበት (ቢያንስ እችላለሁ ብሎ የሚያስብበት) አማካይ የሚዛን ነጥብ ወይም እርካብ (Fulcrum) ማግኘት ከስራችን የመጀመሪያው ክፍል ነው፡፡

ቀበሌ የሚባለው የመልክአ ምድር ክልል ለእንደዚህ አይነቱ ማህበር ይሆናል ብለው የሚያምኑ አሉ፡፡ እኔ እንኩዋን ወረዳ ይበቃል የሚል እምነት ነበረኝ፡፡ ግን የሚቻል ከሆነ፣ ቀበሌ ከወረዳ ይልቅ ለግለሰብነት ይቀርባል፡፡ ዋናው ነገር፣ የምንመርጠው ክልል ነዋሪዎች የተፈጥሮም ሆነ ባህላዊ ጠባያቸው ተመሳሳይ መሆኑ ነው፡፡ የእያንዳንዱም ቀበሌ እድል በያንዳንዱ ቀበሌ ነዋሪዎች ይወሰናል፡፡»

«ቅድም የልጄን ስም ስትጠራ ደስ ብሎኝ ነበር፡፡ የኢትዮጵያም አምላክ በህይወት እያለህ ፊትዋን ትመልስልህ ብዬ ልመርቅህ ፈልጌ ነበር፡፡ ጊዜህን እንዳላባክ ን ብዬ ነበር የተውኩት፡፡» አሉ ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደስላሴ፡፡ «አሁን ግን ጥያቄ ስላለኝ እግረመንገንዴን ልመርቅህ ብዬ ነው፡፡»

«አሜን» አለ ተናጋሪው፣ «አሜን አባቴ።»

ብላቴን ጌታም ቀጠሉ «የቀበሌው ድንበር እንዴት ይወሰናል? ማንስ ይወስነዋል? የቀበሌውስ ነዋሪ ማን ነው?»

«በእርግጥ ከባድ ጥያቄ ነው።» አለ ተናጋሪው። «ፀሀፊዎች ያሰቡትን የሚፅፉት፣ ፈላስፋዎች በየአደባባዩ የሚከራከሩት፣ እንዚህን መሰረታዊ እምነቶች ጊዜው ሲደርስ ያለክርክር ተቀባይነት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። እነዚህን መሰረታዊ እምነቶች ካልተቀበልንማ ኢትዮጵያ የሚባለውን ማህበር ለመገንባት ጊዜው አልደረሰም።

እዚህ ላይ፣ ዛሬ ልናገርበት እኩዋን አልተዘጋጀሁም፣ ግን ጥያቄዎ ስላሳሰበኝ አንድ ሌላ ሀሳብ ላምጣ። አንድ ግለሰብ ያለፍላጎቱ ነፃነት ቢሰጠው፣ ነፃነቱ እንደባርነት ይቆጠራል ወይ? በኔ አስተሳሰብ ነፃነት ምንጊዜም ነፃነት ነው። ያለፍላጎት የተሰጠ ነፃነትም ነፃነት እንጅ ባርነት ሊሆን አይችልም። ስለዚህ በጎ ፈቃድ ያላቸው ጥቂት ኢትዮጵያውያንም ቢሆኑ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነቱን ሊያስገኙለት ይችላሉ። ግለሰብ "ነፃነትን ወይስ ባርነትን ትመርጣለህ?" ተብሎ አይጠየቅም፤ ድቁርና ካልሆነ በስተቀር ባርነትን ሰው ለምን ይመርጣል?። ስለዚህ ነፃነትን በግድ ማጎናፀፍ፣ ማስማር እንጅ ማስገደድ አይደለም። ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ መሰረታዊ እምነቶችን የነፃነት ቀን ከመድረሱ በፊት አውቆዋቸውና አምኖባቸው ይጠብቃል፤ ያለዚያም በነፃነት ዋዜማ ይማራቸዋል። »

«ብዙዎች አሁን ያልከውን ከአምባ ገነንነት የሚለዩት አይመስለኝም።» አሉ አቶ ይልማ ደሬሳ፣ «ነፃነት ማለት፣ አንድ ግለሰብ ፍላጎቱን በነፃ መምረጡ ነው። ስለዚህ ግለሰብ በሀይልም ቢሆን ነፃ ምርጫ እንዲኖረው ማድረግ አምባገነንነት ሊሆን ፈፅሞ አይችልም።»

«አዎን አቶ ይልማ» አለ ተናጋሪው «የኔም እምነት እንደርሶ ነው፡፡ ግለሰብ ለማህበሩ ደህንነት ሲል ከራሱ ቀንሶ ለማህበሩ የሚያስተላልፈው የግል መብት እንኩዋን ለዘለቄታው መሆን የለበትም፡፡ ያ፣ ባርነትን መምረጥ ነውና ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡

በመጨረሻም ሁለት መሰረታዊ ውሳኔዎችን ማሳለፍ ያስፈልጋል፡፡ መሰረታዊ እምነቶች ያላልኩበት ምክንያት ሊለወጡ ስለሚችሉ ነው፡፡ በተጨማሪም የብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ስላሴን ጥያቄዎች ለመመለስ ይረዱኛል፡፡

፩. የቀበሌው ነዋሪ ማነው?
አንድ አመት በአንድ ቀበሌ የኖረ አበሻ ሁሉ የዚያ ቀበሌ ነዋሪ መሆን ከፈለገ፣ የዚያ ቀበሌ ነዋሪ ነው፡፡ ሆኖም አንድ ሰው በአንድ ጊዜ የሁለት ቀበሌ ነዋሪ መሆን አይቻለውም፡፡

፪. የሁለት ቀበሌ የጋራ ድንበር በብዙ ደረጃ ሊወሰን ይችላል፡፡

ሀ. ከቀድሞ ዘመን ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው የቀበሌ ድንበር እንጀምራለን፡፡
ለ. አለመስማማት ከተፈጠረ ከሁለቱ ቀበሌዎች የተውጣጡ ያገር ሽማግሌዎች ይወስናሉ፡፡
መ. ይህም ሆኖ አንዳንድ ድንበር ላይ ያሉ ቦታዎች በየትኛው ክልል እንደሆኑ መወሰን ካስቸገረ፣ አጨቃጫቂው ቦታ ላይ የሚኖሩ ሰዎች ቀበሌያቸውን ይመርጣሉ፡፡

እዚህ ላይ ከኔ እውቀትም ሆነ ጊዜ ውጭ የሆኑ ብዙ ከነፃነት ቀን በፊት ልንማራቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ፡፡ የወንዞች ባለቤትነትና አጠቃቀም፡፡ ከምድር በታች ያለውን ባህር፣ ከመሬት በላይ የሚፈሰውን ውሀና የምንተነፍሰውን አየር

መበከልን፤ የቀበሌዎችን ደህንነት የሚያሰጋ የውጭ ጦር አምጥቶ ማስፈርን የመሳሰሉ ድርጊቶች ከነፃነት በፊት በዝርዝር ተጠንተው አከራካሪ ከመሆን መወገድ አለባቸው።

እርግጥ ማንኛውም ነፃ ሀገር የፈለገውን ባገሩ ማድረግ ይችላል። ነገር ግን ጎረቤቱ የሚተነፍሰውን አየርም ሆነ የሚጠጣውን ውሀ መበከል አይገባውም። እንዲያ ያደረገ አገር፤ የጎረቤቱን የግል መብት ያለፍላጎቱ ነጥቅዋልና ከመሰረታዊ ህጎቻችን ጋር አይጣጣምም።

ንግግሬን ለማጠቃለል፤ የነፃነት ቀን ሲመጣ፤ ለያንዳንዱ ቀበሌ የሚቀርበው ጥያቄ ቀላል ነው። "ኢትዮጵያዊ ናችሁ ወይስ አይደላችሁም?" ይህ እኔ የጀመርኩት ፍልስፍና አይደለም። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምን ብትጋብዙዋቸው በሰፊው ያስረድዋችሁዋል። አይደለንም ያሉትን እንተዋቸው። የኢትዮጵያውንን የግል መብት የሚፃረር ድርጊት እስካልፈፀሙ ድረስ በሰላም ልንሰናበታቸው ይገባል።»

ተናጋሪው ንግግሩን ፈፀመና በስተደቡ ያለው መደብ ላይ ተቀመጠ።

ኮሽ የሚል ድምፅ እንኩዋን አይሰማም። አባቶች ሁሉ ከተቀመጡበት እንዳቀረቀሩ ቀሩ። በመጨረሻም መደቡና ያካባቢው ኮረብታ ብርሀን ሆነ። አንድም ሰው አልተቀመጠበትም። ተናጋሪውም የለም። እኔና ፕሮፌሰር አስራት ብቻ ቀረን። እኛም ብንሆን፤ የነበርነው ከመደቡ ሳይሆን በስተደቡብ ባለው ኮረብታ ላይ ነበር።

«በል እንግዲህ እኔም ልሰናበትህ ነው። ከዚህ ያየህ የሰማኸውን ፃፍ። የነፃነት ቀን ከመድረሱ በፊት ብዙዎች መማር አለባቸው። ባለመማረችን ነው ነፃነትን ከባርነት መለየት ያቃተን።» አሉኝና ፕሮፌሰር አስራት ወደዚያ ዘለአለማዊ ወደሆነ የመንፈስ አለም ተመለሱ።